ዐዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሂዩማኒቲስ የቋንቋዎች ጥናት የጆርናሊዝም እና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል
የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

# ሥዕል በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን

በ
ሕይወት በየነ

መጋቢት ፳፻፲፮ ዓ.ም
አዲስ አበባ

# ሥዕል በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን


ዐዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ የቋንቋዎች ጥናት የጆርናሊዝም እና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ መረቃ መርሐ-ግብር


ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር የኤም.ኤ.ዲግሪ ከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት


በ

ሕይወት በየነ

አማካሪ

ዘላለም መሠረት(ዶ/ር)



ታሕሳስ ፳፻፲፮ ዓ.ም

አዲስ አበባ

**ዐዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ**

**የሂዩማኒቲስ የቋንቋዎች ጥናት የጆርናሊዝም እና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ**

**የአማርኛ ቋንቋ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል**

**የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር**

# ሥዕል በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን

**በ**

**ሕይወት በየነ**

የፈተና ቦርድ አባላት

አማካሪ ስም ------------------------------------------------------------ ፊርማ ---------------------

የውስጥ ፈታኝ ስም ---------------------------------------------------- ፊርማ ---------------------

የውጭ ፈታኝ ስም ----------------------------------------------------- ፊርማ ---------------------

ማውጫ ገጽ


ምስጋና ........ iv
አጠቃሎ ........ v
መግለጫዎች ........ vii
ምዕራፍ አንድ ........ 1
መግቢያ ........ 1
፩.፩ የጥናቱ ዳራ ........ 2
፩.፪ የጥናቱ አነሣሽ ምክንያት ........ 3
፩.፫ የጥናቱ ዐላማ ........ 3
፩.፬ የምርምር ጥያቄዎች ........ 4
፩.፭ የጥናቱ ጠቀሜታ ........ 4
፩.፮ የጥናቱ ወሰን ........ 5
፩.፯ የጥናቱ ዘዴ ........ 5
፩.፰ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ ........ 7
፩.፰.፩ ምልከታ ........ 7
፩.፰.፪ ቃለ መጠይቅ ........ 8
፩.፰.፪ የቡድን ተኮር ውይይት ........ 9
፩.፰.፫ በመስክ ላይ ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሔዎች ........ 9
፩.፰.፬ የጥናቱ አደረጃጀት ........ 10
ምዕራፍ ኹለት ........ 11
፪. የድርሳናት ክለሳ ........ 11
፪.፩ የንድፈ ሐሳብ ቅኝት ........ 11
፪.፩.፩ ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ ........ 11
፪.፩.፪ ሥነ ልቡናዊ ንድፈ ሐሳብ ........ 12
፪.፩.፫ የሥዕል ምንነት ........ 12
፪.፩.፬ ሥዕል እና ፎክሎር ........ 13

፪.፩.፭ የሥዕል አጀማመር በኢትዮጵያ ........ 14
፪.፩.፮ የሥዕል አጀማመር በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ........ 15
፪.፩.፯ የሥዕል ጥቅም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ........ 19
፪.፪ የቀደምት ጥናቶች ቅኝት ........ 19
፪.፫ የታተሙ ተዛማጅ ጥናቶች ........ 24
ምዕራፍ ሦስት ........ 28
፫.፩ የቤተ ክርስቲያን ምንነት ........ 28
፫.፪ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የቀለማት ትርጉም ........ 28
፫.፫ የትውፊት ምንነት ........ 31
፫.፬ የኢትዮጵያ ጥንታዊ ሥዕል ትምህርት ........ 33
ምዕራፍ አራት ........ 36
፬.፩ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የቅዱሳት ሥዕላት አሣሣል. 36
፬.፪ ቅዱሳት ሥዕላት ........ 36
፬.፫ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሥዕል አሣሣል ........ 36
፬.፫.፩ ልደት ........ 36
፬.፫.፪ ሥነ ሥቅለት ........ 37
፬.፫.፫ ትንሣኤ ........ 38
፬.፬ የቅድስት ሥላሴ አሣሣል ........ 38
፬.፭ ምስለ ፍቁር ወልዳ አሣሣል ........ 40
፬.፮ ኪዳነ ምሕረት አሣሣል ........ 44
፬.፯ የቅዱሳን መላእክት አሣሣል ........ 45
፬.፰ የቅዱሳን ነቢያት አሣሣል ........ 47
፬.፱ ቅዱሳን ሐዋርያት ........ 48
፬.፲ ቅዱሳን ሰማዕታት ........ 48
፬. ፲፩ ቅዱሳን ጻድቃን ........ 50

፬. ፲፪ የቅዱሳን እና የርኩሳን ሥዕላት አሣሣል ........................................................................ 51
፬. ፲፫ የቅዱሳት ሥዕላት አቀማመጥ ........................................................................ 52
፬. ፲፬ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሥዕል ትምህርት አሰጣጥ ኹኔታ አኹን ባለንበት ዘመን ........................................................................ 53
፬. ፲፭ ሥዕል ለመሣል የሚያስፈልጉ ቅድመ ኹኔታዎች ........................................................................ 54
፬. ፲፮ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሥዕል ከዓለማዊ ሥዕል ጋራ ያለው ልዩነት 55
፬. ፲፯ የቀለም አጠቃቀም ........................................................................ 56
፬. ፲፰ ኦርቶዶክሳዊ ትውፊትን ጠብቀው የተሣሉ ሥዕሎች ........................................................................ 56
፬. ፲፱ የቤተ ክርስቲያን ሠዓሊዎች ኹኔታ ........................................................................ 57
፬. ፳ የቅዱሳት ሥዕላት ተአምር ........................................................................ 57
ምዕራፍ ዐምስት ........................................................................ 59
፭. ማጠቃለያ ........................................................................ 59
አስተያየት ........................................................................ 60
ዋቢ መጻሕፍት ........................................................................ 61
አባሪ ፩ የተለያዩ ፎቶዎች ........................................................................ 64
አባሪ ፪ ........................................................................ 65
አባሪ ፫ መረጃ ሰጪ ........................................................................ 65
አባሪ. ፬ ለመረጃ ለመሰባሰብ የተዘጋጁ ጥያቄዎች ........................................................................ 67

# ምስጋና

ከኹሉ አስቀድሜ እስከዚች ሰዓት ድረስ ለጠበቀኝ እና ይኽን ጥናት እንዳጠንቅቅ ለረዳኝ ለቸሩ እግዚአብሔር ምስጋናዬን አቀርባለኹ፡፡የትምህርት ዕድሉን ለሰጠኝና ይኽን ጥናት እንዳደርግ በመፍቀድ በተለያዩ ጉዳዮች የደገፈኝ ዐዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ አመሰግናለኹ፡፡

ይኽ ጥናት እዚኽ ደረጃ እስኪደርስ ድረስ ጊዜያቸውን ሰውተው አቅጣጫ በማሳየትና ረቂቁን በማረም ላጋጠሙኝ ችግሮች መፍትሔ በመጠቆም እገዛ ላደረጉልኝ አማካሪዬ ዶ/ር ዘለዓለም መሠረት ምስጋናዬን ከልብ አቀርባለኹ፡፡አክብሮቴም ከፍ ያለ ነው፡፡

መረጃ ለመሰብሰብ በምስቀሳቀስበት ወቅት የምፈልገውን መጻሕፍት ሳይሰለቹ በመፈለግ ተባበሩኝ ለዐዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ቤተ-መጽሐፍት ባለሙያዎች፣የቅድስት ሥላሴ ዩኒቨርስቲ ቤተ-መጽሐፍት ባለሙያዎች፣የቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ መዘክር ቤተ-መጽሐፍት ባለሙያዎች እና የማኅበረ ቅዱሳን ቤተ-መጻሕፍት ባሙያዎችን ምስጋናዬ ይድረሳችኹ፡፡ በማኅበረ ቅዱሳን የሥነ ሥዕል ክፍል ባለሙያ የኾነው ለቃለ መጠይቅ ፈቃደኛ በመኾን የተባበረኝ እና ጽሑፌን ባስተካከልና መረጃ በመስጠት ያገዘኝን ኃይለማርያም ሽመልስን እጅግ አድርጌ አመሰግናለኹ

ይኽን ጥናት ለማካኼድ ኹልጊዜ የሚያበረታቱኝ ቤተሰቦቼ እንዲኹም በተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት በመኼድ መረጃ ለመሰብሰብ የመስክ ጉዞ ባደረግኹበት ወቅት አብራኝ በመጓዝ፣ቪድዮ በመቅረጽ፣ፎቶ በማንሳት፣ሐሳብ በመስጠት እገዛ ላደረገችልኝ እህቴ ትዕግስት በየነ እጅግ አድርጌ አመሰግናለኹ፡፡

ጽሑፌን በማስተካከል፣አስተያየት በመስጠት ሲያበረታታኝ የነበረው ባልደረባዬ ሞላልኝ ሽታሁን እና ሌሎችም የሥራ ባልደረቦቼ አብራችሁን ለነበራችሁ በሙሉ እጅግ ከልቤ አመሰግናችኋለኹ፡፡

## አጠቃሎ

ይኽ ጥናት ሥዕል በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ-ክርስቲያን በሚል የተጠና ነው፡፡የጥናቱ መረጃዎች የተሰበሰቡት በዋናነት በምልከታ፣የቅዱሳት ሥዕላት ባለሙያ ጋራ በቃለ መጠይቅ በማድረግ፣ቅዱሳት ሥዕላት በተመለከተ የተጻፉ ጋዜጣ፣መጽሔት እና መጻሕፍትን በማንበብ፣ የሥዕል ዐውደ ርእይና ዐውደ ጥናት ላይ በመሳተፍ፣በየመደብሩ የሥዕላት መሸጫ ቦታዎች ላይ ምልከታ በማድረግ እንዲኹም በየአብያተ ክርስቲያኑ የሚገኙትን ቅዱሳት ሥዕላትን በመመልከት ነው፡፡በነዚኽ ዘዴዎች የተሰበሰቡት መረጃዎች ጥናቱ ሥዕል በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ-ክርስቲያን ያለውን አገልግሎትና የአሣሣል ሥርዐት ለማሳየት ዐላማ አድርጎ በመነሣቱ የአሣሣል ሥርዐቱን ለማሳየት ተግባራዊ እና ሥነ-ልቡናዊ ንድፈ ሐሳብን ተጠቅሟል፡፡በተግባራዊ እና ሥነ-ልቡናዊ ንድፈ ሐሳብ አቅጣጫ መሠረትም በገላጭ ምርምር ስልት መረጃዎች ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ቅዱሳት ሥዕላት የሚያስገኙት ጥቅም፣የቅዱሳት ሥዕላት አሣሣል ታሪካዊ አመጣጥ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የኾነ ትእዛዝ ያለው መኾኑንና ከጥንት ጀምሮ ሥዕሎቹ ትውፊትን መሠረት በማድረግ የሚዘጋጁ ሲኾን አኹን ባለንበት ዘመን ግን ትውፊትን ያልጠበቁ እና የእምነቱን አስተምህሮ የማይገልጹ ቅዱሳት ሥዕላት መኖራቸው በጥናቱ ላይ ተረጋግጧል፡፡ቅዱሳት ሥዕላት ከመሣላቸው በፊት ከሠዓሊው የሚደረጉ ቅድመ ዝግጅቶች አሉ፡፡እነሱም፡-ንስሓ መግባት፣ሥዕላቱ የሚዘጋጁት በእግዚአብሔር ፈቃድ በመኾኑ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመጠየቅ ጸሎት ማድረግ፣ሥዕሉን ለማዘጋጀት የሚያስፈልጉትን ቁሳቁሶች ማስባረክ እንደሚያስፈልግ ጥናቱ አሳይቷል፡፡ሠዓሊው መሠረታዊ የኾነ የመንፈሳዊ ዕውቀት ያለው፣ሥዕሎችን የመመልከት፣ሥዓሎቹ የሚሣሉት ከመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ መነሻ በማድረግ በመኾኑ ገድላትን ስንክሳርን የማንበብ ልምድ ያለው መኾን እንዳለበት በዚኽ ጥናት ተረጋግጧል፡፡ኾኖም ግን አኹን ባለንበት ዘመን ይኽ ቅድመ ዝግጅት እየተደረገ እንደማይዘጋጅ እና የቤተ-ክርስቲያን አሠሪ ኮሚቴዎችም ሥዕሎችን እንዲሣሉ ማድረጋቸውን እንጂ ትውፊቱን የጠበቁ ቅዱሳት ሥዕላት እንዲዘጋጁ እንደማያደርጉ በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡ከሥዕሎቹ ጭብጥ ጋራ የማይዛመዱ ቅዱሳት ሥዕላትንም በስህተት የሚጠሩበት ሥያሜ እና ታሪካቸው የሚለያዩ መኾናቸውን በዚኽ ጥናት ተለይቷል፡፡ይኸውም አኹን ባለንበት ዘመን ኪዳነ ምሕረት ተብለው የሚታዩት ሥዕሎች የማርያምን ንግሥና ስትቀበል የግብጽ የመገለጧ ማርያም የሚያሳዩ ናቸው እንጂ ቃልኪዳን ስትቀበል የሚያመለክት አለመኾኑንና ትክክለኛውን የኪዳነ ምሕረት ምሥል የትኛው እንደኾነ ተለይቷል፡፡በጥንት ዘመን የሥዕል ትምህርት የቀድሞ አባቶቻችን ከፍተኛ የኾነ ትምህርተ ክርስትና የነበራቸው በመኾኑ የሚሥሏቸው ሥዕሎቹ ከትምህርተ ክርስትና ጋራ እንደማይጋጩ

*በአኹኑ ዘመን ግን የሚታዩት ሥዕሎች መሠረታዊ የኾኑ የእምነቱን አስተምህሮ የማይገልጹ እንደኾኑ ተረጋግጧል፡፡ቅዱሳት ሥዕላት በተመለከተ ትምህርት እየተሠጠ እንዳልኾነ፣በየቤተ ክርስቲያናቱ ሰንበት ትምህርት ቤትና በየዐውደ ምሕረቱ ላይ የተሰበከ ትምህርት አለመኖሩን፣በዚህ ርእሰ ጉዳይ ላይ የተጻፉ መጻሕፍት ጥቂት መኾናቸውን በተጨማሪም በመንፈሳዊያት ዩኒቨርስቲዎች ሥዕል ራሱን ችሎ ትምህርት እየተሠጠ አለመኾኑን ጥናቱ አሳይቷል፡፡የሥዕል ትምህርት ቤቶች አኹን እያስተማሩ ያሉት በማኅበረ ቅዱሳን ሥነ-ጥበብ ክፍል፣በሐመረ ብርሃን፣በገርጂ ማርያምና እግዚአብሔር ምስሌነ ደብረገሊላ ብዙ ሥራ እየሠሩ እንደሚገኙ ታይቷል፡፡*

**መግለጫዎች**

*ሥዕል ፩ የክርስቶስ ልደት*

*ሥዕል ፪ የክርስቶስ ስቅለት*

*ሥዕል ፫ የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ሥዕል*

*ሥዕል ፬. የቅድስት ሥላሴ ሥዕል*

*ሥዕል ፭. ምስለ ፍቁር ወልዳ*

*ሥዕል ፮ የኪዳነ ምሕረት ሥዕል*

*ሥዕል ፯. ቅዱስ ሚካኤል*

*ሥዕል ፰ የሕዝቅኤል ሥዕል*

*ሥዕል ፱. የቅዱስ ማርቆስ ሥዕል*

*ሥዕል ፲. የሰማዕቱ ቅዱስ ጊዮርጊስ*

*ሥዕል ፲ወ፩. ጻድቁ ተክለ ሃይማኖት*

**ሙዳየ ቃላት**

*መላእክት፡- ማለት የቃሉ ትርጒም የእግዚአብሔር መልእክተኞች፣ተላላኪዎች፣አለቆች ማለት ነው፡፡*

*ነቢያት፡-ቀድሞ ከሔኖክ ኋላም ከሙሴ ዠምሮ እስከ ጌታችን የነበሩትንቢተኞች፣ትንቢትተናጋሪዎችና ደጋጎች ሰዎች ኀላፍያትንና መጻእያትን የሚያውቁ በሕዝብ አነጋገር ነቢያት ይባላሉ*

*ሐዋርያት፡ማለት በደስታ ተክለወልድ መዝገበ ቃል እንደተገለጸው ብዙዎች መንገደኞች፣መንገድ ዐላፊዎች፣የወንጌል መልእክተኞች፣ሰባኪዎች የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት፣አስቀድሞ ዓሣ አሥጋሪ- ልብደ-ሠሪ በቅሎ ገሪ የነበሩ አርድእት፣፲፪ ሐዋርያት እንዲሉ*

*ሰማዕት፡- የሚለው ስም ‹‹ሰምዐ›› ሰማ፣አደመጠ፣አስተዋለ፣ ተቀበለ፣መሰከረ፣ምስክር ኾነ ያየውን የሰማውን ተናገረ፣ዐየ'ኹ ሰማ'ኹ አለ ከሚለው ግስ የወጣ ቃል ነው፡፡*

*ሰማዕት ማለት፡- ምስክሮች ሰማዕቶች፣ሃይማኖታቸውን መስክረው በሰማዕትነት የሞቱና የሚሞቱ ማለት ነው፡፡*

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

የሰው ልጆች ሐሳባቸውን በተለያየ መንገድ  ይገልጻሉ፡፡ ሐሳባቸውን ከሚገልጹባቸው መንገዶች መካከል አንዱ በጽሑፍ(በሥዕል) ነው፡፡ጽሑፍ ከመጀመሩ በፊት ሰዎች ሐሳባቸውን መግለጽ የጀመሩት በሥዕል ነው፡፡በተለይ ደግሞ በእምነት ቦታዎች የሥዕል አገልግሎት ብዙ ነው፡፡ሥዕል የእምነቱን ተከታዮች በእምነት እንዲመሠጡ  ያደርጋቸዋል፡፡ሰዎች በጽሑፍ ያልተረዱትን በሥዕል፣በሥዕል ያልተረዱትን በጽሑፍ  ሊረዱት ይችላሉ፡፡አንድን መልእክት በቃል መረዳት ካልቻሉ በሥዕል ሊገነዘቡት ይችላሉ፡፡በመኾኑም ሥዕል በጽሑፍ ሊረዱት ያልቻሉትን ነገር ለመግለጽ ያስችላል ማለት ይቻላል፡፡ሚሊዮን በለጠ ‹‹ቅዱሳት ሥዕላት›› በሚለው መጽሐፉ ላይ ሥዕልን ሲገልጽ ‹‹ሥዕል ብዙ ነገርን ማመልከቻ፣የማንኛውም ነገር አምሳያ ሲኾን በቀለም ቅብ የሚዘጋጅ ማለት ነው››ይላል፡፡ይኽ አገላጽም የሥዕል ጥቅም በርካታ መኾኑን የሚያመለክት ነው፡፡ሥዕላት በገድላት፣በድርሳናት፣በዜና መዋልሎችና ሃይማኖታዊ ጽሑፎች ላይ የተለመዱ ናቸው፡፡

ሥዕል በተለያዩ እምነቶች ውስጥም ለማስተማሪያነት ያገለግላል፡፡በመኾኑም በየእምነቶቹ ውስጥ የሥዕል ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው፡፡ ይኽም በየእምነቱ ሥርዐት ውስጥ ለማስተላለፍ የሚፈልጉትን መልእክት ለማስተላለፍ ይረዳል፡፡ ተመልካቹም ርእሰ ጉዳዩን ለመረዳት ይችል ዘንድ ትኩረትን ለመስጠት ይጠቅማል፡፡በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ውስጥም ሥዕላት የሚሰጡት ጥቅም ከፍተኛ ነው፡፡ሚሊዮን በለጠ ‹‹ቅዱሳት ሥዕላት›› በሚለው መጽሐፍ ላይ ‹‹ቅዱሳትሥዕላት›› የሚለው የከበሩ የተለዩ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ፣የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያምና፣የቅዱሳን መላእክት የነቢያትና የሐዋርያት ፣የጻድቃንና ሰማዕታት ሥዕላት ናቸው›› በማለት ይገልጻል፡፡

የዚኽ ጥናት ውስጥም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ውስጥ የሚገኙ ቅዱሳት ሥዕላትን በተመለከተ ያላቸውን አገልግሎትና ጥቅም እና የመጀመሪያው ሠዓሊ ማን እንደኾነ እና ለመጀመሪያ ጊዜ ሥዕልን የሣሉ እነማን እንደኾኑ ይገልጻል፡፡

ከዚኽ በተጨማሪም የቅዱሳት ሥዕላት አሣሣል እና ከሠዓሊው የሚጠበቁ ሥነ ሥርዐቶችን እንዲኹም የሥዕልን አመጣጥ ይገልጻል፡

## ፩.፩ የጥናቱ ዳራ

የዚኽ ጥናት ትኩረት ሥዕል በመኾኑ ሥዕል ላይ የተጻፉ ጽሑፎችን መመልከት ያስፈልጋል፡፡የተለያዩ ጸሐፍት ሥዕልን በተለያዩ ዘመናት የተለያዩ ፍቺዎችን ሰጥተዋል፡፡ከተሰጡት ትርጉም መካከልም ሞገስ ዕቁበ ጊዮርጊስ አንጋረ ፈላስፋ በሚለው መጽሐፋቸው ላይ ሲገልጹ ‹‹ያልሞተ ሰው የሚንቀሳቀስ ሬሳ ነው››ይላሉ ‹‹ሰው እና ሥዕል፣አካልና ምስል››በማለትም በምናየው እና በማናየው አካል በሚተረጉሙ እና በትርጉሙ መካከል ያለን ወሰን እና ዝምድና የሚያሳይ የአስተማስሎ ዕምቅ መልክም የሚገልጽ ሐሳብ ሰጥተዋል፡፡አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ በመጽሐፈ ሰዋስው ወግስ መዝገበ ቃላት ላይ‹‹ሥዕል በቁም መልክ፣የመልክ ጥላ፣ንድፍ፣አምሳል፣ንድፍ በውሓ በመጽሔት፣በጥልፍ፣በስፌት ወይም በቀለም በወረቀት ገዝፎ ተጽፎ ከደብር፣ከእብን፣ከእድ፣ከማዕድን ታንጦ፣ተቀርጦ፣ተሸልሞ፣አጊጦ የሚታይ የሚዳሠሥ ነገር ነው››በማለት ገልጸውታል፡፡

ጣሊያዊው ፈላስፋ (Bendetto Croce)‹‹የሰውን ልጅ ደመ ነፍስ ሥግው የሚያደርግ ኪናዊ ክዋኔ ነው፡፡››በማለት ይገልጻል፡፡አሜሪካዊው ፈላስፋ ደግሞ (Suzanne Langer)‹‹ሰብአዊ ስሜቶች በትእምርት የሚቀረጹበት ፈጠራ ነው››ይላል፡፡ሥዕል እንደየደራሲዎቹ በተለያየ መንገድ ተገልጾ ይገኛል፡፡በዚኽ ጥናት ውስጥ ዋና ጉዳይ ሥዕል በመኾኑ ሥዕል ላይ የተጻፉ ጽሑፎችን በመሰብሰብ ተንትኗል፡፡

ሥዕልና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ተነጣጥሎ አይታይም፡፡በመኹኑም ሥዕል በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ የኾነ አገልግሎት ይሰጥበታል፡፡በኢትዮጵያ ውስጥ እስከዛሬ በሥዕል ሥራዎቻቸው የሚታወቁት ሠዓሊያን ለሥዕል ሥራዎቻቸው መነሻ የኾናቸው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኙ ሥዕላት ናቸው፡፡ኾኖም ግን በኢትዮጵያ ሥዕል ሥራዎች ላይ ትኩረት ሲሰጣቸው አይታይም፡፡ይኹን እንጂ ሥዕል በተለያዩ ልቦለድ፣ተውኔት፣ግጥም እና በተለያዩ ጥናቶች ላይ በአብዛኛው አገልግሎት ላይ የሚውል ነው፡፡

የሥዕል አገልግሎት ከፍተኛ ከመኾኑ አንጻር ለሥዕል የተሰጠው ትኩረት ዝቅተኛ ነው፡፡ሰዎች ሐሳባቸውን የሚገልጹባቸው መንገዶች ውስጥ አንዱ ሥዕል ነው፡፡ሰዎች ጽሑፍ ከመጀመራቸው አስቀድሞ ሐሳባቸውን በሥዕል ይገልጹ እንደነበር ይነገራል፡፡ ይኹን እንጂ በአኹን ወቅት ደግሞ ከትምህርት ቤት ለሥዕል ትምህርት የሚሰጠው ትኩረት አንስተኛ በመኾኑ የሥዕል ፍላጎት ያላቸው ሰዎች ችሎታቸውን የሚያጎለብቱበትን መንገድ አያገኙም፡፡በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ውስጥ የሚገኙት ሥዕሎችም የቤተ ክርስቲያኗን ሥርዐት ጠብቀው

የሚሣሉ በመኾናቸው ከሠዓሊው የሚጠበቁ ሥርዐቶች ያስፈልጋሉ። በዚኽ ጥናትም ከሠዓሊው የሚጠበቁ ሥርዐቶች እና የሥዕሎቹን አሣሣል ለማሳየት በሚያስችል መልኩ ቀርቧል።

## ፩.፪ የጥናቱ አነሣሽ ምክንያት

ይኽን ጥናት ለማካኼድ አነሣሽ ከኾኑ ምክንያቶች መካከል በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚሣሉ ሥዕሎች በምን ዐይነት የአሣሣል ሥርዐት እንደሚሣሉ ለመመርመር ነው።ሥዕሎቹ በማን መሣል እንዳለባቸው እና ሥዕሉን ሠዓሊው ከመሣሉ በፊት መደረግ ያለባቸውን ዝግጅቶች እና ቅድመ ኹኔታዎችን ለማሳየት ነው።ከሚሣለው ሥዕል ጋራ የአሣሣል ዘዬ ምን መኾን እንዳለበት ማመልከት ሲኾን በአኹኑ ጊዜ ደግሞ ከሠዓሊው የማይጠበቁና ጎልተው የሚታዩ የአሣሣልና ሥዕል ከመሣላቸው በፊት የሚያደርጉት የቅድመ ዝግጅት እንደሌለ፣ማንኛውም ሰው እንደፈለገው እንደሚሥለው በመስማቴ እና የእምነቱን ሥርዐት የጠበቀ ሥዕል በወጉ የተመረመረ ባለመኾኑ ይኽንን ጥናት ለማካኼድ አነሣሽ ምክንያት ኾኖኛል።

አኹን ባለንበት ዘመን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሚሣሉ ሥዕሎች ለአንድ ሥዕል የተለያየ ቀለም የአጠቃቀምና የተለያየ የአሣሣል ዘዬ ያላቸው ሥዕሎች በማየቴና የትኛው አሣሣል ዘዬ የቀለም አጠቃቀም የእምነቱ ሥርዓት ተከትሎ የተሣለ እንደኾነ የማወቅ ፍላጎት ስላሳደረብኝ ነው። ከዚኽም በተጨማሪ ሥዕሉን የሚያዘጋጁት ባለሙያዎች ሥዕሉን ከማዘጋጀታቸው በፊት የእምነቱን ሥርዐት የሚፈቅደውን ሥነ ምግባር ተከትለው እንደማያዘጋጁ ይገለጻል።በዚኽ ጥናት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለሚሠሩ ሰዎች ከሠዓሊዎች የሚጠበቅ ሥነ ምግባርን ማሳወቅ እንደሚያስፈልግ በማሰብ ነው።በአጠቃላይ ለዚኽ ጥናት አነሣሽ የኾኑ ምክንያቶች በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሚዘጋጁት ሥዕሎች ጉራማይሌ መኾናቸው ሲኾን የእምነቱን ሥርዐት እና ሥነ ምግባር መሠረት ተከተሎ የተዘጋጁት ሥዕሎች የትኞቹ እንደኾኑ ለመለየት ነው።

## ፩.፫ የጥናቱ ዐላማ

የዚኽ ጥናት ዋና ዐላማ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሚሣሉ ሥዕሎችን የአሣሣል ሥርዐት መግለጽ፣ሥዕል በቤተ-ክርስቲያን ያለውን ዝምድና እና አገልግሎት እንግዳ ለኾኑ ሰዎች ለማሳየትና ለጥናትም እንዲነሣሡ ለማድረግ ሲኾን በዚኽ ዋና ዐላማ በተጨማሪ ዋና ዐላማውን የሚያጎለብቱ ዝርዝር ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው።

፩. የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሥዕል ታሪካዊ አመጣጥ መግለጽ፣

፪. የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሥዕል ዓላማ ሥርዐት ቅድመ ዝግጅት መግለጽ፣

፫. የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሥዕልን ጥቅምና የአሣሣል ሥርዐት ማሳየት

፬. የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የቅዱሳት ሥዕላት አቀማመጥ ሥርዓት ማብራራት፣

፭. አኹን ባለንበት ዘመን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሥዕልን የትምህርት አሰጣጥ መግለጽ የሚሉ ናቸው።

## ፩.፬ የምርምር ጥያቄዎች

በዚኽ ጥናት ውስጥ የሚመለሱ የምርምር ጥያቄዎች የሚከተሉት ናቸው።

፩. በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የቅዱሳት ሥዕላት አቀማመጥ ሥርዐታቸው እንዴት ነው?

፪. በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሥዕል ታሪካዊ አመጣጥ ምን ይመስላል?

፫. በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የሥዕል ዓላማ ምንድን ነው?

፬. ከሠዓሊው የሚጠበቁ ቅድመ ዝግጅቶች ምንድን ናቸው?

፭. በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሥዕሎቹ ጥቅም ምንድን ነው?

፮. የአሣሣል ሥርዐታቸውስ እንዴት ነው?

፯. አኹን ባለንበት ዘመን በኢትዮጵያ ኦርቶዶእስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሥዕል ትምህርት አሰጣጥ ኹኔታ ምን ይመስላል?

## ፩.፭ የጥናቱ ጠቀሜታ

ይኽ ጥናት መደረጉ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ-ክርስቲያን ውስጥ ለሚሠሩ ሠዓሊዎች የቤተ ክርስቲያኗን ሥርዓት ጠብቀው እንዲሠሩ ይጠቁማል።የሚሣሉት ሥዕሎች አገልግሎታቸውንና ታሪካዊ አመጣጣቸውን ለመረዳት፣ሠዓሊዎች ሥዕሎችን ከመሣላቸው በፊት ማድረግ ስለሚገባቸው ቅድመ ዝግጅት መረጃ ይኾናል።የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱሳት ሥዕላት አሣሣል የተወሰነ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ለሚፈልጉ ሰዎች ስለጉዳዩ መረጃ እንዲኖራቸው ያደርጋል።በተወሰነ ደረጃም ቢኾን የቅዱሳት ሥዕላት አሣሣል ምን እንደኾነ መረጃ ይሰጣል።ከዚኽ በተጨማሪም በዚኽ ርእሰ ጉዳይ ላይ የተጠኑ ጥናቶች ባለመኖራቸው ደግሞ ለሌሎች አጥኚዎች መነሻ ኾኖ ያገለግላል።

## ፩.፮ የጥናቱ ወሰን

የሥዕል አገልግሎት ዘርፈ ብዙ ነው።ሥዕል በተለያዩ ሙያዎች ውስጥ የተለያዩ ተግባራት ይከናወኑበታል።ከነዚኽም መካከል በሥነ ጽሑፍ በቲያትር በተለያዩ የእምነት ሥርዐቶች ውስጥ ሐሳብን ለመግለጽ ይጠቅማል።ሰሎሞን ተሾመ ስለፎክሎር ዐይነቶች ሲገልጽ ‹‹የፎክሎር ቁሳዊ ባህል ዐይነቶች ውስጥ አንዱ ሀገረሰባዊ ሥዕል ሲኾን ሀገረሰባዊ ሥዕሎች ከሚዘጋጁባቸው ዐበይት መንገዶች አንጻር ሃይማኖታዊ ሥዕሎች፣ታሪካዊ ሥዕሎች፣ተፈጥሯዊ ሥዕሎች ወዘተ በሚል መመደብ ይቻላል››በማለት ይገልጻል።ይኽ ጥናት ትኩረት የሚያደርገው ሃይማኖታዊ ሥዕሎች ከኾኑት ሥዕሎች ውስጥ የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱሳት ሥዕላት ላይ ብቻ ተወስኖ የሚቀርብ ጥናት ነው።ይኽን ጥናት ለማካኼድ ጥንታዊ ሥዕሎችን እና አኹን ባለንበት ዘመን ከሚሣሉት ሥዕሎች ጋራ በማነጻጸር ለማቅረብ ስለፈለኩኝ በቦታ አልወሰንኩትም፤ምክንያቱም የጥንታዊውን የአሣሣል ኹኔታ እና አኹን ባለንበት ዘመን የሚሣሉትን ሥዕሎች የአሣሣል ልዩነት ለማሳየት እንዲረዳ ነው።

## ፩.፯ የጥናቱ ዘዴ

ይኽ ጥናት ያተኮረው የአጠናን ዘዴ ገላጭና ተንታኝ ነው።የፎክሎር ጥናት አንድ የተወሰነ የፎክሎር ዘርፍ አመዳደብ መሠረት ተመርጦ የሚሠራ እና በገለጻ የሚቀርብ በመኾኑ ገላጭ ዘዴን መጠቀም አስፈላጊ ኾኖ ቀርቧል።‹‹የገላጭ የምርመር ዘዴ ኺደት ተፈጥሮሯዊ መልክ ያለው ነው።ምልከታ ማካኼድም ያዩትን መመዝገብ፣የዘገቡትን በተገቢው መንገድ መግለጽን ያመለክታል›› (ያለው፣2009) ። በቁጥር የማይገለጹ እንደ ልቦለድ፣ሥነ-ግጥም ያሉ ሥራዎች፣ በምልከታና በቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች የሚተነተኑበት ዘዴ ነው።

ሚደረገው ምልከታ የሥዕሎቹን አሣሣል እና የቀለሞችን አመራረጥ ትርጉም ለመግለጽ ያስችላል።ገላጭ የምርመር ዘዴ የተመረጠበት ምክንያትም በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅ የተገኙትን መረጃዎች ለመተንተን እንዲቻል ነው።ጥናቱን ለመተንተን የተመረጠው ንድፈ ሐሳብ ሥነ ልቡናዊና ጠቀሜታዊ ንድፈ ሐሳብ ሲኾን የተመረጠበት ምክንያትም ሥነ ልቡናዊ ንድፈ ሐሳብ በተለያዩ እምነት ውስጥ የሚገኙ ትእምርቶችን ለመግለጽ የሚጠቅም ንድፈ ሐሳብ ስለኾነ ነው።ሌላው የተመረጠው ንድፈ ሐሳብ ደግሞ ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ ሲኾን በተለያዩ የእምነት ቦታዎች የሚደረጉ ሥርዐቶች የሚከወኑት ከሚያስገኙት ጥቅም አኳያ የሚያጠና ስለኾነ ይኼ ንድፈ ሐሳብ ደግሞ ሥዕላትን ከጠቀሜታቸው አንጻር ለተመተንተን ስለሚረዳ ነው።

## ፩.፰ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ

ለዚኽ ጥናት አስፈላጊ የኾኑ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ተመርጠዋል፡፡እነርሱም ከካልዓይ የመረጃ ምንጮች መካከል በመጽሐፎች፣በመጽሔቶችና በሌሎች ጥናታዊ ጽሑፎች እንደአስፈላጊነታቸው ተመርጠው ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ቀዳማይ የመረጃ ምንጭ የኾኑት በቀዳሚነት በሥዕል ባለሙያዎች የቀረቡ ናቸው፡፡በመኾኑም ጥናቱ ወደ መስክ በመውጣት ተካኺዷል፡፡የመስክ ምርምር በሦስት መንገድ ሊካኼድ እንደሚችል ፈቃደ ይገልጻሉ፡፡እነዚኽ ሦስት መንገዶች ምልከታ ቃለ መጠይቅና መጠይቅ ናቸው፡፡ (1991፣90) ከነዚኽ መንገዶች መረጃ ለመሰብሰብም ኹለቱን የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ማለትም ምልከታና ቃለ መጠይቅ ተመርጠው ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡

የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶችን መጠቀም ምሉዕ የኾነ መረጃ እንድናገኝ ከማድረጉም በተጨማሪ የመረጃዎቹን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ይረዳል፡፡በመኾኑም ይኽን ጥናት የተሟላ ለማድረግ ምልከታና ቃለ መጠይቅ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን በተደጋጋፊነት በመጠቀም መረጃዎችን ለመሰብሰብ ተችሏል፡፡

ሌላው ደግሞ ከዚኽ ጥናት ርእስ ጋራ የሚያያዙ ንድፈ ሐሳቦችንና ፅንሰ ሐሳቦችን በማካተት ቀርቧል፡፡የፎክሎር ጥናት ዘርፍ ውስጥ መረጃ ለመሰብሰብ የሚጠቅመው ምልከታ ነው፡፡በምልከታ በተገኘው መረጃ መሠረት የሥዕሎቹን አሣሣል፣ሥዕሎቹን በመመልከትም አሣሣሉን ለማወቅ በቃለ መጠይቅ አማካይነት መረጃ ለመሰብሰብ ችያለኹ፡፡የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ውስጥ የእጅ ስልክ በመጠቀም፣ ፎቶግራፍ በማንሣት እና ማስታወሻ በመያዝ መረጃዎች አዘጋጅቻለኹ፡፡እነዚኽ መሣሪያዎች ያስፈለጉትም መረጃዎችን በተገቢው መንገድ ለመሰብሰብ እንዲቻል ነው፡፡

### ፩.፰.፩ ምልከታ

ምልከታ ለአጥኚው በሚካኼድበት ወቅት የተመለከተውን፣የሰማውን እና የተከናወነውን እንቅስቃሴ በመከታተል መረጃ ለመሰብሰብ የሚያስችል ጠቃሚ ዘዴ ነው፡፡ስለምልከታ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ ያለው እንዳወቅ የምርምር መሠረታዊ መርሖችና አተገባበር በሚለው መጽሐፍ ላይ የሚከተለውን ሐሳብ አቅርበዋል፡፡ምልከታ በሚደረግበት ሰዓት መረጃ ሰብሳቢው ሰው ከሚፈለግባቸው ተጠኚዎች ጋራ ወይም አካባቢ በመኾን የሚያደርጉትንና የሚናገሩትን ነገርበቅርበት ኾኖ እያየ እናእየሰማ በመመዝገብ መረጃ የሚሰበሰብበት መሣሪያ ነው (ያለው2009፣182-183) ፡፡

ምልከታ የተለያዩ ገጽታዎች እንቅስቃሴዎች በመመልከት መረጃዎችን ለመሰብሰብ ያስችላል፡፡

ምልከታ የምናጠናው ጉዳይ በትክክል እየተከናወነ መኾኑን በአኹኑ ሰዓት ያለውን ነባራዊ ኹኔታ በግልጽ ለመረዳት እንደሚያስችል Khotari ሲገልጽ the main advantage of thio s method is that subjective bias is eliminated, if observation is done accurated; secondly, the information obtained under this method relates to what is currently happening (1990.96).

ምልከታ በዚኽ ጥናትም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የሚሣሉ ሥዕሎችን በመመልከት የሥዕሎቹን ትርጉም ለመግለጽ የሚያሥችል በመኾኑ ለዚኽ ጥናት ምልከታ አስፈላጊ ነው።

ለዚኽ ጥናት በተደረገው ምልከታ መሠረት ለአንድ ሥዕል ዐይነት የተለያዩ የቀለም አጠቃቀም ስልትን የተከተሉ የአሣሣልን ሥርዐቶች በየመደብሩ እና በየአብያተ ክርስቲያናቱ የሚገኙትን ሥዕሎች ለማየት ችያለኹ። ጥናቱ ከምልከታ ኢ-ተሳትፏዊ ምልከታን በመጠቀም የሥዕል ዐውደ ርእዮችን እና ሥዕሎቹ ሲሣሉ በማየት በመቅረጸ ምስል፣ በመቅረጸ ድምፅ፣ በመቅረጽ ምስልና ድምፅ መረጃዎችን ተጠቅሜበታለኹ።

## ፩.፰.፪ ቃለ መጠይቅ

ይኽን ጥናት ዐላማ ከግብ ለማድረስ አጥኚዋ ጥቅም ላይ ያዋለችው ዋናው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ቃለ መጠይቅ ነው።ይኽ ዘዴ ለጥናት ለማካኼድ መረጃዎች ስለሚጠናው ጉዳይ ዕውቀት ካላቸው ሰዎች በመጠየቅ መረጃዎች የሚሰበሰቡበት ዘዴ ነው። የቃለ መጠይቅን ዘዴ የምንጠቀመው በኹለት ዐይነት መንገድ መኾኑን Khotari ሲገልጹ ‹‹ይኽን ዘዴ በኹለት ዐይነት መንገድ እንጠቀመዋለን፤አንደኛ ተጠያቂውን በአካል አግኝተን ፊት ለፊት በመኾን ጥያቄዎችን የምንጠይቅበት ነው።ኹለተኛው ደግሞ በአካል በማናገኝበት ኹኔታ ያሉንን ጥያቄዎች በስልክ የምንጠቀምበትና ምላሽ የምናገኝበት መንገድ ነው››(1990፣97-100)

የዚኽ ጥናት ትኩረት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሚገኙ ሥዕሎች በመኾኑ ሥዕሎቹ በሚዘጋጁበት ቦታው ድረስ በመኼድ ከባለሙያዎቹ ጋራ በአካል በመገናኘት ጥናቱን ሙሉ የሚያደርጉ መረጃዎችን በሚያስገኝ መልኩ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት እና በመጠየቅ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ተችሏል።አንድ አጥኚ ለጥናቱ የሚኾኑትን መረጃዎች ለማግኘት መጠይቆችን በሚያዘጋጅበት ጊዜ ኹለት ዐይነት መንገዶችን መከተል እንዳለበት ፈቃደ ያስረዳሉ።አንደኛው ክፍት ጥያቄ ሲኾን ይኽ የቃለ መጠይቅ ዐይነት ተጠያቂው አካል ሳይወሰን የራሱን አመለካከትና ስሜት እንዲኹም በማኅበረሰቡ ውስጥ ያሉ ጉዳዮችን ጨምሮ ከተለያዩ አንጻር የሚመልስበትና ተጠያቂው በነጻነት ስሜት የሚናገርበት ነው።ኹለተኛው ደግሞ ዝግ ጥያቄ ነው።ይኽ የቃለ መጠይቅ ዐይነት መረጃ ሰጪው አካል ዐጭር የኾነ ምላሽ እንዲሰጠን የምንጠይቅበት ስልት ነው(ፈቃደ 1991፣102)። በዚኽ ጥናት ኹለቱም ቃለ መጠይቅ ዐይነቶች አገልግሎት ላይ ውለዋል።ስለቃለ መጠይቅ ያለው እንዳወቅ በገጽ 176 ላይ እንደገለጹት‹‹ቃለ

መጠይቅ በቃል የሚቀርብ መጠይቅ ሲኾን ከጽሑፉ መጠይቅ የሚለየው በመላሹና ቃለ መጠይቁን በሚያካኺደው ሰው መካከል የፊት ለፊት የቃላት ምልልስ በመኖሩ ነው›› በማለት ያስረዳሉ፡፡ በምልከታ ወቅት አጥኚው ያልተረዳቸውን ነገሮች ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እንዲችል ቃለ መጠይቅ ይረዳል፡፡ በዚኽ ጥናት ውስጥም የተመረጠው ነጻ ቃለ መጠይቅ ሲኾን ይኽ የተመረጠበትም ምክንያት የመረጃ ሰጪዎች ለተጠየቁት ጉዳይ የፈለጉትን ያኽል እንዲናገሩ ዕድል ስለሚሰጥ ነው፡፡ይኽ ነጻ ቃለ መጠይቅ መረጃ አቀባዩ በጥያቄዎቹ ላይ ብቻ ሳይወሰን ተጨማሪ መረጃዎችን ለማግኘት ስለሚቻል ነው፡፡

ለዚኽ ጥናት ቃለመጠይቅ የሚደረግላቸው ሰዎች የሥዕል ባለሙያዎችና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን የአሣሣል ሥርዐት ላይ ዕውቀት ያላቸውን ሰዎች ናቸው፡፡

## ፩.፰.፪ የቡድን ተኮር ውይይት

ቡድን ተኮር ውይይት የሚካኼደው በቂ መረጃ ሊኖራቸው ይችላል ተብሎ የሚታሰቡ ሰዎችን በመውሰድ በሚነሣው ጥያቄ ዙሪያ በቡድን በመኾን እየተወያዩ መረጃ እንዲሰጡ ለማድረግ ኾን ተሳታፊዎቹ እስከ 12 ሊደርሱ ይችላሉ በማለት (2009፣191) በማለት ይገልጻሉ፡፡በዚኽ ጥናት ውስጥ መረጃዎችን ለመሰብሰብ በቃለ መጠይቅ ውይይት ተካኺዷል፡፡

በአጠቃላይ ጥናቱን ለማካኼድ መረጃዎቹን ከቀዳማይ እና ከካልዓይ የመረጃ ምንጮች የተሰበሰቡ ሲኾን በዚኽ መሠረት ቀዳማይ የመረጃ ምንጭ የኾኑትን በሥዕል ዙሪያ ጥናት የሚያደርጉ የማኅበረ ቅዱሳን የሥዕል ባለሙያ የኾኑትን ሥዕልን በተመለከተ በቃለ መጠይቅና ዐውደ ርእዮች ላይ ምልከታ በማድረግ መረጃዎቹ ተሰብስበዋል፡፡ከካልዓይ የመረጃ ምንጮች ደግሞ በዚኽ ርእስ ዙሪያ የተሠሩ የመጀመሪያና የኹለተኛ ዲግሪ ጥናታዊ ጽሑፎችን እና በቤተ መጻሕፍት ውስጥ የሚገኙ ፅንሰ ሐሳባዊ መረጃዎች እና ንድፈ ሐሳባዊ መረጃዎችን ለጥናቱ በግብአትነትትጥቅም ላይ ውሏል፡፡መረጃዎችም እንደአመቺነታቸው በምሥል፣በድምፅ፣በፎቶግራፍ እና በማስታወሻዎች ተደራጅተዋል፡፡

## ፩.፰.፫ በመስክ ላይ ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሔዎች

ይኽ ጥናት ወደ መስክ ወጥቶ በቃለ መጠይቅ በምልከታ መረጃ የሚሰበሰብበት እንደመኾኑ ወደሥራ በሚገባበት ወቅት ኹሉም ነገሮች የተመቻቹ አልነበሩም፡፡ጥናቱን ለማካኼድ አኹን ባለንበት ዘመን የሥዕል ሥራው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እየጠፋ በመምጣቱና እያወቁም መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ ያልኾኑ ስለነበሩ መረጃ የሚሰጡ ባሙያዎችን ማግኘት አስቸጋሪ ነበር፡፡ይኸውም ሥዕል ባለሙያዎች ለቃለ መጠይቁ ለማድረግ በመጀመሪያ ፈቃደኝነታቸውን የገለጹ ቢኾንም ቀጠሮን በተለያየ ምክንያት በማቅረብ ሸሽተዋል፡፡በተደጋጋሚ ስልክ ብደውልም ምላሽ ሊሰጡኝ አልፈለጉም፡፡ለእነዚኽ ችግሮች እንደመፍትሔ የወሰድኩት ሌሎች መረጃ ሊሰጡ የሚችሉ ሌሎች መፈለግ

ነበር፡፡በመጨረሻም ባለሙያዎችን ጉዳዮን በማስረዳት በቀረቡት ጥያቄዎች መሠረት ለመወያየት ችያለኹ፡፡

## ፩.፰.፬ የጥናቱ አደረጃጀት

ጥናቱ በዐምስት ምዕራፎች ተዋቅሮ የቀረበ ሲኾን በምዕራፍ አንድ በመግቢያ ሥር በሚገኙ ንኡሳን ክፍሎች ተደራጅተዋል፡፡እነርሱም፡-የጥናቱ ዳራ፣የጥናቱ አነሣሽ ምክንያት፣የጥናቱ ዐላማዎች፣የምርምር ጥያቄዎች፣የጥናቱ አስፈላጊነት፣የጥናቱ ወሰን፣የጥናቱ ዘዴ፣የመረጃ ምንጮችና መሰብሰቢያ ዘዴ፣እንዲኹም ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችና የሚወሰዱ መፍትሔዎች ናቸው፡፡ምዕራፍ ኹለት ንድፈ ሐሳባዊ ዳራና የተዛማጅ ጥናቶችን ቅኝት የሚመለከት ነው፡፡በምዕራፍ ሦስት ደግሞ የቤተ ክርስቲያንን ትውፊት እና ትርጒም ተብራርቶ የቀረበበት ክፍል ነው፡፡ምዕራፍ አራት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሚገኙ ቅዱሳት ሥዕላትን አሣሣል የተተነተነበት ሲኾን ምዕራፍ ዐምስት የጥናቱ ግኝቶች የተጠቀሙበት ነው፡፡

# ምዕራፍ ኹለት

## ፪. የድርሳናት ክለሳ

በዚኽ ምዕራፍ ሦስት ክፍሎች ቀርበዋል።የመጀመሪያው ክፍል ከጥናቱ ጋራ ተያያዥነት ያላቸውን የምርምር ሥራዎች የተቃኙበት የተዛማጅ ጽሑፍ ቅኝት ሲኾን ሥዕልን ርእሰ ጉዳይ አድርገው የተካኼዱ ዐምስት የመጀመሪያ ድግሪ፣አንድ የኹለተኛ ድግሪ በድምሩ ሰባት ያኽል ጥናታዊ ሥራዎች ከዚኽ ጥናት ጋራ ያላቸው ተመሳሳይነት፣ልዩነትና ዐላማ የቀረበበት ነው።ከዚኽ በተጨማሪም ሰባት የታተሙ መጽሐፎች የቀረቡበት ነው።በኹለተኛው ክፍል ደግሞ የሥዕል ምንነት፣ሥዕልና ፎክሎር፣የሥዕል አጀማመር በኢትዮጵያ፣የሥዕል አጀማመር በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እና የሥዕል ጥቅም በተለያዩ የዘርፉ ምሁራን ያነሧቸውን ሐሳቦች ተብራርተው ቀርበዋል።ሦስተኛው ክፍል ደግሞ ጥናቱ ከግብ ይመታ ዘንድ በጥናት መስኩ የተመረጡት ተዛማጅ የኾኑ ንድፈ ሐሳቦች ተብራርተው ቀርበዋል።እንዲኹም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሚገኙ ሥዕሎችን ለመተንተን የሚያስችሉ ንድፈ ሐሳቦች ተካተዋል።በዚኽ ጥናት ውስጥ እንዴት አገልግሎት ላይ እንደሚውሉ ተገልጿል።

### ፪.፩ የንድፈ ሐሳብ ቅኝት

### ፪.፩.፩ ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ

ለዚኽ ጥናት የተመረጠው ንድፈ ሐሳብ ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ ነው።በተለያዩ እምነት ውስጥ የሚገኙ የእምነቱ ተከታዮች ከሚያስገኝላቸው ጥቅም መካከል ርካታ፣ፈውስ፣ደስታ በመኾኑ ይኽን ለመተንተን ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሚዘጋጁ ሥዕሎችን ፋይዳ ለማሳየት ይጠቅማል።ፎክሎር በተሰኘው የተሾመ መጽሐፍ ላይ ‹‹እምነት ማኅበራዊ ኢኮኖሚያዊ ባህላዊ፣ሥነ ልቡናዊ ጥቅሞችን ያስገኛል›› በማለት ይገልጻል።ከዚኽ በተጨማሪም ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ አራማጆች በአንድ ማኅበረሰብ ውስጥ ያሉትን ምሳሌያዊ አነጋገሮች፣ ተረቶች፣ሚቶች፣እምነቶችና ሌሎቹም ማንኛውም ሎሮች ማኅበራዊ፣ኢኮኖሚያዊ፣ፖለቲካዊ ባህላዊ፣ሥነ ልቡናዊ ወይም ሌላ ጥቅም መስጠት ነው።የሚለውን ሐሳብ የሚያራምዱ እንደኾነ አስረድቷል።

የሥዕል ጠቀሜታ ዘርፈ ብዙ ነው።በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሚዘጋጁ ሥዕሎች ከሚያስገኙ ጥቅሞች ውስጥ የአእምሮ ርካታ ሰላምንና መረጋጋትን ፣እንዲሁም ከሕመም መፈወስን ያስገኛል።ከዚኽ በተጨማሪም ሥዕሎቹ ለእምነቱ ተከታዮች

የሚያስገኘው መንፈሳዊ ጠቀሜታ ያለው በመኾኑ ምክንያት አጥኚው ይኽንን ጥናት ከተገግባራዊ ንድፈ ሐሳብ አንጻር ለመተንተኑ ተገቢ ኾኖ ቀርቧል፡፡

### ፪.፩.፪ ሥነ ልቡናዊ ንድፈ ሐሳብ

በሥነ ልቡናዊ ንድፈ ሐሳብ ተረቶች፣ ሚቶች፣ ፌስቲቫሎች፣ ጨዋታዎች፣ ውዝዋዜዎች፣ ሙዚቃዎች፣ እንቆቅልሾች እምነቶች፣ባህላዊ ትእምርቶች የማኅበረሰቡን ሥነ ልቡና ለማጥናት የሚያገለግሉ ሲኾን እነዚኽ የፎክሎር ዘርፎችም ለፎክሎር ጥናት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አላቸው፡፡ ሥዕሎች የተለያዩ እምነቶች ውስጥ የተለያዩ ትእምርቶች ይዘው ይገኛሉ፡፡በዚኽ ጥናት ላይ ከሚነሡት ርእሰ ጉዳዮች ውስጥ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሚሣሉ ሥዕሎችን ያላቸውን ትእምርት ለማሳየት ይረዳል፡፡የሥዕሎቹ አሣሣል፣ጥቅም ላይ የሚውሉ ቀለማት ከታሪኩ ጋራ ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው በመኾኑና የሚያስተላልፉትን ትእምርት ለመግለጽ እንዲቻል ይኽን ጥናት ለመተንተን ያመች ዘንድ ሥነ ልቦናዊ ንድፈ ሐሳብ ተመርጧል፡፡

### ፅንሰ ሐሳብ

### ፪.፩.፫ የሥዕል ምንነት

ደስታ ተክለወልድ መዝገበ ቃል እንደገለጹት ሥዕል በብራና በወረቀት በደንጊያና በዕንጨት በብረት በሰው ገላ ላይ የተሣለ የተቀረጸ የተቀነሰ የሰውና የማንኛውም ፍጥረት መልክ ምሳሌ ምልክት ነው ይላሉ፡፡

አለቃ ኪዳነወልድ ክፍሌ ደግሞ ‹‹ሥዕል›› በቁም መልክ የመልክ ጥላ፣ንድፍ፣አምሳል፣ንድፍ በጥልፍ፣በስፌት ወይም በቀለም በወረቀት ገዝፎ ተጽፎ ከደብር፣ለእብን፣ከዕንጨት ፣ከእፅ፣ ከማዕድን ታንጦ፣ተቀርጦ፣ተሸልሞ፣አጊጦ፣ የሚታይ የሚዳስስ ነው››ይላሉ፡፡ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል ባዘጋጀው መዝገበ ቃላት ደግሞ ሣለ ማለት የአንድን መልክ ቅርጽ ወይም አንድን ዐይነት ሐሳብ በሥዕል አሳየ፣ምስሉን በወረቀት፣አሻራ፣በግድግዳ ወዘተ ላይ ቀረፀ አሰፈረ ነደፈ›› በማለት ተገልጿል፡፡ሥዕል ማለት ደግሞ ለዐይን እንዲታይ ተደርጎ በወረቀት በአሻራ፣ በግድግዳ ወዘተ ላይ በርሳስ በብሩሽ፣በብዕር የተሠራ፣የተነደፈ ወይም ከጠጠር ነገር የተቀረጸ የአንድን ነገር ወይም ሐሳብ መልክ ቅርጽ ምስል በማለት ማብራሪያ ተሰጥቷል፡፡

ሐውልተ ስምዕ በተሰኘው የኃይለማርያም ላቀው መጽሐፍ ላይ እንደተገለጸው ደግሞ ሥዕልና ምስል እንደሚለያዩ ያስረዳሉ፡፡

አንዳንድ ጸሐፊዎች በምስልና ለሥዕል አንድ ዐይነት ትርጒም በመስጠት ጽፈዋል፡፡ነገር ግን በምስል እና መካከል መሠረታዊ ልዩነት አለ፡፡ በተለይም ቅዱሳት ሥዕላት አብያተ ክርስቲያናት በሌሎች ለመሣል አመቺ በኾኑ ነገሮች በቀለም የሚሣሉ፣በዐይን የሚታዩ፣ በእጅ የሚዳሰሱ ናቸው፡፡ቅርጽ ወይም ምስል ግን ከሥዕል በተለየ ኹኔታ በድንጋይ፣ በዕንጨት በብረታ ብረት በመሳሰሉ ነገሮች ቅርጽ ወጥቶለት የሚሠራ ነው፡፡እነዚኽን መሠረታዊ ልዩነት ያላቸውን ነገሮች አንድ ዐይነት ትርጉም ሰጥቶ መጻፍ ለከፋ ስሕተት ያጋልጣል፡፡

ሥዕል በቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አገልግሎት የሚከናወንበት ታላቅ ምስጢር የያዘ ነገር ነው፡፡ሥዕል የቅዱስ ቃሉ ማገናዘቢያ (መግለጫ) መሣሪያ ነው፡፡ለምሳሌ ቃል በመጮኽ አእምሮ ያሰበውን መልእክት በማስተላለፍ ትርጉም ያለው ግንዛቤ ይፈጥራል፤ሥዕል ግን በአርምሞ ያስተምራል (ከፍያለው፣1986፣56)

## ፪.፭.፬ ሥዕል እና ፎክሎር

በፎክሎር የሚለው ፅንሰ ሐሳብ ዘርፈ ብዙ የኾነ ባህሎችን የሚይዝ ነው፡፡በተለያዩ ማኅበረሰብ ውስጥ ሰዎች ሐሳባቸውን ከሚገልጹባቸው መንገዶች ውስጥ አንዱ ሥዕል ነው፡፡ሥዕላት በተለያዩ ሰው ሠራሽና ተፈጥሯዊ ነገሮች ላይ የሚሣሉ ሲኾን ለአብነትም ሥዕል በዕንጨት፣ በድንጋይ፣ በጨርቅ እና በቆዳ በመጠቀም ሊተገበር ይችላል፡፡ በእነዚኽም ሥዕሎች የየዘመናቱን ገጠመኝ፣ታሪክ፣ሃይማኖት፣ፍልስፍና እና አመለካከት ይንጸባረቅበታል፡፡

ፎክሎር ሰዎችን እና የፈጠራ ችሎታቸውን፤ማንነታቸውን እምነትና ዕሴቶቻቸውን የምንተረጒምበት የዕውቀት ዘርፍ ነው፡፡ቀድሞ ፎክሎር ጥናት ያተኩር የነበረው እየጠፉ ባሉና በጠፉ ቅርሶች ላይ ነበር፡፡የጥናት ዘርፉንም በመጥፋት ላይ ያሉና የጠፉ ቅርሶችን ሰብስቦ መሰነድ ነበር፡፡በመኾኑም ለፎክሎር ጥናት መሠረት የኾነው ጉዳይ በመጥፋት ላይ ያሉ ቅርሶች ናቸው (ፌኔጋን1992፣35)፡፡

በፎክሎር ጥናት ከተነሡ ሐሳቦች አብዛኞቹ በፈርጅ ከፋፍሎ ማጥናት ተገቢ እንደኾነ ያምናሉ፡፡የተወሰኑት በሦስት ለመክፈል የሞከሩ ቢኾንም የሀገራችንን ምሁራንን ጨምሮ በአብዛኛው የሚስማሙት አራቱን ክፍሎች ነው፡፡ከነዚኽም ውስጥ (Sims and Stephen, 2005 12-13) ቃላዊ፣ቁሳዊ እና ልማዳዊ በማለት የከፈሉት ሲኾን፤ሌሎች ደግሞ ሥነ ቃል ሀገረሰባዊ ልማድ፣ቁሳዊ ባህል እና ሀረሰባዊ ትውን ጥበባት በማለት የጥናት አመቺ እንዲኾን ከፍለውታል (Dorson, 1972; 3), (ፈቃደ፣1991፣10) (Sims and Stephen, 2005; 2-3)

ለጥናት አመቺ እንዲኾኑ በዘውግ ይከፋፈሉ እንጂ በመካከላቸው ድንበር መሥራት ተገቢ አለመኾኑን ይገልጻሉ፡፡

አንዱ ባንዱ ውስጥ ሊኖር ስለሚችል መርጦ ማጥናቱ የተሻለ እንደሚኾን ይስማማሉ፡፡ (Simsand Stephen, 2005; 17) ፡፡የማኅበረሰብ ታሪክ፣አስተሳሰብ፣ከአምላኩ ጋራ ያለውን ግንኙነት፣ሥነ ልቡናዊ ማንነቱን ለመረዳት በሃይማኖቱ ውስጥ በቅብብል የሚያከናውኗቸውን ትውፊቶች መመርመር የተሸለ ይኾናል፡፡

ሰሎሞን ተሾመ ባዬ (2007፣ 248) ባህል ውስጥ የሚካተቱት በዐይን የሚታዩ፣በእጅ የሚዳሰሱና በምላስ የሚቀመሱ ተጨባጭ የፎክሎር ዐይነቶች እንደኾኑ ያስረዳሉ፡፡እነርሱም በቁሳዊ ባህል ውስጥ የሚካተቱት የፎክሎር ዘርፎች ሀገረሰባዊ የእጅ ሥራ፣ሀገረሰባዊ ሥንክን፣ሀገረሰባዊ ምሕንድስና፣ሀገረሰባዊ አልባሳትና ሀገረሰባዊ ምግብና መጠጥ በሚል ዶርሰን (1972) በዐምስት ከፍሏቸዋል፡፡በእነዚኽ የፎክሎር ዐይነቶች ማኅበረሰቡ በአካባቢው የሚያገኛቸውን ግብአቶች፣በራሱ ዕውቀት የፈጠራቸውን የማምረቻ መሣሪያዎች የራሱን ዕውቀት መሠረት በማድረግ የሚሠራባቸው ቁሶች ናቸው፡፡ሥዕልም ሲዘጋጅ ከአካባቢያቸው በሚያገኙት ቁሳቅሶችና በራሳቸው ዕውቀት መሠረት የሚያዘጋጁት ነው፡፡ሥዕልም የሐሳብ መግለጫ፣ ለማስተማሪያነት የሚያገልግል በመኾኑ በፎክሎር ዘውጎች ቁሳዊ ባህልን የሚገልጽ ስለኾነ ሥዕልና ፎክሎርን የማይነጣጠሉ የማኅበረሰቡ ውጤቶች ናቸው፡፡

## ፪.፩.፫ የሥዕል አጀማመር በኢትዮጵያ

በኢትዮጵያ ስለሥዕል አጀማመር የተለያዩ አጥኚዎች የተለያዩ ጥናቶችን ያካኼዱ ሲኾን ከእነዚኽም መካከል የታየ አሰፋ ጥናት አንዱ ነው፡፡ታዬ አሰፋ የኢትዮጵያ ጥናት ተቋም ‹‹ስለኢትዮጵያ ሥነ ጥበብ እድገት ሴሚናር ኢግዚቢሽን ግምገማ›› በሚል ርእስ ባቀረቡት ጥናት ላይ ስለኢትዮጵያ ሥዕል አጀማመር ሲያስረዱ

> የድንጋይ ዘመን ሥራዎች 1955 እ.ኤ.አ ሙሴ ጅሪ ባዩ ባደረጉት ጥናት በሐረር ክ/ሀገር በርከት ያሉ ከዋሻ ውስጥ እንደተገኙ ሙሴ ኤፍሬም በሲዳሞ ክፍለሀገር በዲላ አካባቢ ያገኟቸው እንደዚኹም በኤርትራ ክ/ሀገር ደአር የተባለው አካባቢ በቋጥኝ ላይ የተፈለፈሉ የጥበብ ሥራዎች መገኘታቸውን የቅድመ የሥነ ጥበብ ማስረጃቸውን በማቅረብ ማጠቃለያ ሰጥተዋል፡፡ በ፬ ተኛ ክ/ዘመን ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ መግባቱ በካሌብ ዘመን በ፮ተኛ ክፍለዘመን በሦርያ ዘጠኙ ቅዱሳን (ዘሚካኤል፣ ይሥሐቅ፣ አፍጼ፣ይማዐታ፣ጽሕማ፣ጰንጠሌዎን፣ጉባ፣አሌፍ፣ሊቃኖስ)መጻሕፍት ይዘው

መምጣታቸውን ከታሪክ ጠቅሰው የሥዕል ጥበብ በሀገሪቷ ከሃይማኖት ጋራ መተሳሰሩን አስረድተዋል፡፡የክርስትና መጻሕፍት ሲተረጐሙ ሥዕልም ዐብሮ እንደማስሪያ፣ብዕር ከሸንበቆ ብሩሽ ከዝንጀሮ ጸጕር፣ ቀለም ከድንጋይ አፈር ቅጠላ ቅጠል ውሐና የእንቁላል አስኳል እንደሚዘጋጅ ያወሣሉ፤ይኸም የኢትዮጵያ ሥነ ጥበብ ከሌሎች ለየት ያለ መኾኑን ይናገራሉ፡፡ተጽዕኖውም ከባዛይንታይንና ከኮፐቲክ ይልቃል ማለት እንደማይቻልና ከነቢዩ መሐመድ በኋላ አሠራሩ መለየቱ ይኸው የርእዮተ ዓለም ልዩነት ለሥነ ጥበብ እድገት እንዲኖረው አድርጓል ይላሉ፡፡የየዘመናቱን የሥዕል ታሪክ ሲገልጹም በ16ተኛ ክፍለ ዘመን ኮፒ ከማድረግ ሌላ ከመጽሐፍ ትረካ አንጻር ሥዕል መሥራት እንደተቻለ እና ጦርነት ለማራመድ ዋጋ ላይ እንደዋለ፣በ17ተኛው እና በ18ተኛው ክፍለ ዘመን ከሃይማኖት ቀለበት ወጥቶ የዕለት ኑሮን ለማንጸባረቅ እንደተሞከረ፣በ18ተውኛ እና በ19ኛው ክፍለ ዘመን ከቤተ ክርስቲያን ሌላ የመሳፍንቱን በመጨመር የገዢውን መደብ በማንጸባረቅ ከዕለት ወደዕለት እየጨመረ መኼዱን እና በ19ኛው እና በ20ኛውክፍለ ዘመን ከቤተ ክህነት ሰዎች በስተቀር አንዳንድ ኢትዮጵያውያን በሥነ ጥበብ ሙያ መሳተፍ መጀመራቸውን ከአብዮት ፍንዳታ በኋላ ሥነ ጥበብ በማንቃት፣በማደራጀት ከፍተኛ እንቅስቃሴ ላይ መገኘቱን ይገልጻሉ፡፡

ታደሰ መስፍን ‹‹ገና ፊደል ከመፈጠሩ በፊት የሰው ልጅ በዋሻ ውስጥ የመጀመሪያ መግባቢያ ቋንቋው የመንደፍ የመሣል የመቅረጽ ችሎታውን በመጠቀም የሕይወት ግንዛቤውን አንዳዳበረ›› ያስረዳሉ፡፡

## ፪.፩.፮ የሥዕል አጀማመር በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን

ሥዕል በቤተ ክርስቲያን የቆየ ታሪክ ያለው መንፈሳዊ የጥበብ ዘርፍ ነው፡፡ሥዕል እግዚአብሔር ጋራ የተያያዘና በብሉይም ኾነ በዐዲስ ኪዳን የሚሠራበት ነው፤በእግዚአብሔር የተሰጠ ሕግ ነው፡፡ይኸውም ለሙሴ በታቦተ ሕጉ በጽላት ኪዳኑ ላይ ሥዕለ ኪሩብን እንዲሥል ታዞ ነበር፡፡በብሉይ ኪዳን የመጀመሪያው ሠዓሊ ሙሴ ነው፡፡ ሥዕል አምላካዊ ትእዛዝ ያለበት ነው(ኦሪትዘፀአት 35-30)፡፡ባስኤልን በሥራ ኹሉ ብልኀት በጥበብም፣ በማስተዋልም ፣በዕውቀትም የእግዚአብሔርን መንፈስ ሞላበት፤የጥበብን ሥራ ያስተውል ዘንድ በወርቅና በናስ በብር ይሠራ ዘንድ በርሱ ጥበብን ሞላ (1ኛ ነገሥት 1-23) ከስርየት መክደኛውም ጋራ አንዱን ኪሩብ በአንድ ወገን፣ኹለተኛውንም ኪሩብ በሌላው ወገን አድርገኽ በአንድ ላይ ትሠራዋለኽ፡፡ኪሩቤልም

ክንፎቻቸውን ወደላይ ይዘረጋሉ፣የስርየት መክደኛውንም በክንፎቻቸው ይሸፍናሉ፤ፊታቸውም ርስ በርሱ ይተያያል፡፡የኪሩቤልም ፊቶቻቸው ወደ ስርየት መክደኛው ይመለከታሉ(ዘፀ19፣20)በቅድስተ ቅዱሳኑም ውስጥ ቁመታቸው ዐሥር ክንድ የኾነ ከወይራ ዕንጨት ኹለት ኪሩቤል ሠራ፡፡የኹለቱም ክንፎች በቤቱ መካከል ርስ በርሳቸው ይነካኩ ነበር፡፡ኪሩቤልንም በወርቅ ለበጣቸው ይላል(ትንቢተ ሕዝቅኤል 10-1)፡፡ሰሎሞንም የመጀመሪያውን ቤተ መቅደስ በሠራ ጊዜ ሥዕለ ኪሩብን ሥኣል፡፡ ኹለት ኪሩቤልንም ከተቀጠቀጠ ወርቅ ሠራ፤መክደኛውም ላይ በኹለት ወገን አደረጋቸው፡፡ ከስርየት መክደኛውም ጋራ አንዱን ወገን፣ኹለተኛውንም ኪሩብ በሌላው ወደን አድርጎ በአንድ ላይ ሠራቸው፡፡ኪሩቤልም ክንፎቻቸው ወደ ላይ የዘረጉ ኾኑ፣የስርየት መክደኛውንም በክንፎቻቸው ሸፈኑ፣ ርስ በርሳቸውም ተያዩ፤የኪሩቤልም ፊቶቻቸው ወደ መክደኛው ተመለከቱ (ዘፀ 37፣70)፡፡አሠራሩም (1ኛ ነገሥት 6፡23) በቅድስተ ቅዱሳኑም ውስጥ ቁመታቸው ዐሥር ክንድ የኾነ ከወይራ ዕንጨት ኹለት ኪሩቤል ሠራ፡፡የኪሩብም አንደኛው ክንፍ አዐምስት ክንድ፣የኪሩብም ኹለተኛው ክንፍ ዐምስት ክንድ ነበረ ከአንደኛው ክንፍ ጫፍ ጀምሮ እስከ ኹለተኛው ክንፍ ጫፍ ድረስ ዐሥር ክንድ ነበረ፤ኹለተኛውም ኪሩብ አሥር ክንድ ነበረ ኹለቱም ኪሩቤል አንድ ልክና አንድ መልክ ነበረ፡፡ የአንዱ ኪሩብ ቁመት ዐሥር ክንድ ነበረ ፤ኹለተኛውም ኪሩብ እንዲኹ ነበረ ፤የኪሩቤልንም በውስጠኛው ቤት አኖራቸው፡፡ የኪሩቤልም ክንፎቻቸው ተዘርግተው ነበር የአንዱም ኪሩብ ክንፍ አንደኛውን ግንብ ይነካ ነበር፤የኹለተኛውም ኪሩብ ክንፍ ኹለተኛውን ግንብ ይነካ ነበር፤ የኹለቱም ክንፎች በቤቱ መካከል እርስ በርሳቸው ይነካኩ ነበር፡፡ ኪሩቤልም በወርቅ ለበጣቸው፡፡ የክርስትና ሃይማኖት ከተስፋፋባቸው መንገዶች አንዱ ቅዱሳት ሥዕላትን ፣ሕማማተ መስቀልን ፣ግፍዐ ሰማዕታትን(ሰማዕታት የተቀበሉትን ግፍ) ፣በመሣል ለማስተማሪያነት በማዋል ነው(ሐውልተ ስምዕ፣2004፣146) ሥዕል አጀማመር በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በተለያዩ መጽሓፍት ላይ ተጽፎ ይገኛል፡፡አባ ጎርጎርዮስ የኢትዮጵያ ቤተ-ክርስቲያን ታሪክ በሚለው መጽሐፋቸው ላይም እንደሚከተለው ይገልጻሉ፡፡

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ-ክርቲያን የሥዕል አጀማመር እንደገለጹት በቤተ ክርስቲያን ታሪክ የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ትምህርታቸውን ያስፋፉት ዋሻ ፈልፍለው፣ጉድጓድ ቆፍረው በዋሻ በፍርክታ ውስጥ ነው፡፡ ካታኮምብ (ግበበ ምድር) ይሉታል፡፡በዚኽ ዋሻ ውስጥ የሰማዕታትን ዐፅም እየሰበሰቡ ጸሎት ይጸልዩበት ነበር፡፡በዚኹ ውስጥ አማኞች እየመጡ የማኅበራቸው አባል መኾን ጀመሩ፡፡በዚኽ የክርስትናን ትምህርት አስፋፍቶ ለመስጠት በቂ መጻሕፍት አልነበሩም፡፡እንደልብ ወጥቶ ለመፈለግና ለማዘጋጀት

ነጻነት ስላልነበራቸው ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንዳንድ ምሳሌዎች በሥዕል እያሰፈሩ ማስተማሪያ ኹኖ ቆይቷል። (ጎርጎርዮስ 1974፣113) (ዐምደ ሃይማኖት፣2010፣141)

እንግዳ መርጊያ ቅዱሳት ሥዕላት በሚለው መጽሐፍ እና ዐምደ ሃይማኖት በተሰኘው መጽሐፍ ውስጥ የሥዕል በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክስቲያን አጀማመር የመጀመሪያው ሠዓሊ ራሱ ክርስቶስ እንደኾነ ይገልጻል፡፡ለዚኽም መግለጫ የቀረበው በመጽሐፍ ቅዱስ ‹‹እግዚአብሔርም አለ፡፡ ሰውን በመልካችን እንፍጠር››የሚለው ሐሳብ ሥዕል ክርስቶስ የሰውን ልጅ አፈጣጠር ጋራ በሚዛመድ እንደኾነ ይገልጻል፡፡በዚኹ መጽሐፍ ላይ እንደተገለጸው ‹‹የሰው ልጅ ያልተጠበበትን ሥዕል የቬሮኒካ ላይነን››በማለት እንደሚጠራ የዚኽም ታሪክ ሲተረክ ‹‹ቬሮኒካ››የምትባል ወላድ ሴት ጌታችን መዳኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ቀራንዮ አደባባይ መስቀሉን ተሸክሞ በስድስተኛው የዕረፍት ቦታ ሲያርፍ ሻሽዋን አውልቃ የፊቱን ላብ ይጠርግ ዘንድ ሰጠችው፡፡ ጌታችንም ፊቱን አብሶ /ዐድፎ ሲመልስላት ያንጊዜም የፊቱ መልክ፣ገጹ በላይነኑ ላይ ማንም ሳይሥለው በራሱ በጌታችን ጥበብ ተሥሎ፣ታትሞ ተገኝ››በማለት ሥዕል እንደተጀመረ ምዕራባውያን እንደሚገልጹ ያስረዳል፡፡

ስለክርስቶስ ሥዕል አመጣጥ የሚነገሩ ታሪኮች (ትውፊቶች) አሉ፡፡አቡነ ጎርጎርዮስ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በሚለው መጽሐፍ እንደተገለጸው የጌታን ሥዕል እንዴት እንደተሣለ እንደሚከተለው ይገልጻሉ፡፡

ለመጀመሪያ ጊዜ የጌታን ሥዕል የሣለው ዮሐንስ ወንጌላዊው ነው ይባላል፡፡ታሪኩም ከሞላ ጎደል እንደዚኽ ነው፡፡ከ፲፬-፴፯ዓ.ም.ሮምን ይገዛ የነበረው ጢባርዮስ ቄሳር ነው፡፡በሱ ዘመነ መንግሥት ነው ጌታ የተሰቀለው፤ይኸው ጢባርዮስ ቄሳር የሚወደው አንድ ልጅ ነበረው፡፡ርሱው ሞተበት ጢባርዮስ በልጁ መሞት ዐዝኖ ሬሳውን ሳያስቀብር ሰነበተ፤ከጥቂት ቀንም በኋላ ጌታ በኢየሩሳሌም ያደርገው የነበረውን ታምራት ያውቅ ነበር፤‹‹ከጢባርዮስ ቄሳር ምድራዊ ንጉሥ የተላከች ጦማር (መልእክት) ለጌታ ለኢየሱስ ክርስቶስ ንጉሠ ሰማይ ወምድር ትድረስ››ብሎ ልጁን እንዲያስነሣለት የምልጃ ልመና ጽሑፍ ጽፎ ይኽችን መልእክትና የልጁን ሬሳ ወስደው ጎልጎታ (የጌታ መቃብር) ላይ እንዲያኖሩለት ለባለወጎቹ ላከ፡፡እነርሱም የዚኽንስ ሰው እናቱን አምጡልኝ፤እኔ ቋሚ ለንሚ፤ለሚስቴ ገረድ ደንገጠር ኹነን እናገለግላታለን ብሎ እንደገና ሰው ቢልክ፤የድንግል ማርያም ክብር ሰማያዊ እንጂ ምድራዊ ስላልኾነ ተሰውራባቸው አላገኟትም፡፡ጢባርዮስ ግን ተስፋ ሳይቆርጥ ዮሐንስ ወንጌላዊ በዕለተ ዓርብ በመስቀሉ ላይ እንዳየው አድርጎ ከለሜዳ አስታጥቆ ጌታን ሥሎለታል፡፡ስለሥዕሉ እውነተኛነትም ለማረጋገጥ ዮሐንስ የሣለው ይኽ ሥዕል ‹‹‹አይሁድ በኢየሩሳሌም እንደ ሰቀሉኝ አንተ ደግሞ ኹለተኛ ሰቀልከኝ?››የሚል ድምፅ አሰምቷል፡፡ሥሎ

ሲጨርስ ዮሐንስ ቢስመው ከንፈሩ ከሥዕሉ ጋራ ተጣብቆ ቆይቷል፡፡ይኽ ኹሉ ከሥዕሉ የታየው ተአምራት ነው፡፡‹‹አይሁድ የሰቀሉት ራቁቱን ነበር፡፡ከለሜዳ አስታጥቆ መሣል የተጀመረው ከዚያ ወዲኽ ነው›› እያሉ የሀገራችን ሊቃውንት ይተርካሉ (ጎርጎርዮስ1974፣117)፡፡

(ዐምደ ሃይማኖት፣2010፣146) የሥዕልን አመጣጥ ሚሊዮን በለጠ ቅዱሳት ሥዕላት በሚለው መጽሐፍ ደግሞ ከላይ ከቀረቡት ሐሳቦች ይለያል፡፡ ጌታ በዕለተ ዐርብ መስቀል ተሸክሞ ደሙን እያንጠፈጠፈ ወደ ቀራንዮ ሲወጣ ይከተሉት ከነበሩት ሴቶች መኻል ቬሮኒካ የጌታን ሥቃይ ዐይታ ልቧ በሐዘን ስለተነካ በፊቱ ላይ የሚፈሰውን ደምና ላብ እንዲጠርግበት ሻሿን ወረወረችለት፡፡ርሱም ፊቱን አብሶ መለሰላት፡፡የርሱም ሥዕል ከሻሹ ላይ ታትሞ ተገኝቷል፡፡ከዚኽ በማያያዝ የጌታችንን ሥዕል መሣል ተጀምሯል፡፡

ነቅዕ ሕይወት በሚለው የኃይለማርያም ላቀው መጽሐፍ ላይ እንደተገለጸው ቅዱሳት ሥዕላት በብሉይ ኪዳን የሰው ልጅ ከሕገ ልቡና ወደ ሕገ ኦሪት ሲሻገር መፍቀሬ ሰብእ የኾነው ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር በሊቀ ነቢያት ሙሴ አማይነት ሕገ ኦሪትን በደብረ ሲና ለሕዝበ እስራኤል እንደሰጠ በመጽሐፍ ቅዱስ ተገልጿል፡፡ ሌላው የሥዕል መነሻ ተደርጎ የሚነሣው ጌታ ተገንዞበት የነበረው ከፈን(ሰበን)እና መጠምጠሚያ ነው፡፡ዮሐንስ ወንጌላዊና ጴጥሮስ በባዶው መቃብር ውስጥ ገብተው ያዩት ጌታ ተገንዞበት የነበረው ሰበንና መጠምጠሚያ ላይ የጌታ አካል ታትሞበት ነበር፡፡ይኽንንም በኋላ ጊዜ የተነሡት ምድራውያን ልዩ ምርመራ አድርገው በመጨረሻ ሰው ሠራሽ ቀለም፣እንዲኹም የሠዓሊ ቡሩሽ ያላረፈበት መኾኑንና በተአምር ተሥሎ የተገኘ መኾኑን የቃል እማኝነታቸውን ሰጥተዋል፡፡በአኹኑ ጊዜ ይኽ የመግነዝ ጨርቅ በሮም ይገኛል፡፡(ዐምደ ሃይማኖት፣2010፣149)፡፡በአገራችን የሚገኙ ልዩ ልዩ ገዳማትና አድባራት የአብያተ ክርስቲያናት ግድግዳዎች እና በጥንታዊ የብራና መጻሕፍት ገጾች ላይ በድንቅ ኹኔታ ተሥለው የሚገኙ ሥዕሎች በኢትዮጵያ የሥዕል ጥበብ ረጅም ዘመናትን ያስቈጠረ መኾኑን ያመለክታሉ(የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ፪፣2014፣190)፡፡

የጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት ‹‹ግማደ መስቀሉ››በዐፄ ዳዊት ዘመነ መንግሥት በዐሥራ አራተኛው ምእት ዓመት ከኢየሩሳሌም ወደ ኢትዮጵያ ሲመጣ በተጨማሪም ቅዱስ ሉቃስ በጌደንያ የሣላት‹‹አሆ በኃሊት›› /ተናጋሪት እሽ በጎ ባይ/በመባል የታወቀችው

የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ሥዕልና ‹‹ኩርዐተ ርእሱ››ዐብረው ወደ ኢትዮጵያ እንደመጡ ይነገራል (ከፍያለው፣1986፣48) ፡፡

## ፪.፩.፯ የሥዕል ጥቅም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን

ቅዱሳት ሥዕላት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለሚያምኑ ሰዎች የሚያስገኘው ጥቅም ዘርፈ ብዙ ነው፡፡ ከነዚኽም ጥቅሞች ‹‹ክብረ ቅዱሳን››በሚል ርእስ በአባ ገብርኤል የተጻፈው መጽሐፍ ላይ እንደተገለጸው ሥዕልና ዕጣን የአምልኮት መገለጫዎች እንደኾኑ ይገልጻል፡፡ከሥዕል የሚገኙ ጥቅሞችም አንዱ ትምህርት ሲኾን በሥዕሎች አማካይነት የመጽሐፍ ቅዱስን ታሪክ በምኅጻረ ቃል በኀላና በተረዳ ኹኔታ ማጥናትና ማወቅ እንደሚቻል ረድኤት ለማግኘት እና ምሕረትና ይቅርታን ለመቀበል እንደሚረዳ ተገልጿል፡፡

ይትባረክ ገሠሠ (1992፣59) የታሪክ ማስታወሻ ኪነ-ጥበብ ሥነ-ጥበብ በሚለው መጽሐፍ ላይም የሥዕል ጥቅም ከቅዱስ መንፈስ ጋራ የረቀቀ ዉሕደት ካለን የሥዕልን ክብር ማየት እንደሚቻል እና በሥዕሉ አማካይነት ረቂቅ ኅሊናችን ከቅዱስ መንፈሱ ጋራ እንደሚገናኝ እንዲኹም በሥዕል ላይ ተአምር እንደሚፈጸም ያስረዳል፡፡

እንግዳ መርጊያ(መምህር) ቅዱሳት ሥዕላት በሚል ርእስ ባዘጋጁት መጽሐፍ ስለሥዕል ጠቀሜታ ሲገልጹ ሥዕል ነገረ መለኮትን ያስተምራል፤በጽሑፍ በቃል መረዳት የማይችሉትን ክርስቲያኖች ለማስረዳት፣የቅዱሳንን መንፈሳዊ ተጋድሎ በዘመኑ ባንኖርም በዐይነ ኅሊናችን እንድናይ ለማገዝ፣በሃይማኖትና በምግባር ጸንተን መቆም እንዳለብን ለማስገንዘብ፣ፈውስንና በረከትን፣ርዳታን ከሥዕሉ ባለቤት ለማግኘት እና መንፈሳዊ ተመሥጦ እንዲኖረንና ምድራዊውን ከሰማያዊው ጋራ በመንፈስ እንዲገናኝ እንደሚረዱ በዝርዝር አቅርበዋል፡፡

ብዙዎቹ አብያተ ክርስቲያናት በግድግዳቸው በጣራቸው በዐምዶቻቸው በየመስኮቶቻቸውና በየበሮቻቸው በጌታ፣በእመቤታችን፣በቅዱሳን መላእክት፣በነቢያት፣በሐዋርያት፣በጻድቃንና በሰማዕታት ሥዕሎች የተዋቡና ያሸበረቁ ናቸው፡፡ይኽም የሚኾንበት ምክንያት የጌታም ኾነ የእመቤታችን እንዲኹም የቅዱሳን መላእክትም ኾነ የጻድቃንና የሰማዕታትም ሥዕላቸው በየቤተ ክርስቲያኑ መሣሉ ለሰው ልጅ የተደረገውን ድኅነትና ትድግና እንዲኹም ሥራቸውንና ቅድስናቸውን አጉልቶ ለማሳየት በሥዕላቸው ለመማጠን ምእመናንን በሥዕል ለማስተማር ነው (ከፍያለው፣1997፣53) ፡፡

## ፪.፪ የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

ከዚኽ ጥናት ጋራ በቀጥታ የተገናኙ የሦስተኛ ድግሪ ጥናቶች አላገኘኹም፡፡ይኹን እንጂ ከዚኽ በፊት ከዚኽ ርእስ ጋራ በቅርብ ይኹን በሩቅ ተያያዥነት ያላቸው ጥናቶችን ለማየት

ሞክሬያለሁ።ምንጫቸውም በዐዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የኾኑ በኢትዮጵያ ሥነ-ጽሑፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት አንድ የድግሪ ሚሚያ፣አንድ የኹለተኛ ድግሪ ሚሚያ ጥናቶች እና በቅድስት ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ የሚገኙ በድግሪ የቀረቡ ዐምስት ጥናቶች ናቸው።እንዲኹም በማኅበረ ቅዱሳን የሚገኙ ስድስት የታተሙ መጸሕፍት እና አንድ መጽሔት ይገኙበታል።እነርሱም፦ የሚከተሉት ናቸው።

የመጀመሪያው በአገኘሁ አዳነ (2007ዓ.ም) ለኹለተኛ ድግሪ ሚሚያ ከቀረበው ጥናት ውስጥ ሥዕል፣ሠዓሊነት እና ሠዓሊ ገጸ ባሕርያት በተመረጡ የዐማርኛ ዘመናዊ ልቦለዶች በሚል ርእስ የቀረበው ነው።የጥናቱ ዐላማ በዐማርኛ ዘመናዊ ልቦለዶች ውስጥ ሥዕል፣ሠዓሊነትና ሠዓሊ ገጸ ባሕርያት እንዴትን ለምን ፋይዳ እንደመጡ መመርመርና ሥነ ጽሑፍና ሥዕል ያላቸውን ቁርኝት እና የወል ተጋቦት ማሳየት በሚል ቀርቧል።

ይዞ የተነሣውን ዐላማ ከግብ ለማድረስ የሚያመለክቱ ኺደቶች አሉ።በትንታኔው ሥዕል በልቦለድ ዐውድ ውስጥ፣በልቦለድ ውስጥ የሠዓሊነትና የሠዓሊ ገጸ ባሕርያት ሚና ርእስ ውስጥ ሥዕልና በዐማርኛ ዘመናዊ ልቦለድ ውስጥ የሚገኙትን ሠዓሊ ገጽ ባሕርያትን በማቅረብ ሥነ ጽሑፍና ሥዕልን ያላቸውን ቁርኝት ይተነትናል።ይኸም ሥዕል በአራቱ የልቦለድ ሥራዎች (ከበዓሉ ግርማ ከአድማስ ባሻገር፣ከዳኛቸው ወርቁ አደፍርስ፣ከአዳም ረታ ማሕሌት እና ግርዶሽ ) ውስጥ ሠዓሊ በገጸ ባሕርያት የተሣሉ ሥዕሎችን በማቅረብ ሥነ ጽሑፍና ሥዕል በልቦለዱ ታሪክ ውስጥ ያላቸውን ትስስር ተዘርዝሯል።ገጽ ባሕርያቱ ሠዓሊ በመኾናቸው የቀረቡት ሥዕሎች የልቦለዱን ታሪክ የሚያንጸባርቁ ናቸው።

መረጃዎችን ለመሰብሰብ አገልግሎት ላይ የዋሉት ቀዳማይ እና ካልዓይ የመረጃ ምንጮች ናቸው።ቀዳማይ ምንጮች አደፍርስ፣ ከአድማስ ባሻገር፣ማሕሌትና እና ግርዶሽ የተሰኙ ዘመናዊ የዐማርኛ ልቦለድ እንዲኹም ካልዓይ የመረጃ ምንጭ የኾኑት ደግሞ የተለያዩ ነገረ ኪን እና ኪነ ጥበብ ንድፈ ሐሳባዊ ጽሑፎች እንደተጠቀመ ይገልጻል።ለጥናቱ ትንተና አመቺ እንዲኾን አራት ዘመናዊ ልቦለዶችን መርጧል።

አገኘሁ በዘመናዊ ክርስቲያን የዐማርኛ ልቦለድ ውስጥ ሥዕል፣ሠዓሊነትና ሠዓሊ ገጸ ባሕርያት ለምን ፋይዳ እንደመጡ በመመርመር መቅረቡ እና መረጃዎችን ለመሰብሰብ ቀዳማይ መረጃዎችን መጠቀሙ ከእኔ ጥናትም ሥዕልን ላይ ትኩረት በማድረጉ ከእኔ የጥናት ጋራ ይመሳሰላል።በኪነ-ጥበባትና የነገረ ኪን ንድፈ ሐሳቦችን በመጠቀም የልቦለድ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙት ሠዓሊ ገጸ ባሕርያትንና ሥዕሎቻቸው ተገልጸዋል። የእኔ ጥናት ከዚኽ ጥናት ጋራ የተነሣው ርእሰ ጉዳይ ጋር ይመሳሰላል። የሚለይበት ደግሞ የአገኘሁ አዳነ ጥናት በሥነ ጽሑፍ

ሥራዎች ላይ የሚያተኩር ሲኾን ይኽ ጥናት ደግሞ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሚገኙ ሥዕሎችን የሚመለከት ነው፡፡ አገኝሁ ጥናቱን ለማካኼድ የጠቀሰው ንድፈ ሐሳብ ኪነ ጥበባትና ነገረ ኪን ሲኾን እኔ የተጠቀምኩት ንድፈ ሐሳብ ደግሞ ተግባራዊና ሥነ ልቡናዊ በመኾኑ ይለያል፡፡

ኹለተኛው ሙሐመድ ሰይድ ‹‹የነቢዩ የሱፍና የነቢዩ ሙሳ አሣሣል በቅዱስ ቁርኣን››በሚል ርእስ በ1997ዓ.ም ለድግሪ ሟሟያ አቅርቧል፡፡ይኽ ጥናት ይዞ የተነሣው ዐላማ የቅዱስ ቁርኣንን የገጸ ባሕርያት አሣሣል ለማሳየት እና በቅዱስ ቁርኣን የተጠቀሱትን ኹለት ገጸ ባሕርያትን እንዴት እንደተሣሉ ቅኝት ማድረግ ነው፡፡በሥሩም አራት ዐላማዎችን ይዟል፡፡ ዐላማውም ከእኔ ጥናት ጋራ ተመሳሳይነት አለው፡፡

ሙሐመድ የነቢዩ የሱፍንና የነቢዩ ሙሳን በቅዱስ ቁርኣን ውስጣዊና ውጫዊ አሣሣል አሳይቷል፡፡በዚኽ ውስጥ የገጸ ባሕርያት አሣሣል በድርጊት፣በድምፀት፣በንግግር ወይም በውይይት፣በምልሰት፣በግጭት፣በስም እና የነቢዩ ሙሳንና የነቢዩ የሱፍን ውጫዊና ውስጣዊ ገጽታን ይገልጻል፡፡ የእኔ ጥናት ዋና ርእሰ ጉዳይ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የሚገኙ ሥዕሎችን የአሣሣል ሥርዐት የሚገልጽ በመኾኑ ተዛማጅነት አለው፡፡

በምዕራፍ ኹለት ንድፈ ሐሳባዊ ዳራ ቀርቧል፡፡ የገጸ ባሕርያት አሣሣል በድርጊት፣በድምፀት በንግግር ወይም በውይይት፣ በምልሰት፣ በውጫዊገጽታ፣በግጭት በስም አቅርቧል፡፡ እያንዳንዱም ዝርዝር ተደርገው ቀርበዋል ፤ትርጕም ተሰጥቶቷል፡፡ ይኽም የገጸ ባሕርያቱን በድርጊት፣ በቃላት፣በንግግር እና በውይይት አማካይነት የቀረቡበትን የአሣሣል ኹኔታ የሚያሳይ ነው፡፡

በምዕራፍ ሦስት ላይ የቀረበው ደግሞ የገጸ ባሕርያቱን አሣሣል በቅዱስ ቁርኣን ተገልጿል፡፡በዚኽም ውስጥ የኹለቱ ነቢያት በቃላት አማካይነት የቀረቡበትን ገጽታ ምስል ያስረዳል፡፡ በቁርኣን ታሪክ ውስጥ የተጠቀሱት ባለተሪኮች ማንነታቸውን ለማወቅ በሚደረግ ጥረት ስለግለሰቦቹ የተብራራ ገለጻ እንደማይገኝ እና ውጫዊ ገጽታቸው ጎልቶ የማይታይ መኾኑን የጥናቱ ግኝት አሳይቷል፡፡ ሙሐመድ በጥናቱ ውስጥ ንድፈ ሐሳብ ባለመካተቱ የተጠቀመበት የመረጃ ምንጭ መጻሕፍትን ብቻ በመኾኑ ከእኔ ደግሞ ንድፈ ሐሳብ እና ቃለ መጠይቅ በማድረግ መረጃ በመሰብሰቤ ይለያል፡፡የእኔ ጥናት በቀለም ተቀብቶ፣በቅርጽ ተቀርጾ የሚታየውን ሥዕል የሚያሳይ ሲኾን የሙሐመድ ጥናት ግን ነቢያቱ በቃላት አማካይነት የተሣሉበትን ባህርይ እና ተግባር በምናብ የሚያመለክት በመኾኑ የተለየ ያደርገዋል፡፡የመሐመድ ጥናት በእስልምና እምነት ያሉትን ነቢያት ብቻ በመኾኑ የእኔ ጥናት ደግሞ አጠቃላይ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሚገኙ ሥዕሎችን የአሣሣል ሥርዐት የሚያሣይ በመኾኑ ይለያል፡፡

ሦስተኛውን ሰሎሞን ኃይለማርያም በ2007 ዓ.ም ‹‹Origin and Development of Ethiopian Orthodoxs Tewahido Church Iconology (Analyis in relation with Hymnology)››በሚል ርእስ ለድግሪ ማሟያ ለሥላሴ ዩኒቨርስቲ አቅርቧል፡፡ይኽ ጥናት ይዞ የተሣነው ዐላማ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የአሣሣልን ሥርዐት እያሳየ ያለውን እድገት ያሳያል፡፡በጥናቱ ውስጥ የቅዱሳት ሥዕላትን ምንጭ እና በየዘመኑ የታዩት የአሣሣል ኹኔታዎች በዝርዝር ቀርበዋል፡፡መረጃዎቹን ለመሰብሰብ የተጠቀመው ጥንታዊ የኾኑ ቤተ መዘክሮች በመጎብኘት፣ከሠዓሊዎች ጋራ በመወያየት፣አውደ ርዕይ በመጎብኘት እና የኤሌክትሮኒክ ምንጮች በመጠቀም ነው፡፡የቅዱሳት ሥዕላት የአሣሣል ቀኖና በአብዛኞው የቤተ-ክርስቲያኗ አባላት ዘንድ በቂ የኾነ ግንዛቤ ባለመኖሩ ጥናቱ መንፈሳዊና ሥነ ልቡናዊ ጥቅም እንዳለው አስረድቷል፡፡

የሰሎሞን ጥናት ከእኔ ጥናት ጋራ ይዞ የተነሣው በዐላማው እና በመረጃ ለመሰበብሰብ የተጠቀመባቸው የመረጃ ምንጮቹ የሚመሳሰል ሲኾን የሚለያየው ደግሞ የእኔ ጥናት ንድፈ ሐሳብ የተካተተበት በመኾኑ ነው፡፡

አራተኛው የኔነህ ደምሴ በ2010 ዓ.ም ‹‹The Teaching of the Orthodox Churches Concering the Holy Icon›› በሚል ርእስ ለድግሪ ማሟያ ለሥላሴ ዩኒቨርስቲ የቀረበ ሲኾን በዐምስት ምዕራፍ ቀርቧል፡፡በጥናቱ በእያንዳንዱ ክርስቲያን ቤት ውስጥ የሚገኙ ሥዕላት ላይ ባደረገው ምልከታ የቅዱሳት ሥዕላት ችግሮችን የተገለጸ ሲኾን ይኸውም መሠረታዊ የኾኑ የአሣሣል ትምህርት ተመሳሳይ ኾኖ ሳለ በቤተ-ክርስቲያን ውስጥ የተለያዩ የአሣሣል ሥርዐት እና አደረጃጀት መኖራቸውን፣ተመሳሳይ ባህርይ ያላቸው ቅዱሳት ሥዕላት በተለያየ የአሣሣል ሥርዐት መቅረባቸውን ገልጿል፡፡በየምዕራፎቹ ውስጥ በቅዱሳት ሥዕላት እየታየ ያለውን የምዕራባውያንን የአሣሣል ሥርዐት ተጽዕኖ እና ባህላዊው የአሣሣል ሥርዐት ላይ ያመጣውን ተጽዕኖ እና በየዘመኑ የነበረውን የሥዕል እድገት አሳይቷል፡፡ጥናቱን ለማካኼድ ጥቅም ላይ የዋለው የመረጃ ምንጭ ደግሞ የተለያዩ ቤተ-መጻሕፍትን በመጠቀም መጻሕፍትና ጋዜጣዎችን በማንበብ፣በይነ መረብ(Intrenet)፣በገዳማትና በቤተ ክርስቲያን፣በገበያ ቦታዎች የሚገኙ ቅዱሳት ሥዕላትን በመጎብኘት መረጃዎቹን አቅርቧል፡፡የመረጃ አጠቃቀሙ ከእኔ ጥናት ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡የንድፈ ሐሳብን ባለማካተቱ ደግሞ ከእኔ ጥናት ጋራ ይለያል፡፡

የኔነህ በምዕራፍ ዐምስት ላይ ማጠቃለያና የመፍትሔ ሐሳቦችን አቅርቧል፡፡ቅዱሳት ሥዕላት አስተምህሮ በቀጥታም ኾነ በተዘዋዋሪ ከባዛይታይን እና oriental churches ጋራ የተቀላቀለ መኾኑን ይኽንን መሠረታዊ የኾነ የአሣሣል ሥርዐት ትምህርት እንደሚያስፈልግ አስረድቷል፡፡

ዐምስተኛው ሽመልስ ግርማ 2008ዓ.ም (Servey on Historical and Theological Developmenet of Holy Icons in Ethiopia Orthoox Tewahedo church) በሚል ርእስ ለድግሪ ማሟያ ለሥላሴ ዩኒቨርስቲ የተዘጋጀ ጥናት ነው፡፡ይኸም በኢትዮጵያ ኦርቶዶአስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን የሥዕል ታሪክና እድገት፣የቅዱሳት ሥዕላት ጥቅሞችን፣እና የቅርብ ጊዜ የሥነ መለኮት የቅዱሳት ሥዕሎችን ጥናቶች ጠቀሜታዎች እና በመጽሐፍ ቅዱስ የቅዱሳት ሥዕላት ፅንሰ ሐሳብና ምንጭ አካቷል፡፡

በምዕራፍ ዐምስት ላይ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የቅዱሳት ሥዕላት ባህላዊ አሣሣል እና የሠዓሊዎቹን የአሣሣል ዘዴውን ያስረዳል፡፡በተጨማሪም የኢትዮጵያን ኦርቶዶእስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አሣሣል ሥርዐት ላይ በምዕራባውያን አማካይነት የተደረገውን ተጽዕኖ ያመለከተ ሲኾን ከየኔነህ ጥናት ከእኔ ጥናት ጋራ ተመሳሳይነት አለው፡፡

የሽመልስ ግርማ ባቀረበው ጥናት ላይ የመጀመሪያና የኹለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጮችን ተጠቅሟል፡፡እነርሱም፦ውይይትን በመከታተል፣የተለያዩ ቤተ-መዛግብትን በመጎብኘት፣ቃለ መጠየቅ በማድረግ፣ ምልከታ በማድረግ፣የጽሑፍ መጠይቅ (ዝግ እና ክፍት ቃለመጠይቅ) በማድረግ ጥናቱን አካኺዷል፡፡የተጠቀመው የመረጃ ምንጭ እስካኹን በቅድስት ሥላሴ ዩኒቨርስቲ ከጠቀስኳቸው ጥናቶች የሚለየው ቃለ መጠይቅ በመጠቀሙ ሲኾን ከእኔ ጥናት ጋራ ደግሞ ንድፈ ሐሳብ ባለመካተቱ ይለያል፡፡

ስድስተኛው ዳንኤል ሰይፈ ሚካኤል በ2004ዓ.ም Prospect On The Art Histioy of Ethiopian Orthodox Tewahedo Church (A PANORAMA OF HER INDIGNOUS ICONOGRAHY AND ITS THEOLOGICAL BACK GROUND) በሚል ርእስ ለድግሪ ማሟያ ያቀረበው ለቅድስት ሥላሴ ዩኒቨርስቲ የተዘጋጀ ጥናት ነው፡፡ በጥናቱም ላይ የቀረበው የኢትዮጵያን ጥንታዊ የሥዕል ታሪክ በመከፋፈል ማለትም የጎንደርን፣የመካከለኛው እና ዘመናዊውን ዘመን አሣሣል በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥዕል የሚዘጋጅባቸውን ግብአቶችን በመከፋፈል በዐምስት ምዕራፎች ቀርቧል፡፡የሥዕሎችን ውክልና በመግለጽ እና የተለያዩ ዐውደ ጥናቶች ላይ በመሳተፍ፣የሥዕል ክፍለ ጊዜ ትምህርቶችን በመከታተል፣ሙዜየሞችን በመመልከት፣ምልከታበማድረግ፣የጽሑፍ መጠይቅ፣ቃለ መጠይቅ በማድረግ እና ድረ ገጾችን በመጠቀም መረጃዎቹን ሰብስቧል፡፡የዳንኤል ጥናት ከእኔ ጥናት ጋራ የሚመሳሰለው ርእሰ ጉዳዩ ተያያዥነት ያለው ስለኾነ ነው፡፡የሚለየው ደግሞ የእኔ ጥናት ንድፈ ሐሳቦችን ያካተተ በመኾኑ ነው፡፡

## ፪.፫ የታተሙ ተዛማጅ ጥናቶች

ስለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥዕል የሚያወሡ በተለያዩ ዘመናት የተጻፉ መጻሕፍት አሉ፤በዚኽም ዳሰሳ ለዚኽ ጥናት ተዛማጅ የኾኑ የታተሙ መጻሕፍት አሉ።

አንደኛው ኃይለምርያም ሽመልስ ኦርቶዶክሳዊ ቅዱሳት ሥዕላት በሚል ርእስ በ2007 ዓ.ም የታተመው መጽሐፍ ነው።መጽሐፉ በ0ምስት ምዕራፍ የተዘጋጀ ሲኾን የቅዱሳት ሥዕላት ታሪካዊ አመጣጥ፣የኢትዮጵያ ኦርቶዶስ ተዋሕዶ ቤተ ክስቲያን ቅዱሳትሥዕላት ክብር፣ቅዱሳት ሥዕላት በዘመናችን፣ሥዕልን የሚቃወሙ መናፍቃን ከቤተ ክርስቲያን የተሰጠ ምላሽን፣የአጋንንትናየመናፍቃን አሣሣል፣የቅዱሳት ሥዕላትን አቀማመጥ፣የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ-ክርስቲያን ለሥዕል ጥበብ ያበረከተችውን አስተዋጽኦ፣ወቅታዊ ፈተናዎች እና መፍትሔዎቻቸው በቅዱሳት ሥዕላት የተፈጸሙ ተአምራትን የሚል ርእሶችን በማካተት የተዘጋጀ መጽሐፍ ሲኾን ከዚኽ ጥናት ጋራ የሚመሣሠለው ጥናቱ በሥዕሎች ላይ ትኩረት ያደረገ መኾኑ አሣሣላቸውን በማካተቱ ነው።

በመጽሐፉ የቀረቡት ዝርዝር ሐሳቦች የሚያመለክቱት በኢትዮጵያ ኦርቶዶእስ ተዋሕዶ ቤተ-ክርስቲያን የሚገኙ ቅዱሳት ሥዕላት ትውፊትና ሥርዐት የጠበቁ ሥዕላት እንዲዘጋጁ ጥቆማ የሚሰጥ ነው።የሥዕሎቹን ትውፊት መጠበቅ ያስፈለገበትን ምክንያት የቀረበ ሲኾን ከዚኽ ጥናት ጋራ ተዛማጅነቱ የጎላ ነው።

ኹለተኛው ተዛማጅ የታተመ መጽሐፍ የኃይለ ማርያም ሽመልስ ሥዕለ ቅድስት አርሴማ በሚል ርእስ በ2008ዓ.ም ያዘጋጀው መጽሐፍ ነው።ይኽ ጥናት ተደጋጋፊ የኾኑ ሐሳቦችን የያዘ ነው።በጥናቱም ላይ የቅድስት አርሴማ ሥዕል ላይ ያገኛቸውን የአሣሣል ስሕተቶችን በመግለጽ ማብራሪያ አቅርቧል።የቅዱሳት ሥዕላትን ታሪክ፣የቅዱሳት አንስትን አሣሣል፣ የቅዱሳት አንስትን ሥዕል አሣሣል የተጋድሎ ሕይወታቸውን የሚያሳይ መጽሐፍ ነው።

ኃይለ ማርያም ሽመልስ ቅድስት አርሴማ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ- ክርስቲያን ከቅዱሳት አንስት ወገን በመኾኗ ስትሣል ጸጕሯን ተሸፋፍና መሣል እንዳለባት ያስረዳል።ረዥም ዘመናት ያስቆጠረ በ15ተኛው መ.ክ.ዘ ገደማ በደብረ ቤቴል ኮሕሎ ዮሐንስ ቤተ ክርስቲያን የሚገኘው ገድለ ሰማዕታት ላይ የተሣለ ሥዕል መገኘቱን አመልክቷል።የቅድስት አርሴማ አሣሣል ፀጕሮቿን ተሸፋፍና እጆቿን ዘርግታ በአንቃዕድዎ ስትጸልይ እንደተሳለች እና አኹን በየቦታው የሰማዕቷ ላይ የተጠቀሱትን ዘንባባ፣መስቀል እና ጽዋ ምልክቶችን ይዛ እንደማትታይ አሳይቷል።ዘንባባ እና ጽዋ ይዘው የሚሣሉት ሌሎች ቅዱሳት አንስት እንደኾኑ በምርምሩ ያገኘውን መረጃዎች ገልጿል።በተጨማሪም የቅድስት አርሴማ ሥዕል በግብጽ ኦርቶዶክስ ቤተ-ክርስቲያን፣በአርመን

ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እና በምሥራቅ ባይዛንታይን አብያተ ክርስቲያናት አሣሣል በምስል ያሳየ ሲኾን ዘንባባ እና መስቀል ይዛ እንደማትታይ ያስረዳል፡፡በቅድስት አርሴማ ተብለው ተሠራጭተው በአብዛኛው የሚሸጡ ሥዕሎች የርሷ አለመሆናቸውን አረጋግጧል፡፡በአጠቃላይ በመጽሐፉ የቅዱሳን አንስት አሣሣልን የሚገልጽ ነው፡፡

ከመጽሐፉ የኔ ጥናት የሚለይባቸው ነጥቦች አሉ፡፡አንደኛው መሠረታዊ የኾኑ የአሣሣል ትውፊቶችን ይዘረዝራል፤በየመደብሩ የሚገኙትን ቅዱሳት ሥዕላት ምልከታ በማድረግ ይመረምራል፡፡በመጽሐፉ ያልተካተቱ ሌሎች ቅዱሳን ሥዕላት በመኖሩ ነው፡፡

ሦስተኛው መጽሐፍ የሚሊዮን በለጠ አሰፋ ነው፡፡የተጻፈው በ1994ዓ.ም ሲኾን መጠሪያውም ቅዱሳን ሥዕላት ይሰኛል፡፡ጸሓፊው በአብዛኛው ያቀረበው ምስጢረ ሥላሴ፣ መላእክት፣ቅድስት ድንግል ማርያም፣ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያለውን ዜና እና ጻድቃን ስለሚባሉት እና የቅዱሳት ሥዕላት ታሪካዊ አመጣጥ፣የሥዕላት ጥቅም ያስረዳል፡፡ከእኔ ጥናት ጋራ የሚመሳሰለው የቅዱሳት ሥዕላትን ታሪካዊ አመጣጥን ስለሚገልጽ ነው፡፡ የሚለየው ደግሞ የእኔ ጥናት ቅዱሳን ሥዕሎችን የአሣሣል ሥርዐት በመመርመሩ ነው፡፡

አራተኛው መጽሐፍ የከፍያለው መራሒ ነው፡፡የታተመው በየካቲት 16/1986ዓ.ም ነው፤ ርእሱም የቤተ- ክርስቲያን አስተዋፅኦ ለኢትዮጵያ ሥልጣኔ ይሰኛል፤፤መጽሐፉም በአራት ክፍሎች የቀረበ ሲኾን በአራተኛው ክፍል የቀረበው ኪነ ጥበባት የሚል ነው፡፡በዚኽ ርእስ ሥር የሥዕልን ምንነት እና ስለሥዕለ አድኅኖ ክብር ይገልጻል፡፡የጥንት ኢትዮጵያውያን መንፈሳዊ ሥዕሎችን የሚሥሉ የቀድሞ አባቶቻችን ከፍተኛ የኾነ ትምህርተ ክርስትና የነበራቸው መኾኑን የሚሥሏቸው መንፈሳውያት ሥዕሎችም በምሥጢር ከቲዎሎጂ ጋራ እንደማይጋጩ ያመለክታል፡፡በዘመናችን ያለውን መንፈሳዊ ሥዕሎች በየቤተ ክርስቲያኑ የሚሥሉ አንዳንድ ሠዓልያን የቲዎሎጂ ትምህርት ስለሌላቸው ያልተዋሐደ ጥሬ ቀለም መቀባት እንደኾነ የሚገልጽ ነው፡፡እንደምሳሌ የቀረበው አንድ ሠዓሊ በአንድ በታወቀ ቤተ-ክርስቲያን የሥላሴን ነጣጥለው ለየብቻቸው መሣላቸው የምስጢረ ሥላሴን ትምህርት የሚያዛባ እንደኾነ ያሳያል፡፡በኢትዮጵያውያን አእምሮ ታስበው የሚሠሩትን የሥዕል የፈጠራ ውጤቶች የሚያዳክሙና የሚለውጡ ከቤተ መንግሥት ቁጥጥር ሳይደረግበትና ትኩረት ሳይሰጠው ከምዕራብና ከምሥራቅ ሥዕሎች ወደ አገራችን ያለገደብ መጉረፉን ያመለክታል፡፡የዚኽ ጥናት ዐላማም በየመደብሩ የሚታዩትን ጉራማይሌ የኾነ የቀለምን እና የአሣሣልን ሥርዐት ለመመርመር በመኾኑ በመጽሐፉ የቀረቡት ሐሳቦች ተመሳሳይነት አላቸው፡፡የእኔ ጥናት የሚለየው የአሣሣል ሥርዐቱን ለመርመር ጥረት ስለሚያደርግና ትውፊቱን ለማሳየት ስለሚሞክር ነው፡፡

ዐምስተኛ ኾኖ የታተመው ጽሑፍ የማኅበረ ቅዱሳን መጽሔት ነው።በ2010ዓ.ም በታተመ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጥናት መጽሔት የተዘጋጀ ሲኾን መጽሔቱ ስምንት ጥናቶች አካቷል።ከዚኽ ጥናት ጋራ ተዛማጅነት ያለው ጥናት ደግሞ በእንግሊዘኛ የተጻፈው Roak art at Bete Mariam,Lalibela;Biblical and Archaeological Interpretation ይሰኛል።የጥናቱ አዘጋጅ ጌታቸው መርሻ ነው።ጥናቱ በላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት መካከል ቤተ-ማርያም የሚገኘውን በተለያዩ ቀለማት ያሸበረቀውን ከታሪክና ከመጽሐፍ The fish and the bread,The two fighting oxen depicted in black and red colors, The bas-relief figures of two riders on horseback killing the dragon with a spear በሚሉ የተመረጡ ሐሳቦች ላይ ትኩረት አድርጎ የተጻፈ ነው።ከእኔ ጥናት ጋራ የሚመሳሰለው በሥዕል ላይ ያተኮረ በመኾኑ ሲኾን የሚለየው ደግሞ ሥዕሎቹ በውቅር አብያተ ክርስቲያናት ላይ የሚገኙ ሥዕሎች ላይ ትኩረት ያደረገ በመኾኑ ነው።

ስድስተኛ ኾኖ የታተመ ጽሑፍ የእንግዳ መርጊያ ነው።በ2013ዓ.ም የታተመ ሲኾን የቅዱሳት ሥዕላት ክብር እና አገልግሎት የቅዱሳት ሥዕላት ተቃዋሚዎች ነን በሚሉ ርእስ የቀረቡ ናቸው።በክፍል ኹለት ላይ ቅዱሳትና ቅዱሳን አበው ስለቅዱሳን አበውና ስለቅዱሳት አንስት የሚገልጽ ነው።የቅድስት በርባራን፣የቅድስት አርሴማን የቅድስት ሉሲ/ያን ሥዕላት ልዩነት እና የቅድስት መሪንና እና የኢትዮጵያዊቷን ጻድቅት የቅድስት ክርስቶስ ሠምራን ሥዕል ልዩነት ይገልጻል።ቅድስት ክርስቶስ ሠምራ ተብሎ የሚቀርበው ሥዕል በገድሏ ካለው ታሪክ ጋራ የማይዛመድ መኾኑን አስረድቷል።በተጨማሪም ቅዱሳን አበው ወሰማዕታት በሚል ርእስ የቀረበ ሦስቱ ቅዱሳን አበው ባሕታውያን መገለጫ የኾነው ተመሳሳይት ስላለው እና የገብረ መንፈስ ቅዱስ ሥዕል ከኹለቱ ባሕታውያን ለየት ያለ መኾኑን ያስረዳል።ጸሓፊው የገብረ የገብረ መንፈስ ቅዱስ ሥዕል ከኹለቱ ባሕታዊያን ለየት ያለ መኾኑን እና የገብረ መንፈስ ቅዱስ ሥዕል ሙሉ በሙሉ ጸጉር የተሸፈነ መኾኑን ያስረዳሉ።የአባ ጳውሊ ርእሰ ባሕታውያን እና በተለይ የአባ ኖብ የጺሕማቸው ርዝመት ከአባታችን ከገብረ መንፈስ ቅዱስ ጋራ ስለሚመሳሰል ባለማወቅ አንዳንድ ኢትዮጵያውያን እነዚኽን ቅዱሳት ሥዕላት ሲመለከቱ በገብረ መንፈስ ቅዱስ ስም የተሣሉ ናቸው ብለው የሚጠሩ ወገኖች መኖራቸውን በመስማታቸውና ሰማዕቱ ቅዱስ አበ ኖብንም ጻድቁ በልጅነታቸው ሳሉ የነበረ ሥዕላቸው ነው በማለት አንዳንድ ሰዎች ሲናገሩ በመስማታቸው በዐጭሩ የቅዱስ አባ ኖብን ታሪክ በማቅረብ ልዩነቱን ለማሳየት ቀርቧል።በመጽሐፉ ውስጥ ቅዱሳት ሥዕላት የሚጠሉ(ኢኮኖላትሪያ)ና መጥፋት አለባቸው የሚሉ እና የሥዕልን ክብር ወደ አምልኮት መቀየር የሚለውን ሐሳብ የሚያራምዱ ቡድኖችን በመግለጽ ለነዚኽ ሐሳቦች መልስ የሚኾን

ሐሳቦችን በማቅረብ ተዘጋጅቷል፡፡ከእኔ ጥናት ጋራ የሚመሳሰለው ቅዱሳት ሥዕላት በተመለከተ የሚታዩ ችግሮች ላይ መሠረት በማድረጉ ሲኾን የሚለየው ደግሞ ከእኔ ጥናት ተጨማሪ ሌሎች ሥዕላት በማካተቱ ነው፡፡

ሰባተኛው ኾኖ የታተመ ጽሑፍ የአንዱዓለም ዳግማዊ ነው፡፡መጽሐፉ 2002ዓ.ም የታተመ ነው፡፡መጽሐፉ አራት ምዕራፎች ያሉት ሲኾን በአራተኛው ምዕራፍ የቀረበው ርእስ ቅዱሳት ሥዕላትን በተመለከተ ማብራሪያ ተሰጥቶበታል፡፡ይኸውም የቅዱሳት ሥዕላት አመጣጥ፣ የቅዱሳት ሥዕላትን ኅብረቀለማት ሃይማኖታዊና መንፈሳዊ ትርጓሜያት እና የኦርቶዶክሳውያን ቅዱሳት ሥዕላትን ልዩ ገጽታዎች በመግለጽ ቀርቧል፡፡በመኾኑም ከእኔ ጥናት ጋራ ተመሳሳይነት ያለው ሲኾን የሚለየው ደግሞ በመጽሐፉ ውስጥ ያልተካተቱን ሥዕላት የአሣሣልን ሥርዐት በዚኽ ጥናት ውስጥ ስለሚቀርብ ነው፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

በዚኽ ምዕራፍ ቅዱሳት ሥዕላት በዘፈቀደ የሚሣሉ ባለመኾናቸው የአሣሣል ሥርዐታቸውን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ይኽ ምዕራፍ ውስጥ የሥዕሎችን ትውፊት ይቃኝበታል፡፡ሥዕሎች ሲዘጋጁ ቀኖናዊ በመኾናቸው ሥርዐት እና ደንብ ወጥቶላቸው አበው በእግዚአብሔር መንፈስ ተመርተው የሚሏቸው ናቸው፡፡ሥርዐቱ ከትምህርተ ሃይማኖት ጀምሮ መልክአ የቀለም አጠቃቀም የወጣላቸው ሲኾን የቤተ ክርስቲያን ሥዕላት የሚባሉት እነዚኽን ቀኖናዎች ጠብቀው የሚሣሉ መኾን ይኖርባቸዋል (ኃይለማርያም፣2007፣70)፡፡በመኾኑም የቤተ ክርስቲያን ትርጉም፣የቀለም ትርጓሜዎች እና የጥንት የሥዕልን የትምህርት አሠጣጥ ዝርዝር ቀርቧል፡፡

## ፫.፩ የቤተ ክርስቲያን ምንነት

ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል ትርጓሜ ደስታ ተክለወልድ መዝገበ ቃላት ላይ እንደተገለጸው ‹‹በቁሙ የክርስቶስ ወገኖች ለጸሎት፣ለምስጋና፣ለስግደትና ለቍርባን የሚሰባሰቡባት ታቦት፣ መስቀልና ሥዕል ያሉባት ናት፡፡ክርስቲያን ቤት ባለ፫ ክፍል ናት፡፡እነዚኹም ቅኔ ማሕሌት፣ ቅድስትና መቅደስ ናቸው፡፡ምእመናንም ቤተክሲያን ይባላሉ፡፡››

ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ቁጥር ፩ በሚለው መጽሐፍ ደግሞ እንደሚከተለው ተገልጿል፡፡

> ‹‹ቤተክርስቲያን››የምንለው የክርስቲያንን ሃይማኖት ነው፡፡ትርጓሜውም ማደር፣ወገን፣ነገድ፣ዘር፣ጉባኤ፣ማኅበር፣ ቤተሰብ ማለት ነው፡፡ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል መሠረቱ ከግዕዝ ነው፡፡የቃሉ መነሻም ቤተ፣ዐደረ፣ይበይት፣ ይቢት፣ በያቲ በያትያን፣ በያትያት የሚለው ቃል ነው፡፡

ቤተ ክርስቲያን በቀጥተኛ ትርጉሙ ቤተ ኦርቶዶክሳውያን ማለት ነው፡፡በዐለም ዓቀፍ ትርጉሙ ቤተ ክርስቲያን ማለት የቦታ ሳይኾን የወገን የአማኞች የምእመናን መጠሪያ ኾኖ እናገኘዋለን፡፡በተለዋጭ ትርጉሙ የክርስቲያኖች መሰብሰቢያ፣መገናኛ፣ ቤተ ክርስቲያን ማለት ሕንጻው፣ግንቡ ኾኖ እናገኘዋን (ሐዲስ የሻነው፣2010፣18) ፡፡ማንኛውም መንፈሳዊ አገልግሎት መንፈሳዊ ምስጢር የሚከናወንበት ቤተ ክርስቲያን ይባላል (ሐዲስ የሻነው፣49፣2010)፡፡

## ፫.፪ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የቀለማት ትርጉም

ዓለም ስትፈጠር የተለያዩ ቀለም የያዘች ናት፡፡በተለያየ ቀለማት የተዘጋጁ ሥዕላት ውበታቸው ይጎላል፤በቀለማት መሸብረቃቸው ተመልካቹ ትኩረት እንዲሰጥ ያደርገዋል፡፡ኦርቶዶክሳዊ ቅዱሳት

ሥዕላትም በተለያዩ ቀለማት የሚሣሉ ናቸው፡፡እያንዳንዱ ቀለም የተለያየ ትርጉም አሏቸው፡፡ሥዕላቱ በያዙት ትርጓሜ መሠረት የተለያዩ መልእክቶችን ለማስተላለፍ ያስችላሉ፡፡የቅዱሳት ሥዕላትን መልእክት ለመረዳት የቀለማቱን ትርጓሜ ማወቅ አስፈላጊ ነው፡፡ኦርቶዶክሳዊ ቅዱሳት ሥዕላት አስተምህሮ መሠረት መደበኛ በመኾን ሌሎች ቀለማትን የሚያስገኙ ሦስት ዐበይት ቀለማት አሉ (አንዱዓለም፣ 2002፣127) ፡፡ እነርሱም ሰማያዊ፣ቢጫና ቀይ ናቸው፡፡እነዚኽ መሥራች ቀለም በመኾናቸው በእነርሱ አማካይነት ሌሎች ሕብረ ቀለማት ይመሠረታሉ፡፡

ቀለማት የሚያስተላልፉት የየራሳቸው ትርጕም አላቸው፡፡ነቅዐ ሕይወት በሚለው የአንዱዓለም መጽሐፍ ላይ የሚከተሉት የቀለማት ትርጓሜዎች ቀርበዋል፡፡

የነጭ፡-ቀለም የብሩህነት መግለጫ ቀለም ሲኾን በምስጥራዊ ትርጓሜው ብርሃንነትንና ዘላለማዊነትን ይገልጻል፡፡አምላካዊ መገለጥን ጸጋ እግዚአብሔርንና በመለኮታዊ ብርሃን ሕይወታቸው የበራ ቅዱሳንን ያመለክታል፡፡ንጽሕናንና ቅድስናን፣ደስታንና ሐሤትን፣መለኮታዊ ጥበብንና አምላካዊ ክብርን የሚያስረዳ ቀለም ነው፡፡‹‹እጠበኝ ከበረዶም ይልቅ ነጭ እኾናለኹ›› (መዝ.54፣7) ፡፡

ሰማያዊ፡- ከኹሉም ቀለማት ይበልጥ ጠንካራ ቀለም ሲኾን ሰማይንና ሰማያዊነትን፣ከዚኽ ከምድራዊው ዓለም የመለየት ሕይወትን ያመለክታል ፤ ትሕትናንም ያሳያል፡፡ ጥቁር ሰማያዊ የመለኮታዊ ሕይወትን ምስጢር ያስረዳል፡፡

ቀይ፡- የሕይወት መሠረት ከኾነው የደም መልክ ጋራ ተመሳሳይነት ያለው መካከል ዋንኛው ነው፡፡ለጋነትን ወይም ወጣትነትን፣ ውበትን፣ሀብትን፣ ጤንነትን፣ ፍቅርን፣ መሥዋዕትነትንና ሕይወትን ያመለክታል፡፡

ሐምራዊ፡-ኃይልንና ሥልጣንን የሚያመለክት ቀለም ነው፡፡

አረንጓዴ፡-አብዛኛውን ጊዜ ከዕፀዋት ዓለምና ከጸደይ ወቅት ጋራ የሚገናኝ ሲኾን ትርጕሙ መታደስን፣ልምላሜን፣ደኅንነትን፣ዐዲስ ሕይወትን ፣ተስፋን ያመለክታል፡፡

ቢጫ፡-ይኽ ቀለም በዋናነት እውነትን፣እውነተኛነትን የሚገልጽ ቀለም ነው፡፡

ወርቅ ወርቃማ፡-ይኽ ቀለም ብሩህና ነጸብራቃዊ ሲኾን በምስጥራዊ ትርጓሜው ‹‹ፀሓይ ዘኢየዐርብ ወማኅቶት ዘኢይጠይፍእ፣ፀሓይ ዘዘልፈ ያበርህ ዲበ ቅዱሳን፤የማይጠልቅ ፀሓይ፤የማይጠፋ ብርሃን ለቅዱሳን ዘወትር ዕውቀትና

ሕይወት››የኾነውን ጌታ የሚያበራላትን ሰማያዊቷን ኢየሩሳሌምን ይገልጻል (ራእይ21፥23 ሚል4፥2 ማቴ፥4፥14፥17፥2) ።ዳግመኛም ወርቅ በባሕርዩ የማይለወጥ ንጹሕና ጽሩይ በመኾኑ ለክርስቲያኖች ዘላለማዊ ሕይወትን፣እምነትና ፀሓየ ጽድቅ የተባለውን የኢየሱስ ክርስቶስን መለኮታዊ ብርሃንነት ያመለክታል።

ቡኒ፣ቡናማ፡- የመሬት የመሬታዊነት፣የሸክላ ወይም የትቢያ የአፈርነት ቀለም ነው።በመኾኑም ይኽ ዐይነቱ ቀለም ጠውልገው የረገፉና የሞቱ ቅጠሎችን፣መፀውን፣የዕፀዋትን መፍረስና መበስበስ ወደ አፈርነት መለወጥ ያመልክታል።ቡኒ ወይም ቡናማ ቀለም ትርጓሜው አብዛኛውን ጊዜ የገዳማውያን አባቶች እናቶች አልባሳት የሚሣሉበት የቀለም ዐይነት ነው።መንፈሳዊ ትርጓሜውም ድኽነትን፣ምናኔን ትሕትናን ይገልጻል።በዐጭር አፈርነትን ፣መሬታዊነትንና መሞትን የሚያሳየው ይኽ ገዳማዊ ቀለም መናንያኑ ለዚኽ ዓለም ምውታን መኾናቸውን ያስገነዝባል፡ ፤በአንጻሩ ደግሞ ገዳማውያኑ ለመንፈሳዊው ገድልና ትሩፋት እንደለሰለሰ መልካም መሬት የተመቸ በጸጋ እግዚአብሔር የተዘጋጀ ሕይወት እንዳላቸው ይጠቁማል።

ጥቁር፡-የብሩህነት መታወቂያ ከኾነው ነጭ ቀለም ተቃራኒ በመኾኑ ጥቁር ቀለም ብርሃንን ሳያንጸባርቅ ውጦ የሚያስቀር የቀለም ዐይነት ነው።ከዚኽ በተጨማሪ ደግሞ ጥቁር ቀለም ህልውና ማጣትን፣መዘበራረቅን፣ጭንቀትንና ሞትን የሚገልጽ ቀለም ነው።ይኹን እንጂ ከመንፈሳዊ ምስጢሩ አንጻር ስናየው ደግሞ የሌሊት ጨለማ ዐልፎ የሚመጣውን የንጋት ብርሃን ተስፋ አመልካችም ነው።በዐጭሩ ጥቁር ቀለም ወደ ዐዲስ ሕይወት ተስፋ መሸጋገሪያ ቀለም ነው።

የእነዚኽን ቀለማት ትርጓሜ ማወቅ ቅዱሳት ሥዕላት የያዙትን መልእክት ለመረዳት ያስችላል።ቀለማቱን ከትርጕማቸው ጋራ እያገናዘቡ ሲመለከቱ መንፈስን ያድሳል፤ ተስፋን ያጎናጽፋል። ይኽ የቀለማት ትርጓሜ እና የአሣሣል ጥበብ ኹሉም ሰው እንዲያውቅ የሚያስችል መርሐ ቢፈጠር መልካም ነው።

የቀለማት ትርጓሜ እንደየሀገራት ባህልና አኗኗር ይለያያል።ከላይ የቀረበው አንዱዓለም ያቀረቡት ትርጓሜም የሚያመለክተው የራሺያን ሀገር የቀለም ትርጓሜ የሚያሳይ ነው።ለምሳሌ ከላይ ከተጠቀሱት ቀለማት መካከል ሐምራዊ፣ወርቅ ወርቃማ፣ቡኒ ቡናማ፣ጥቁር በኢትዮጵያ አይገኙም።በመኾኑ ሥዕሎች ሲሣሉ በአካባቢው በሚገኙ ቀለማት ሊሣሉ ይችላሉ።‹‹በቤተ-ክርስቲያን አብዛኛው ጊዜ ሠዓልያን የሚጠቀሙባቸው ቀለማት ሰማያዊ፣ቀይ፣አረንጓዴ እና ቢጫ

መኾናቸው አንዱ መለያ ነው፡፡ይኽ የኾነበት ደግሞ አረንጓዴ፣ቢጫ፣እና ቀይ በቀላሉ በሀገራችን ከሚገኙ ዕፀዋት መዘጋጀት ስለሚችሉ ነው፡፡ሰማያዊ ቀለም ደግሞ በብዛት ከውጭ ሀገር ይመጣ ነበር (ስምዐ ጽድቅ ከሐምሌ ፲፮-፴ቀን፳፻፮ዓ.ም) ፡፡የቀለም ምርጫ እንደሚሣለው ሥዕል ማንነትና ታሪክ ይለያያል (ሕይወት 2012፡50) ፡፡

ግራጫ ቀለም የሰይጣን መግለጫ ነው (ኃይለ ማርያም ሠኔ 20፣2015) ፡፡ጥቁር ቀለም በብዛት አገልግሎት ላይ አይውልም፡፡ሠዓልያን የሚጠቀሙበት የአንድን ሥዕል ተፈጥሯዊ ቅርጽ ለማስያዝ ሲሉ ነው፡፡ለምሳሌ የአንገት የአገጭ መለያያ ላይ ይጠቀሙበታል (ስምዐ ጽድቅ ከሐምሌ ፲፮-፴ ፳፻፮ዓ.ም) ፡፡

## ፫.፫ የትውፊት ምንነት

የትውፊት የሚለው ፅንሰ ሐሳብ ሰፊ ነው፡፡የቃሉ ትርጓሜውም‹‹ትውፊት፡-ወፈየ ካለው የግዕዝ ቃል የወጣ ሲኾን ትርጕሙም ውርስ፣ቅብብል ማለት ነው፡፡ይኸውም አንድ ትውልድ ከርሱ በፊት ከነበሩት የሚወርሰው፣የሚያገኘው፣የሚቀበለው ነገር ነው፡፡ኺደቱም በዚኽ የሚያበቃ ሳይኾን ርሱም በተራው ለተተኪው ያስተላልፋል›› (ማኅበረ ቅዱሳን፣ቤተ ክርስቲያንኽን ዕወቅ አንደኛ መጽሐፍ፣1988፣9) ፡፡

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የምታምነውና የምታስተምረው እምነት በቅዱሳት መጻሕፍት፣ በብሉይና በሐዲስ ኪዳን ከዚኽም ጋራ ከሐዋርያት ጀምሮ ባፍ-በመጣፍ፣በቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ትምህርትና ትውፊት ላይ የተመሠረተ ነው (ጎርጎርዮስ፣1974፣101) ፡፡

ትውፊት ሊቀ ካህናት ክንፈ ገብርኤል አልታየ፣በፈለገ ጥበብ መጽሔት 2ተኛ ዓመት ቁጥር /5 1992 ዓ.ም ገጽ 15 ላይ እንደሚከተለው ገልጸውታል፡፡

> ትውፊት፡-በቃል ወይም በጽሑፍ ወይም በተግባር እንቅስቃሴ ከአንዱ ወደ ሌላው የሚተላለፍ ታሪክ፣ትምህርት፣ ባህል፣ወግና ሥርዐት ነው፡፡ትውፊት በተጨባጭ በትክክል የተደረገ፣የተፈጸመ የተገኘ እንጂ ተረትና ፤ልብ ወለድ አይደለም፡፡ከሕገ ልቡና ወደ ሕገ ኦሪት፣ከሕገ ኦሪት ወደ ሕገ ወንጌል፣ከሕገ ወንጌል ወደ ሕገ አበው ወይም ከዘመነ አበው ወደዘመነ ብሉይ፣ከዘመነ ብሉይ ወደ ዘመነ ሐዲስ፣ከዘመነ ሐዲስ ወደ ዘመነ ሊቃውንት፣ከዘመነ ሊቃውንት ወደ ዘመናችን ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ የተወረሰና ለተከታዩ ትውልድ የተላለፈ ነው፡፡ትውፊት ልማደ ሀገርን፣ሕገ እግዚአብሔርን፣ባህለ ሃይማኖትን ኹሉ የሚያጠቃልልና እንደመጽሐፋዊ ሕግ ኾኖ ሊያዝ የሚችል ነው (ሊቀ ካህናት ክንፈ ገብርኤል አልታየ፣ፈለገ ጥበብ መጽሔት) ፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ሥርዐት አምልኮትና የውጭ ግንኙነት (ሐምሌ 19988 ዓ.ም ገጽ 17) በሚል ርእስ የቀረበው ጽሑፍ ደግሞ ትውፊትን እንደሚከተለው ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡

> ትውፊት ማለት ከጥንት ጀምሮ በቤተ ክርስቲያን በኵል ቃል በቃል ሲነገር የመጣ በቃልም፣በጽሑፍም ከአበው ወደ ትውልድ ሲተላለፍ የኖረና የሚኖር ማለት ነው፡፡ትውፊት በቅዱሳት መጽሐፍ ያልተጻፉትን የእምነት የሥርዐት የትምህርትና የታሪክ ውርሶች እያጎላ ያቀርባል፡፡መሠረታቸውም ቅዱሳት መጻሕፍት ኾነው በትርጕም ያልተገለጡትን በተግባር ያሳያል (የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ሥርዐተ አምልኮትና የውጭ ግንኙነት ሐምሌ 1988፣47) ፡፡

ትውፊት የሚተላለፍባቸው መንገዶች በቃል እና በጽሑፍ የሚገኙ ሲኾኑ በአብዛኛው የሚተላለፈው በቃል እንደኾነ ተገልጿል፡፡ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፈ የሚኼድ መኾኑን በተለያዩ መጻሕፍት ላይ የቀረቡ ጽሑፎች ያመለክታሉ፡፡የቅዱሳት ሥዕላትም ትውፊትን ጠብቀው መሣል እንዳለባቸው የሚጠቁሙ ሐሳቦች አሉ፡፡‹‹ሠዓልያን ሥዕለ ቅዱሳንን ሲሥሉ ቤተ ክርስቲያን በቃልና በጽሑፍ ያቆየችውን መሠረት አድርገው ገልጸዋል (ቤተ ክርሲቲያንኽን ዕወቅ አንደኛ መጽሐፍ፣1998፣9) ፡፡ይኽም የሚያመለክተው ቅዱሳት ሥዕላት ሲሣሉ ትውፊትን መሠረት በማድረግ መኾኑን የሚያሳይ ሐሳብ ነው፡፡

ትውፊት እግዚአብሔር በቅዱሳኑ ዐድሮ ያዘጋጀው እንጂ ተራ የፈጠራ ሐሳብ አለመኾኑን ቅዱስ መጽሐፍ ያረጋግጣል፡፡‹‹ይኽን በመጀመሪያ ዕወቁ፤በመጽሐፍ ያለውን ትንቢት ኹሉ ማንም ለገዛ ራሱ ሊተረጕም አልተፈቀደም፤ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና፡፡ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ›› (2 ጴጥ.1.21)፡፡

ትውፊት የምንሠራውን ሥራ ሥርዐት እንዲኖርው ለማድረግ እንደሚቻል እና ቃላዊ እንደኾነ ያሳያል፡፡ትውፊት የሚለውን ቃል በቃል የሚተላለፍ ለሥነ ጽሑፍ፣ለታሪክ፣ለሕግ፣ለእምነትና ለአምልኮት ወዘተ… በአጠቃላይ መልኩ እያዋልን ብንገለገልበትና የሀገረሰብን ሙዚቃና ዳንስንም በጨመረ ጊዜ ልዩ ማብራሪያ ብናክል ወይም ከመጀመሪያው አክለን ብንሠራበት ለአሠራራችን ውበት ይሰጠዋል፡፡የምንግባባበት ቃል ከኾነ ደግሞ የሙያ ቃልነቱ ተግባራዊ ኾነ ማለት ነው (ፈቃደ አዘዘ፣1973፣3) ፡፡

ትውፊትና ቅዱስ መጽሐፍ አንድም ኹለትም መኾናቸውን የሚያሳዩ ጥቅሶችም አሉ፡፡‹‹ወንድሞች ሆይ! በኹሉ ስለምታስቡኝና አሳልፌ እንደሰጠኋችኹ ወግን ፈጽማችኹ ስለያዛችኹ

አመሰግናችኋለኹ›› (1ቆሮ.11፡2፣23፣15፣1-3) ፡፡‹‹ስለዚኽም የመላእክትን ቃል ርሱም የእግዚአብሔር ቃል ከእኛ በተቀበላችኹ ጊዜ በእውነት እንዳለ በእናንተ በምታምኑ ደግሞ እንደሚሠራ እንደእግዚአብሔር ቃል እንጂ እንደሰው ቃል አድርጋችኹ ስላልተቀበላችኹት እኛ ደግሞ እግዚአብሔርን ሳናቋርጥ እናመሰግናለን›› (1ተሰ.2.13) ፡፡‹‹እንግዲኽ ወንድሞች ኾይ ጸንታችኹ ቁሙ በቃላችንም ቢኾን ወይም በመልእክታችን የተማራችኹትን ወግ ያዙ›› (2ተሰ.2.15) ፡፡

የቅዱስ ትውፊትን ቀኖናዎች ካሕሳይ ገብረ እግዚአብሔር ባህልና ክርስቲያናዊ ትውፊት በኢትዮጵያ በሚለው መጽሐፋቸው እንደገለጹት ቅዱስ ትውፊት የሚባሉት ቀኖናዎች መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት እንደኾኑ ይገልጻሉ፡፡እነርሱም፡-

ትውፊት ኹሉ ከሐዋርያት ታያይዞ የመጣና ሐዋርያዊና ቤተ ክርስቲያናዊ ምልክት ያለው መኾን አለበት፡፡

ከጥንት ጀምሮ በየትም ኹልጊዜ በዓለም ዐቀፋዊነት ቤተ ክርስቲያን የታመነ የተጠበቀና በተግባር የዋለ መኾን አለበት፡፡

ሕግ ባልተሠራበት ዘመን ይኖሩ የነበሩ አበው በትውፊት ባገኙት ዕውቀት እግዚአብሔርን ያገለግሉ ነበር (ሐውልተ ሰምዕ፣2004፣167) ፡፡

ትውፊት እንደኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ከጥንት ጀምሮ በቤተ ክርስቲያን በኩል ቃል በቃል /በቃለ-አፍ/ ሲያያዝ የመጣና ለትውልድ የተላለፈ እምነት፣ባህልና ልማድ ማለት ነው፡፡ክርስቲያናዊ ትውፊት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያት የሰጣቸው ከሐዋርያትም ጀምሮ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከትውልድ ወደትውልድ እየተቀባበለ የመጣው ኦርቶዶክስ እምነት ነው (ከፍያለው፣1986፣73) ፡፡

## ፫.፬ የኢትዮጵያ ጥንታዊ ሥዕል ትምህርት

የኢትዮጵያ የሥዕል ታሪክ መነሻ የራቀ ነው፤የሥዕልና ቅርጻቅርጽ ባህል መዲና ከኾነችው ከአፍሪካ ውስጥ ከቅርጽ ጋራ ያልተቋረጠ ዝምድና የሥዕልም ባህል ያላት ናት (ሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅነህ ፣373) ፡፡ “ካሕሳይ ገብረ እግዚአብሔር ባህልና ክርስቲያናዊ ትውፊት በኢትዮጵያ በሚለው መጽሐፋቸው እንደገለጹት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሥርዐተ ትምህርት የሚሰጠውን ትምህርት ኹለት ደረጃ ያለው እንደኾነ ያስረዳሉ፡፡

የመጀመሪያው ተማሪው ከፊደል ከፊደል ትምህርት ጎን ለጎን የሚማረው ሲኾን ኹለተኛው ደግሞ መጻሕፍት ለመጻፍ የሚያስችል የተሟላ ሥርዐትና ሕግ ያለው የሐረግንና የሥዕልን ጥበብ አጣምሮ የያዘ ነው፡፡እንደ ሥነ ጽሕፈት ኹሉ በጥንት

ጊዜ የሥዕልና የቅርጻ ቅርጽ ትምህርትም ይሰጥ ነበር፡፡የዚኽ ዐይነት ትምህርት ከፍላጎትና ከተሰጥዎ ጋራ የተያያዘ በመኾኑ ጥበቡን የሚማሩት ፍላጎትና ችሎታ ያላቸው የተወሰኑ ነበሩ፡፡እንደፊደሉና የትምህርት አሰጣጥ ሥርዐት ኹሉ የሥዕል አሣሣል ጥበብ ባህል የተለየና ራሱን የቻለ ‹‹ኢትዮጵያዊ ጥበብ ነው›› (ካህሳይ 2010፣68-69) ፡፡

ይኽም የሚያመለክተው ሥዕልን የሚከታተሉ ሰዎች ከጥንት ጊዜ ጀምሮ የተወሰኑ መኾናቸውንና ፍላጎት ያላቸው ሰዎች ጥቂት መኾኑን የሚያመለክት ነው፡፡ ሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅነህ ባህላዊውን አሣሣል እንዲህ በማለት ይገልጻሉ፡፡

በኢትዮጵያ ባህል ዋንኛው ሥራ መንፈሳዊ ሥዕሎች ስለኾኑ እነኝኽ ሥዕሎች እየተደጋገሙ በብዛት ከመሣላቸው የተነሣ የተወሰነ የማይለወጥ ባህላዊ ልማድና ምድቦች ወጥቶላቸዋል፡፡ከእነዚኽም ውስጥ ዋና ዋናዎቹ፡-
ጌታችንን ኢየሱስን የሰቀሉት አይሁድ፣አረማውያን ዲያብሎስ ሰይጣናት የሚባሉት በአንድ አቅጣጫ፣በአንድ መልክ፣በአንድ ዐይን ብቻ ይሣላሉ፤ቅዱሳን መላእክት ሌላም ሰው ቢኾን በሙሉ መልክ ከኹለት ዐይን ጋራ ይሣላሉ፡፡ለማንም አመልካች ኹሉ ባንድ ጎን አንድም አቅጣጫ ባንድ ዐይን የተሣለ ኹሉ የክፉ የኀጢያተኛም ምልክት ነው፡፡በሙሉ መልክና ከነኹለት ዐይኑ የተሣለ ግን ቅዱስ መኾኑን በማየት ባጭሩ ይረዳዋል፡፡
በሥነ ስቅለት ላይ ኹልጊዜ ጌታችን ራሱን ወደ ቀኝ እንዳዘነበለ ይሣላል፡፡
ምስለ ፍቁር ወልዳም ኹልጊዜ ጌታ ከግራ ወደ ቀኝ ኹኖ እመቤታችንም ራሷን ወደግራ አዘንብላ ትሣላለች፡፡

የጥንቱ የሥዕል ትምህርትን በተመለከተ ‹‹በኢትዮጵያ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ሥዕልን የሚሥሉና ቅዱሳት መጻሕፍትን የሚጽፉ የሃይማኖት ሰዎች ካህናት ነበሩ››ይላሉ ከፍያለው፡፡ ሥዕሎቹም ከብዙ ዓመታት በኋላ ዛሬ ስናያቸው በሰው እጅ የተሣሉ እንደማይመስሉና የቀለሙ አለመደብዘዝ ከምን ዐይነት ንጥረ ነገሮች እንደተዘጋጁ ለማወቅ እንደሚያስቸግር የፈጠራ ችሎታቸው ምን ያኽል የረቀቀና የጠለቀ መኾኑን እንደሚያመለክትና(ጎንደር) ደብረብርሃን ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ጣራ ላይ የተሣሉት ሥዕሎችና (ሳይንት) ተድባበ ማርያምን እንደምሳሌ ይገልጻሉ(ከፍያለው1986፣53) ፡፡መንፈሳዊ ሥዕሎችን የሚሥሉ የቀድሞ አባቶቻችን ከፍተኛ የኾነ ትምህርተ ክርስትና ነበራቸው ስለኾነም የሚሥሏቸው መንፈሳውያን ሥዕሎችም በምስጥር ከቲዎሎጂ ጋራ አይጋጩም ነበር(ከፍያለው1986፣54)፡፡

በጥንት ጊዜ የሠዓሊ ዋጋ ከፍ ያለ በኢትዮጵያ ማኅበረሰብ ውስጥ ምሁር በመኾኑ በሊቅነት ደረጃ የሚቈጠሩ ስለኾኑ አለቃ የሚል መጠሪያ ነበራቸው (ሀብተ ማርያም፣1962፣377)፡፡

ምንትዋብ በሚል ርእስ የቀረበው የሕይወት ተፈራ ልቦለድ መጽሐፍ ላይ የቀረበው ታሪክ እንደሚያሳየው የጥንት ሠዓልያን ጥቂት መኾናቸውን እና ሥዕልን ለመሣል በቂ የኾነን ዕውቀት ማዳበር፣ማለትም የቅዱሳንን ታሪክ፣የምስጢረ ሥላሴን፣የመላእክትን ታሪክ እና የሰማዕታትን ታሪክ ጠንቅቆ ማወቅ እንደሚያስፈልግ ይገልጻል፡፡

# ምዕራፍ አራት

## ፬.፩ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የቅዱሳት ሥዕላት አሣሣል

በዚኽ ምዕራፍ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ትውፊት መሠረት ሥዕላት በቀኖና የሚሣሉ በመኾናቸው የአሣሣል ሥርዐትን የሚቀርብበት ክፍል ነው። ይኽ ምዕራፍ የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ፣ የቅዱሳን፣የሥላሴ፣የሰማዕታት፣ የድንግል ማርያም፣የነቢያትና የሐዋርያትን የአሣሣል ትውፊቶች ቀርበውበታል፡፡ከዚኽ ምዕራፍ በተጨማሪም የቅዱሳት ሥዕላት ከሌሎች ዓለማዊ ሥዕሎች የሚለዩበትንና የአቀማመጥ ሥርዐታቸውን ያሳያል፡፡

## ፬.፪ ቅዱሳት ሥዕላት

ቅዱሳን ማለት የከበሩ የተለዩ ማለት ነው፡፡ሥዕላት ማለት ደግሞ ይኽ ቃል የብዙ ነገር ማመልከቻ ነው፡፡ሥዕል የማንኛውም ነገር አምሳያ ሲኾን በቀለም ቅብ የሚዘጋጅ ማለት ነው፡፡ቅዱሳን ሥዕላት የሚለው ደግሞ የከበሩ የተለዩ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ፣የእመቤታችን፣የቅድስት ድንግል ማርያም፣የቅዱሳን መላእክት የነቢያትና የሐዋርያት የጻድቃንና ሰማዕታት ሥዕላት ናቸው (ሚሊዮን፣1994፣88) ፡፡

## ፬.፫ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሥዕል አሣሣል

የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚኽች ምድር ላይ ለ33 ዓመት 3 ወር ከ10 ቀናት በእግር ተመላልሶ ባስተማረበት ጊዜ ያደረጋቸውን ተዓምራት የሚያሣዩ ዐበይት ተአምራት ነው (ኃይለማርያም 2007፣86) ሥዕላት እንዴት እንዴት እንደሚሣሉ ከዚኽ ቀጥሎ ይቀርባል፡፡ ኵርዐተ ርእሱ ሥዕል በመባል የሚጠራው ወደ ኢትዮጵያ የመጣው በዐፄ ዳዊት ዘመን በ14ኛውምእት እንደኾነ ይነገራል(ሥርግው፣1981፣89)፡፡የጌታችንን መስቀል፣የእመቤታችንን እና ኵርዐተ ርእሱን ሥዕል፣ የቅዱስ ሚካኤልን ሥዕል በክብር ተቀብለው በልብሰ መንግሥታቸው አጐናጽፈው አስቀመጡ (መጽሐፈ ጤፉት፣2006፣53) ፡፡

### ፬.፫.፩ ልደት

የልደት ሥዕል ሲሣል ሦስቱንም ነገሥታት እየመራ ቤተልሔም ያደረሳቸው ኮከብ እየታየ በሌሊት ዋሻ(በበረት) ጌታችን በሕፃን አካል በእመቤታችን ክንድ በከብቶች ግርግም ላይ ተኝቶ ይሣላል፡፡ቅዱስ ዮሴፍ አረጋዊ ተደርጎ ሲሣል፣ሰብአ ሰገል እጅ መንሻ አቅርበው ሲሰግዱ፤እረኞች (የገና ጨዋታ ሲጫወቱ ሊሣሉ ይችላል) ከመልአኩ የተረዱትን በማየታቸው ተደስተው በአድናቆት ሲያመሰግኑ፣የበረት እንስሳትም (አኽዮች እና በሬ) ትንፋሻቸውን


ሲገብሩ ይሣላል (ኃይለማርያም 2007፣87) ።‹‹በሬ ገዢውን፣አኽያም ጋጣውን ዐወቀ›› (ኢሳ.1፣1-3 ማቴ 2. ፡12፤ሉቃ 2፡15-20)




ሥዕል ፩ የክርስቶስ ልደት

## ፬.፫.፪ ሥነ ሥቅለት

በሥዕለ ስቅለት ላይ ኹልጊዜ ጌታችን ራሱን ወደቀኝ እንዳዘነበለ ይሣላል (ለቀ ሥልጣናት ሀብተማርያም፣375) ።



ሥዕል ፪ የክርስቶስ ስቅለት

## ፬.፫.፫ ትንሣኤ

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ሥዕል ሲሣል መቃብሩ እንደታተመ ባለቁልፍ ኾኖ የአይሁድ ጭፍሮችና ጠባቂዎች በዙሪያው ወድቀው፣ጌታችን በትረ መስቀል በእጁ ይዞ፣ ነጭ ልብስ ለብሶ፣ብርሃን ተጐናጽፎ፣ቅዱሳን መላእክት በቀኝ እና በግራ ኾነው ይሣላሉ።የትንሣኤ ሥዕል ሲሣል አዳምና ሔዋን መኖር አለባቸው ((ኃይለማርያም 2007፣89) ።አንዳንድ የምዕራባውያን ሥዕላት ላይ ጌታችን በተከፈተ መቃብር ሲወጣ፣ አንድም መላእክት ከፍተውለት ሲወጣ ይታያል።ይኽ ክሕደት ነው፤ምክንያቱም ጌታችን በተዘጋ መቃብር መግነዝ ክፈቱልኝ፤ሳይል ተነሥቷልና በመለኮታዊ ኃይልና ሥልጣን መነሣቱን ያሳያል (ቃለ/መ ሰኔ 20/2015) ።




ሥዕል ፫ የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ሥዕል

## ፬.፬ የቅድስት ሥላሴ አሣሣል

ሥላሴ ማለት ሦስትነት ወይም ሦስት፣አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ በስም፣በአካል፣በግብር ሦስት ሲኾኑ በባሕርይ፣በአምላክነት፣በፈቃድ፣በሥልጣንና በግዛት አንድ የኾኑ ማለት ነው (ሚሊዮን፣1994፣7) ።ቅድስት ሥላሴ ሲሣሉ ከመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ጋራ በማስተሳሰር መልእክትን ለማስተላለፍ በሚያመች መልኩ እንደሚሣል ሰይፈ ሚካኤል ፈለቀ ሥዕለ ሥላሴ በምስጥረ ሥላሴ በሚለው መጽሔት ላይ የሥላሴን አሣሣል ሥርዐት እንደሚከተለው ይገልጻል።

ቅድስት ሥላሴ ሲሣሉ በስም፣በአካል፣በግብር ሦስት መኾናቸውን፤በአገዛዝ፤ በሥልጣን አንድ መኾናቸው መገለጥ አለበት፡፡አንድነታቸውን ለማመልከት በኪሩቤል መንበር ላይ እንደተቀመጡ ያለቅደም ተከተል (ፊትና ኋላ/ ከላይ ወደ ታች ሳይኾኑ) አንድ ዐይነት አስተያየትና አቀማመጥ ተቀምጠው ልብሳቸው ወይም ቀሚሳቸው አንድ ላይ ሳይነጣጠል (ለየብቻው ሳይኾን) በአንድዓይነት ቀለም ይሣላል፡፡መንበር የሥልጣን፣የአገዛዝ፣የመንግሥት፣ምሳሌ ሲኾን በአንድ መንበር መቀመጣቸውም በሥልጣን፣በአገዛዝ አንድ መኾናቸውን ያመለክታል፡፡ተቀምጠው መሣላቸው በኹሉ ቦታ ያለ፣በኹሉ የነገሠ (ንጉሠ ነገሥት፣እግዚአ አጋዝእት) መኾኑን ለመግለጽ ነው፡፡ያለ ቅደም ተከተል መቀመጣቸው በቅድምና አንድ መኾናቸውን ያሳያል፡፡

የቅድስት ሥላሴ የአሣሣል ሥርዐት ቤተ ክርስቲያንኽን ዕወቅ በሚለው በማኅበረ ቅዱሳን በተዘጋጀው መጽሐፍ ላይ ደግሞ እንደሚከተለው ተገልጿል፡፡

ሦስትነታቸውን ለመግለጥ ዓለምን በግራ እጃቸው እንደያዙ በቀኝ እጃቸው ሲባርኩ (የጠቋሚ ጣት ወደ ላይ ቀጥ ከመኻል ጣት እስከ ትንሽ ጣት ያሉት ሦስቱ ጣቶች ታጥፈው) የሦስቱም ፊት ወደ አንድ አቅጣጫ የሚያይ ኾኖ አካላዊ ገጽታቸውም እኩል (የተመጣጠነ)፣የልብሳቸውም ከውስጥ እና ከላይ መጐናጸፊያቸው ቀይ ተደርጎ ይሣላል፡፡ሲሣሉም በአምሳለ አረጋዊ (ብሉየ መዋዕል በግዕዙ) መኾን አለበት፡፡ ይኽም ዘላለማዊነታቸውን፣ በኹሉ ቦታ መኖራቸውን፣ታጋሽነታቸውን ፈራጅነታቸውንና አስተዋይነታቸውን ለመግለጥ ነው፡፡የምድር ነገሥታት ያልፋሉ፡፡እርሱ ግን የተለየ፣የማያልፍ፣መነሻውም ፣መድረሻውም የማይታወቅ መኾኑን ለመግለጥ በአምሳለ አረጋዊ ይሣላሉ፡፡

ምንትዋብ በሚለው የሕይወት ተፈራ ልቦለድ ውስጥ እንደተገለጸው የሥላሴ አሣሣል ገፀ ባሕርዩ እንደሚያስረዳው ሥላሴ በሚሣሉበት ሰሌዳ አራት ማእዘን ይኾንና በአራቱም የማእዘኖች መገናኛ ላይ ሌሎች አራት እኩል ማእዘኖች ይሠመራሉ፤ስምንት ይኾናሉ፡፡የሥላሴ በስምንት ማእዘን መሣል የሚያመለክተው አንደኛ የስምንቱ የሰማይ መስኮቶች ምሳሌ መኾናቸው፣ኹለተኛ እኩል የዓለም ቅርጽ ይዘው በክብ ማእዘን ውስጥ መቀመጣቸው ሲኾን ሦስተኛ በተመሳሳይ መልክመሣላቸው ነው፡፡በስምንቱ መሥመሮች ውስጥ፣ የሰው፣የአንበሳ ፣የላምና የንስር ምስሎች ይሣላሉ፡፡የክቡ ትርጓሜ ዓለም በመዳፋቸው ላይ መኾኗ ያሳያል፡፡ክብ የዓለማችን ቅርጥ መኾኑንና

የዓለማችን ፈጣሪም መጀመሪያውም ፍጻሜውም የማይታወቅ የሕያው እግዚአብሔር ምስጢር ነው። በሥላሴ ሥዕል ራስ ላይ እግረ ፀሓይ ይሣላል።የብርሃን ክበብ ነው።ብርሃኑ መንፈስ ቅዱስ ነው።አካሉ ደግሞ ወልድ ነው።ሥላሴ አንድም፣ሦስትም ስለኾኑ በተመሳሳይ መንገድ ይሣላሉ።በተመሳሳይ መንገድ መሣላቸው ደግሞ የፍጹም አንድነታቸው ማሳያ ነው።ሥላሴ ሲሣሉ ከግራም፣ቀኝም፣ከላይም፣ከታችም እኩል መደረግ አለበት።



*ሥዕል ፬. የቅድስት ሥላሴ ሥዕል*

ከዚኽ በተጨማሪም በዙፋናቸው ዙርያ በአራቱ ማእዘናት አራቱ እንስሳት ባለ ስድስት ክንፍ ኾነው በገጸ አንበሳ እና ገጸ ላሕም፣በገጸ ሰብእ እና ገጸ ንስር በኹለት ክንፋቸው እጃቸውን ሸፍነው፣በኹለት ክንፋቸው እግሮቻቸውን ሸፍነው፣በኹለት ክንፋቸው ደግሞ ቀኝ እና ግራ ዘርግተው ይሣላሉ።ኻያ አራቱ ካህናትም ልብሰ ተክህኖ አውልቀው ወይም ለብሰው እጣን የሞላበት የወርቅ ማዕጠንት ይዘው እያጠኑ አንድም አክሊላቸውከራሳቸው አውርደው በዙፋኑ ፊት ሲሰግዱ መሣል አለበት።

## ፬.፳ ምስለ ፍቁር ወልዳ አሣሣል

ማርያም ሥያሜ በተለያዩ መጻሕፍት ትርጓሜ ተሰጥቶታል።የተወሰኑት ትርጓሜዎች የሚከተሉት ናቸው።ማርያም ማለት ጸጋ ወሀብት ማለት ነው።ለጊዜው ለእናትና አባቷ ጸጋ ኾና ተሰጥታለች፤ፍጻሜው ግን ለሰው ኹሉ ጸጋ ኾና ተሰጥታለች።ይላሉ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን

(ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜ፣45) ። (ዐምደ ሃይማኖት፣2010፣93) ። የማርያም ትርጓሜ ይኸ ብቻ አይደለም እነርሱም፡-

> እነሆ በዚኽ ዓለም ከሚመገቡት ኹሉ ምግብ አፍ የሚጥም፣ለልብ የሚመጥን ማር ነው።በገነትም በሕይወት የተዘጋጀ ለጻድቃን ለቅዱሳን ያም የሚባል ምግብ አላቸው።ኹለቱን በሕይወት ስናጋጥመው ማርያም የሚል እናገኛለን።ስለዚኽ ከዚኽ ኹሉ የበለጥሽ፣የከበርሽ ነሽ ሲሉ ማርያም ብለው አወጡላት።
>
> ማርያም ማለት መርሕ ለመንግሥተ ሰማያት ማለት ነው።ይኽስ እንዴት ነው ቢሉ፣እነኾ ዛሬ በዚኽ ዓለም ለዕውር መሪ በትር እንዲሰጡ ኹሉ ርኅም በፍቅሯ ፣በጣዕመ ፍቅሯ የሰውን ኹሉ ኃጢአት ክፋት፣ፍቃ፣ከልጅዋ አስታርቃ፣ከገሀነመ እሳት አውጥታ፣መንግሥተ ሰማያት የምታገባ ስለኾነ መንግሥተ ሰማይ መርታ የምታስገባ አሏት።
>
> አንድም ማርያም ማለት ተለአተ እግዚአብሔር ወሰብእ ማለት ነው።እንዴት ነው? ቢሉ መለኮት ከትብስእት፣ትብስእት ከመለኮት ጋራ ተዋሕዶ በእመቤታችን በእግዝእትነ ማርያም ማሕፀን ዐድሮ ነበርና ስለዚኽ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የምትላላክ አሏት።
>
> አንድም ማርያም ማለት ልዕልት ማለት ነው።አርያም ማለት ልዑል ማለት እንደኾነ።እመቤታችንንም መትሕተ ፈጣሪ፣መልዕልተ ፍጡራን ይላታልና።
>
> እንዲኹም በእብራይስጥ ማሪሃም ይሏታል።ማሪ ማለት እመቤት ማለት ነው።ሃም ማለት ብዙኃን ማለት ነው።ስለዚኽ ማሪሃም የብዙኃን እመቤት ማለት ነው።

‹‹ማ ››ማለት ማህደረ መለኮት ወይም የመለኮት ማደሪያ ‹‹ር››ማለት ርግብየ ይላታል ማለት ነው።‹‹ያ››ማለት ፍጥረት ኹሉ ወደአንቺ ይማጸናሉ ማለት ነው።‹‹ም››ማለት የምንማጸንብሽና ኃጢአታችንን የማናስተሰርይብሽ ማለት ነው (አበራሽ፣1988፣21) ።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቀለማት የየራሳቸው ትርጒም አላቸው።በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ከተከናወኑት በመጽሐፈ ጤፉት እንደተገለጸው የኢትዮጵያ ንጉሥ ሰይፈ አርዕድም እመቤታችንን ሥዕል በወርቅ ዕንቊ ያሥሉ ነበር። በምስለ ፍቁር ወልዳ አሣሣል የቀለም ትርጓሜዎች ኦርቶዶክሳዊ ቅዱሳት ሥዕላት በሚለው የኃይለማርያም መጽሐፍ ላይ የምስለ ፍቁር ወልዳ ሥዕልን አሣሣል እንደሚከተለው ተገልጿል።

እመቤታችን ከተወደደው ልጅዋ ጋራ ስትሣል በቀኝ በኩል ኾና ትሣላለች፡፡ይኽ ደግሞ መዝ 44፤9‹‹በወርቅ ልብስ ተሸፋፍና እና ተጐነጻጽፋ ንግሥቲቱ በቀኝ ትቆማለች››የሚለውን ቃል መሠረት በማድረግ የምስለ ፍቁር ወልዳ ሥዕል ላይ ዘወትር እመቤታችን በቀኝ ኾና የምትሣል መኾኗን ያመለክታል፡፡ጌታችን ወንጌልን በግራ እጁ እንደያዘ፣በቀኝ እጁ ሲባርክ፣በራሱ ላይ ደግሞ ዘውድ ሳይኖርበት መሣል አለበት፡፡ቅዱስ ሚካኤል በቀኝ፣ቅዱስ ገብርኤል በግራ በኩል ኾነው ይሣላሉ፡፡ የእመቤታችን ሥዕላት ሲሣሉ አንደኛ ተሸፍና መኾን አለበት፤ምክንያቱም ‹‹በወርቅ ልብስ ተሸፋፍና እና ተጐነጻጽፋ ንግሥቲቱ በቀኝኽ ትቆማለች፡፡››በማለት (መዝ 44:9) ላይ ይገልጸዋል፡፡በ1ኛ ቆሮ 11:6 መልእክቱ ላይ ሴቶች ጸጕራቸውን መሸፋፈን እንዳለባቸው ያስተምራሉ (ኃይለ ማርያም፣2007፣91) (ከፍ ያለው፣1986፣52) ፡፡

‹‹ምስለ ፍቁር ወልዳ ኹልጊዜ /ከውድ ልጅዋ ጋራ/በመባል የሚታወቀው የእመቤታችን ሥዕል ግራ ቀኝ ኹልጊዜ የመላእክት ሥዕል ዐብሮ ይኖራል) ›› (ክርስቲን ሻዮ፣1999፣143)

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሚሣሉ ሥዕሎች የሚዘጋጁት ቀኖናን ተከትለው በመኾኑ የሥዕሎቹ አሣሣል እና የቀለም አጠቃቀም የተለያዩ ምስጢራትን የያዙ ኾነው ይገኛሉ፡፡በሥዕል ላይ የሚቀርቡትን ቀለማት ትርጕም መምህር አንዱዓለም ነቅዐ ሕይወት በሚለው መጽሐፋቸው ላይ እንደሚከተለው ገልጸውታል፡፡

የእመቤታችን መጐናጸፊያ ዙሪያውን በወርቅማ ዘርፍ አጊጦ መታየቱ ምሳሌዋ የኾነችው ታቦተ ጽዮን ከማይነቅዝ ዕንጨት ተቀርጻ በውስጥ፣በአፍኣ በወርቅ እንደተለበጠች ያስገነዝባል፡፡ እመቤታችን በለበሰችው መጐናጸፊያ ላይ ወርቅማ የኾኑ ሦስት ብሩሃን ከዋክብት ይታያሉ፡፡እነዚኽም ሦስት ዋና ዋና ነገሮችን ትርጕሞች ይገልጻሉ፡፡አንደኛው እመቤታችን በሦስት ወገን ማለትም በሥጋዋ፣በነፍሷና በልቡናዋ ንጽሕት፣ቅድስት፣ክብርት፣ልዕልት መኾኗን ያስረዳሉ፡፡ኹለተኛው ትርጓሜ ደግሞ ድንግል ማርያም ለሰማያዊው ንጉሥ ዙፋንነት በመመረጧ ምክንያት‹‹ሰማይ ዳግሚት ዲበ ምድር፤በምድር ያለች ኹለተኛ ሰማይ›› መኾኗን ለመግለጥ ነው፡፡በሥዕላቱ ላይ ቅድስት ድንግል እመቤታችን ሰማያዊ መጐናጸፊያ ተጎናጽፋ መታየቷም ኹለተኛ ሰማይነቷን ያስገነዝበናል፡፡በሦስተኛ ደረጃ ሦስቱ ብሩሃን ከዋክብት እመቤታችን ድንግል ማርያም ለሦስቱ አካላት ማለትም ለአብ፣ለወልድና ለማንፈስ ቅዱስ ማደርያነት

አማናዊት ቤተ መቅደስ መኾንዋን ይገልጻሉ፡፡እመቤታችን የተቀዳጀችው ወርቅማ የብርሃን አክሊል ዘላለማዊ ንጽሕናዋንና ቅድስናዋን በተመስጦና በአንቃዕድዎ የተሞላ ሰማያዊ ሕይወቷን እና እውነተኛውን የጽድቅ ፀሐይ እየሱስ ክርቶስን ወልዳ እመ ብርሃን፣ምዕልተ ጸጋ፣ምዕልተ ምክር፣ምልዓተ ውዳሴ መኾኗን ይገልጻል፡፡ ሌላው ደግሞ በቅዱሳት ሥዕላቱ እንደምንመለከተው እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ሰማያዊ ልብስ ተጐናጽፋ መታየቷ የዚኽን ዓለም ከንቱ ነገር ከማሰብም ኾነ በገቢር ከማድረግ ፈጽማ የተለየች ‹‹ሰማይ ጻግሚት ዲበ ምድር››መኾኗን ለመግለጽ ነው፡፡ከእመቤታችን መጐናጸፊያ ሥር የሚታየው አረንጓዴ ልብስ በሞት ጥላ ሥር ለነበረው ዓለም ፍጹም የአንድነትና የነጻነት ተስፋ መኾኗን ያስረዳል፡፡ስለኾነም አረንጓዴ ቀለም መታደስና የዐዲስ ሕይወት ቀለም በመኾኑ ሊቁ ‹‹ወብኪ ተሐደሰ ቀዳሜ ኲሉ ፍጥረት፤አንቲ ውእቱ ተስፋሁ ለአዳም አመ ይሰደድ እምገነት፤የሰው ዘር ኹሉ መጀመሪያ የኾነ አዳም የታደሰብሽ አንቺ ነሽ፤ከገነት በተሰደደ ጊዜ ከልጅ ልጅኽ ተወልጄ አድንኻለኹ ያለው የአዳም ተስፋ ድኅነት አንቺ ነሽ››ብሎ መስክሯል(ዘፍ.3፣15፤ገላ.4፤4)፡፡ እመቤታችን ከመጐናጸፊያዋ ከታች ቀይ መልበሷ ውስጣዊ መንፈሳዊ ውበቷን ይገልጻል፡፡ይኸውም ምስጢሩ መሠረተ ሕይወት ድንግል ማርያም በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ፈጽማ የከበረች መኾኗን በግልጥ የሚያሳይ ነው፡፡ከዚኽም ጋራ በመልዕተ መስቀል ላይ እውነተኛ መሥዋዕት ኾኖ በወርቀ ደሙ ፈሳሽነት ዓለምን ከሞት ርግማን የሚዋጀውንና በማሕየዊት ሞቱ የሚያድነውን መሲሕን የወለደች የበረከት እናት መኾኗን ያጠይቃል፡፡



*ሥዕል ፳. ምስለ ፍቁር ወልዳ*

## ፬.፮ ኪዳነ ምሕረት አሣሣል

የኪዳነ ምሕረት ሥዕል የሚያመለክተው ክርስቶስ ለድንግል ማርያም ቃል ኪዳን ሲገባላት የሚያሳይ ምስል ነው፡፡የኪዳነ ምሕረት ሥዕል ሲሣል ብቻዋን መሣል የለበትም፤ኪዳነ ምሕረት ቃል ኪዳን ስትቀበል ታሪኳ ላይ እንደተገለጸው እልፍ አእላፋት መላእክት በሙሉ ተሰብስበው ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወርዶ በጎልጎታ እጆቿን ይዞ ቃል ኪዳን ገብቶላታል ስትሣል የሚያሳየውን ታሪክ መሠረት ማድረግ ያስፈልጋል (ኃይለማርያም፣ 20/2015) ፡፡ አብዛኛው ምእመን እጅ በዚኽ ሰዓት የሚገኙት ኹለት ሥዕሎች ናቸው፡፡ ይኹን እንጂ በየመደብሩና በየአብያተ ክርስቲያናቱ የምናገኛቸው የኪዳነ ምሕረት ምስል እጆቿን ዘርግታ ብቻዋን ኾና የተሣለችውን ነው፡፡ይኽም ምስል የኪዳነ ምሕረት ሳይኾን ሥዕለ ንግሣ እና ዘይት አፍላቂዋ ማርያም ወይም የመገለጧ ማርያም ምትባለዋን ነው፡፡



*ሥዕል ፲ የኪዳነ ምሕረት ሥዕል*

## ፬.፲ የቅዱሳን መላእክት አሣሣል

መላእክት ማለት የቃሉ ትርጒም የእግዚአብሔር መልእክተኞች፣ተላላኪዎች፣አለቆች ማለት ነው(ሚሊዮን፣1994፣38) ፡፡መላእክት ተፈጥሯቸው ከነፋስና ከእሳት ነው፡፡ይኽ ማለት ፍጥረታቸውን፣ርቀታቸውን እና ኀያልነታቸውን ለመግለጽ እንዲኽ አለ እንጂ ተፈጥሯቸው እመነበ አልቦ ነው፡፡መላእክት ግን ረቂቃን ስለኾኑ በሰው አኳኃን ሊፈጠሩና ያለፈቃዳቸው ሊታዩ አይችሉም፡፡ለምን ከነፋስ ከእሳት ተጠፈሩ ተባለ ሲባል ነፋስ ፈጣን ነው፡፡መላእክትም በረቂቅነታቸው ከአምላክ ወደ ሰው ምሕረትን ቸርነትን በረከትን ለማምጣት ፈጣኖች ስለኾኑ ነው፡፡እሳትም ብሩህ ነው፡፡መላእክትም ብሩሃን ናቸው፡፡ (ሚሊዮን፣1994፣38) ፤ (ሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም፣83) ፡፡

የመላእክትን አሣሣል ለማወቅ በመጽሐፍ ቅዱስ የቀረቡትን ትውፊቶች በደንብ ማስተዋልና መመርመር አስፈላጊ ነው፡፡መላእክት በሚከተለው መንገድ እንደሚሣሉ ኃይለ ማርያም እና ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ ይገልጻል፡፡

> መላእክት ሲሣሉ መስቀልና ሰይፍ ይዘው ይሣላሉ፡፡ለምን?ቢሉ መስቀል ለምሕረት(አሳ 6፣6-7)፤ሠይፍ ደግሞ ኀጢአት በሚሠሩ ላይ ለመቅሠፍት በሚገለጹበት ጊዜ የሚይዙት ነው (አሳ 37፣36፤ዘኁ22፡31)፡፡ሲሣሉ አደግድገው መኾን አለበት፤ምክንያቱም ለአገልግሎት የሚፋጠኑ መኾናቸውን ያሳያል፡፡ በአለባበሳቸው ደግሞ ልብሰ ተክኅኖ ለብሰው ይሣላሉ፤ለምን?ቢሉ የምእመናንን

ጸሎት በማዕጠንታቸው እንደሚየሳርጉ፣እንደሚባርኩም ሥልጣናቸውን የሚያመለክት ነውና፡፡መስቀል ይዘው ይሣላሉ፡፡መስቀል ለምሕረት የሚለኩ መኾናቸውን ይጠይቃል፡፡አበባ ይዘው ይሣላሉ፡፡አበባ የሚወክለው የገነት መዓዛና የገነት አበቦችን ይጠይቃል፡፡ከዚኽ በተጨማሪ አበባ የሚሰጠው ቅዱስ ትርጕምም ሊኖረው ይችላል፡፡ለምሳሌ የምስለ ፍቁር ወልዳ ሥዕል ላይ ቅዱስ ሚካኤልና ቅዱስ ገብርኤል አበባ ይዘው ይሣላሉ፡፡በዚኽ ወቅት ቅዱስ ሚካኤል የሚይዘው አበባ ምሳሌነቱ የእመቤታችን ቅድስና የሚያሳየውን የሱፍ አበባ፤አንድም ከእሴይ ስር የወጣሽ መዓዛሽ ያማረ አበባ እንዲል ማር ቅዱስ ኤፍሬም ይኽንን ለማመልከት ቅዱስ ሚካኤል አበባ ይዞ ሊሣል ይችላል፡፡‹‹በዙፋኑ ሌላ መልአክም መጣ፡…ለቅዱሳን ኹሉ ጸሎት እንዲያሳርገው ብዙ ዕጣን ተሰጠው፡፡የዕጣኑ ጢስም ከቅዱሳን ጸሎት ጋራ ከመልአኩ እጅ ወደ እግዚአብሔር ፊት ዐረገ››(ራእይ 8፡3ዘፍ፡48፡16፡መሳ13፡20) ቅዱስ ሚካኤል ሲሣል በዙፋኑ ላይ ተቀምጦ (ይኽም ሊቀ መላእክትነቱን ያሳያል፣)ወይም ቆሞ፣በእጁ ሰይፍ እና በትረ መስቀል ይዞ ዲያብሎስን በገሃነመ እሳት ሲቀጣው ሰራዊተ መላእክት አጅበውት ይሣላል፡፡ሕዝበ እስራኤልን እየመራ ከግብጽ ባርነት እንዳወጣ እና አፎምያንም ከዲያብሎስ እጅ ሲያድናት….ወዘተ እንዲያሳይ ተደርጎ ይሣላል፡፡



ሥዕል ፲. ቅዱስ ሚካኤል

## ፬.፰ የቅዱሳን ነቢያት አሣሣል

ነቢያት ቀድሞ ከሔኖክ ኋላም ከሙሴ ዠምሮ እስከ ጌታችን የነበሩ ትንቢተኞች፣ትንቢት ተናጋሪዎችና ደጋጎች ሰዎች ኀላፍያትንና መጻእያትን የሚያውቁ በሕዝብ አነጋገር ነቢያት ይባላሉ (ደስታ ተክለ ወልድ፣1962 334፣) ።ቅዱሳን ነቢያት በእግዚአብሔር ፈቃድ እና ትእዛዝ ስለጌታችን፣ስለእመቤታችን፣ስለቤተክርስቲያን ወዘተ ትንቢት የሚናገሩ ቅዱሳን ናቸው።ቅዱሳን ነቢያት በእግዚአብሔር ፈቃድና ትእዛዝ ስለጌታችን፣ስለእመቤታችን፣ስለቤተ ክርስቲያን ስለኀልፈተ ዓለምና ስለሌሎችም ጉዳዮች ትንቢት የተናገሩ ቅዱሳን ናቸው (ስምዐ ጽድቅ ከነሐሴ ፩-፲፫ ፳፻፺ዓ፣ም) ።የሚሣሉትም በተሰጣቸው ጸጋ ከፈጸሟቸው ተጋድሎ ወይም ተአምር ጋራ ነው።

ሙሴ፡-እስራኤልን ሲመራ፣ሲከፍል፣በሲና ዐሥርቱ ትእዛዛት የተጻፉበትን ጽላት ከእግዚአብሔር ጋራ ሲቀበል፣ ኤልያስ፡-በእሳት ሠረገላ ሲያርግ፣ኢሳይያስ፡-በመጋዝ ሲተረተር፡እጁን ወደ ምስለ ፍቁር ወልዳ ሥዕል እያመለከተ ድንግል በድንግልና ትፀንሳለች ያልኳት ድንግል ርሷ ናት ሲል ነቢዩ ሕዝቅኤል፡- ስለ ድንግል ማርያም ድንቅ በሆነ ታላቅ ቁልፍ የተዘጋች ደጅ በምሥራቅ አየሁ ሲል ዳንኤል፡-ለአናብስት ሲጣልና መልአኩ ከአናብስቱ አፍ ሲያድነው ተደርገው ይሣላሉ (ኃይለ ማርያም፣2007፣102) ።




ሥዕል ፰ የሕዝቅኤል ሥዕል

## ፬.፱ ቅዱሳን ሐዋርያት

ሐዋርያት ማለት በደስታ ተክለወልድ መዝገበ ቃል እንደተገለጸው ብዙዎች መንገደኞች፣መንገድ ዐላፊዎች፣የወንጌል መልእክተኞች፣ሰባኪዎች የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት፣አስቀድሞ ዓሣ አሥጋሪ-ልብደ-ሠሪ በቅሎ ገሪ የነበሩ አርድእት፣፲፪ ሐዋርያት እንዲሉ (ደስታ ተክለወልድ) ፡፡

ቅዱሳን ሐዋርያት የሚሣሉት ጌታችን ሲያስተምራቸው፣በምስጢረ ቍርባን በተፈጸመበት በጸሎተ ኀሙስ፣ከትንሣኤ በኋላ ጌታችን ሲያርግ፣በበዓለ ኀምሳ እመቤታችንን መኻል አድርገው ሲጸልዩ፣ጸጋ መንፈስ ቅዱስ በእሳት አምሳል ሲወርድ፣በተናጠል ካደረጓቸው ተአምራት እና ከተቀበሉት ሰማዕትነት ጋራ ኾነው ይሣላሉ፤በእጃቸው ወንጌል እንደያዙ ኾነው ይሣላሉ፡፡ለምሳሌ ቅዱስ ጴጥሮስ ቁልቁል ሲሰቀል፣ቅዱስ ዮሐንስ በፍጥሞ ደሴት ወንጌልን እና ራእዩን ሲጽፍ፣መልአኩ በእንቁላል ቅርፊት ውሓ ከውቅያኖስ ሲቀዳ ይሣላል፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ አንገቱን ሲሰየፍ ይሣላል፡፡ሌሎቹም ሐዋርያት እንዲኹ ይሣላሉ (ኃይለማርያም፣2007፣102) (ስምዐ ጽድቅ ነሐሴ ፩-፲፰ ፳፻፯ዓ.ም) ፡፡




ሥዕል ፱. የቅዱስ ማርቆስ ሥዕል

## ፬.፲ ቅዱሳን ሰማዕታት

ሰማዕት የሚለው ስም ‹‹ሰምዐ›› ሰማ፣አደመጠ፣አስተዋለ፣ ተቀበለ፣መሰከረ፣ምስክር ኾነ ያየውን የሰማውን ተናገረ፣ዐየኹ ሰማኹ አለ ከሚለው ግስ የወጣ ቃል ነው፡፡ሰማዕት ማለት ምስክሮች ሰማዕቶች፣ሃይማኖታቸውን መስክረው በሰማዕትነት የሞቱና የሚሞቱ ማለት ነው፡፡ሔኖክ ‹‹በምድር ላይ የሚፈሰውን ደምና በምድር ላይ የሚደረገውን ግፍ ዐዩ››እንዳለው (ሔኖ 2፣28) ሰማዕተ ሀሰት የዲያብሎስ ወገኖች ሲኾኑ ሰማዕተ ሐሰት ጽድቅ የእግዚአብሔር ወገኖች

ናቸው።ሰማዕታት ሃይማኖታቸውን ላለመካድ በሰይፍ፣በጦር፣በእሳት፣በመሳሰለው ስለሚሞቱና ለመንግሥተ እግዚአብሔር ደማቸውን ስለሚያፈሱ አሸናፊዎች ናቸው፤‹‹ስለዚኽም ሰማዕታት መዋዕያን››ይባላሉ (የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ ፳፻፣፪፻፶፯) ።

እስከ ደም ጠብታ ለጌታችን የመሰከሩ ሰማዕታት ገድላቸውን በመሠረት በማድረግ ይሣላሉ፤አብዛኛውን በፈረስ ላይ ተደርገው ይሣላሉ (ዮሐ ራእይ 19፡11-19) ።እመቤታችን ድንግል ማርያም በደብረ ምጥማቅ ለ፩ምስት ቀናት በምትገለጽበት ወቅት ሰማዕታት በፈረስ እንደሚገለጹ ተአምረ ማርያም እንዲኽ በማለት ይገልጸዋል።‹‹የምትገለጸውም ብቻዋን አይደለም፤ክንፍ ያላቸው መላእክት ዐብረው ይገለጻሉ እንጂ፣በፈረስ የተቀመጡ መንፈሳውያን የሚኾኑ ክርስቲያን ሰማዕታት ይመጣሉ፤መጥተውም ከፈረሳቸው ወርደው ማርያም ለሚሏት ከእግሯ በታች ወድቀው ይሰግዳሉ››(ተአምረ ማርያም፣60-61)።

በመከራቸው ጊዜ ሰማዕትነት በሚቀበሉበትም ጊዜ ፊታቸው ሲሣል የጭንቀት ስሜት ያለበት ኾኖ አይሣልም።ነገር ግን የተረጋጋ ሰላም እና ደስታ የተሞላበት ፊት ይሣልባቸዋል። ይኽም የሚያሳየው በክርስቶስ የሚመጣባቸውን መከራ ደስ ብሏቸው እንደተቀበሉ ነው።‹‹ሐዋርያትንም ጠርተው ገረፏቸው፤እንግዲኽ ወዲኽ በኢየሱስ ስም እንዳያስተምሩ ገሥጸው ተውዋቸው።እነርሱም ከሸንጎው ፊት ደስ እያላቸው ወጡ፤ስለስሙ መከራ የቀበሉ ዘንድ መንፈስ ቅዱስ አድሏአቸዋልና (ሐዋ 5፡40-41››ይላል) ።ሰማዕታት ለጌታችን ለክርስቶስ ፍቅር ሲሉ ስለአዳኝነቱ፣ሲመሰክሩ አንገታቸውን በሰይፍ ተቀልቶ ወይ በእሳት እቶን ውስጥ ተጥለው ስለሚሞቱ ያፈሰሱትን ደም ለመዘከር በቀይ ቀለም ይሣላሉ (ሕይወት 2012፣150) ።

ቅዱስ ጊዮርጊስ ፡-በፈረስ ተቀምጦ ደራጎንን በጦር ወግቶ ሲገድለው፣ቤሩታዊትም በዛፍ ላይ ኾና ይሣላል። ነገር ግን ወታደራዊው ልብስ እና በግማሽ ፊት ተደርጎ አይሣልም።

ቅዱስ እስጢፋኖስ፡-በድንጋይ ሲወገር እና ሥሉስ ቅዱስም በዙፋናቸው እንዳሉ ሲመለከት ይሣላል።

ቅዱስ መርቆሪዎስ፡-ቅዱስ ፋሲለደስ፣ቅዱስ ሚናስ ወዘተ በፈረስ (ገድሎቻቸው ላይ ላይ ያለውን የፈረስ ቀለም መሠረት በማድረግ) ላይ ተቀምጠው ይሣላሉ (ኃይለማርያም፣2007፣104) ።



*ሥዕል ፲. የሰማዕቱ ቅዱስ ጊዮርጊስ*

## ፬. ፲፩ ቅዱሳን ጻድቃን

ጻድቃን ማለት ጻድቅ ከሚለው ከግዕዝ ቃል የተወሰደ ሲኾን ትርጕሙ የእግዚአብሔርን ሕግና ትእዛዝ በመጠበቅና በመፈጸም በሕግ መኖር፣መመራት በአጠቃላይ ትክክለኛነትና እውነተኛነት ማለት ነው (ሚሊዮን፣1994፣62) ፡፡

ቅዱሳን ጻድቃን በአብዛኛው ከገድላቸው በመነሣት በተለያየ አገላለጽ ሲጸልዩ ወይም መስቀል ወይም መጽሐፍ ይዘው የደረሱበትን ደረጃ ለማጠየቅ ወይም ክንፍ አውጥተው ወይም ሲያርጉ ይሣላሉ፡፡ጻድቃን ይኽን ዓለም ንቀው በጽድቅ ኖረው ያለፉ አባቶቻችን ፈዘዝ ባለ ቀለም ይሣላሉ (ሕይወት 2012፣150) ፡፡

> አቡነ ተክለሃይማኖት፡- በደብረ ዐሰቦ በአንድ እግራቸው ሲጸልዩ፣ ስድስት ክንፋቸውን ዘርግተው በግራና በቀኝ ጦር ሰክተው የተቆረጠውን እግራቸውን ከዚያው ተቀምጦ ይሣላ፤ልብሰ ተክህኖ አይለብሱም፤ልብሰተክህኖው ምክንያቱም ለቤተ መቅደስ አገልግሎት ብቻ ስለሚለበስ ነው፡፡
>
> አቡነ ገበረ መንፈስ ቅዱስ፡-በዝቋላ ባሕር ቆመው ሲጸልዩ፣በሰውነታቸው ጸጕር መላ አካላቸውን ሸፍኖ በወገባቸው ሰንሰለት አስረው፣በእጃቸው1 መስቀልና መቊጠሪያ ይዘው፣ በግራ በቀኝ አንበሶችና ነብሮች ኾነው በቁራ ተመስሎ የመጣው ሰይጣን ዐይናቸውን ሊያወጣ ሲል ይሣላሉ፡፡

አቡነ ሳሙኤል ዘዋልድባ፡-በአንበሳ ላይ ኾነው መጻሕፍቶቻቸውንም በአንበሶቹ ላይ ጭነው ለተልዕኮ ሲፋጠኑ ይሣላል፡፡

ቅዱስ ያሬድ፡- በዎፎች ተመስለው የመጡ ሦስቱ መላእክት በዛፍ ላይ ኾነው፣ርሱም መቋሚያና ጽናጽል በእጁ ይዞ፣ጥንግ ድርብ ለብሶ፣ሲዘምር ይሣላል፡፡ሌሎችም ቅዱሳን ጻድቃን ከመጽሐፍ ቅዱስ ወይም ከገድላቸው በመነሣት ይሣላሉ (ኃይለማርያም፣2007፣105) ፡፡



ሥዕል ፲ወ፩. ጻድቁ ተክለ ሃይማኖት

## ፬. ፲፪ የቅዱሳን እና የርኩሳን ሥዕላት አሣሣል

በኢትዮጵያ ኦርቶዶአስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አሣሣል ቅዱሳት ሥዕላት እና ርኩሳን ሥዕላት የራሳቸው የኾነ የአሣሣል ዘይቤ አላቸው፡፡ቅዱሳት ሥዕላት ሲሣሉ ፊታቸው ሰፊና ክብ የፍጹምነት ምሳሌ ነው፡፡መላ ሕይወታቸውን ለጸሎት እና ለተመስጦ ማዋላቸውን ያሳያል፡፡ ዐይናቸው ጎላ ተድርጎ ይሣላል፡፡ጨለማውን ከብርሃኑ ለይተው በተቀደሰ ጎዳና በፍጹም አስተዋይ ልቡና የተያዙ መኾናቸውን ለማሳየትና የተመልካቹን በምእመን ልብ ለመሳብ፣ ለመመሰጥ፣የመደመጥን ስሜትና ፈሪሀ እግዚአብሔርን ለመፍጠር ይጠቅማል፡፡ ዐዓይኖቻቸውም ወደ አንድ አቅጣጫ ብቻ ተደርጎው ይሣላሉ፡፡አንዲት መንግሥተ ሰማያትን በዐይነ ኅሊና በመመልከት ለክብር እንደበቁ ለማመልከት በኦርቶዶክስ ሃይማኖት በልባቸው ለማሳየት ይጠቅማል፡፡የሥዕሉ ባለቤት ራስ ዙርያ ጸዳለ ብርሃን/አክሊለ ብርሃን/በክብ ቅርጽ ይሣላል፡፡ከቤተ ክርስቲያን የቅድስና ማዕረግ

እንደተሰጣቸው ያመለክታል፡፡ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ መላእክት ሲሣሉ ጸዳለ ብርሃኑ ላይደረግ ይችላል፡፡ርኩሳት ሥዕላት አጋንንትና መናፍቃን ሲሣሉ አካላቸው ትንሽ ተደርጎ ዐይናቸው ደም እንዲመስል ተደርጎ ግብራቸው ለማመልከት አስፈሪና መልክ ጥፉ ተደርጎ ይሣላል(ቃለ መጠይቅ፣ሰኔ/20/2015)፡፡

## ፬. ፲፫ የቅዱሳት ሥዕላት አቀማመጥ

ቅዱሳት ሥዕላት ተአምር የሚፈጸምባቸው ናቸው፡፡ሥዕል በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የአቀማመጥ ሥርዐት አለው፤አቀማመጡም አቅጣጫዎችን መሠረት ያደረገ ነው፡፡ሥዕሎቹም የሚሣሉት የአቀማመጡን ሥርዐት ተከትሎ ነው፡፡አቀማመጥ ቅደም ተከተሉም እንደሚከተለው ተገልጿል፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በቅኔ ማሕሌት፣በመቅደስና በቅድስት የተከፈለ ሲኾን፤ኹልጊዜ ሥዕሎቹ የሚሣሉት በመቅደሱ አራት ገጾች ላይ ነው፡፡የማይለወጠውን ባህላዊ አቀማመጣቸውን ቀጥሎ የቀረበው መግለጫ ያመለክታል፡፡

፩. በምሥራቅ ገጽ ነገደ ኢየሱስ ተብሎ ጌታችን የጌታችን የተአምራት ታሪኮች፣የሐዋርያት ተጋድሎ፤ የኤፍሬም እመቤት የተባለችው ይሣላሉ፡፡

፪. በምዕራብ ገጽ ነገረ ስቅለትና የልደት የጥምቀት፣ሕማማተ መስቀል ፣ትንሣኤ፣ ምስለ ፍቁር ወልዳ፣የቅዱስ ጎዮርጊስ ሥዕሎች ይሣላሉ፡፡

፫. በሰሜን ገጽ፣ነገደ ሰማዕታት ተብሎ የሰማዕታት ታሪክና እሞሙ ለሰማዕታት የተባለችው የእመቤታችን ሥዕሎች ይሣላሉ፡፡

፬. በደቡብ ገጽ ነገደ ማርያም ተብሎ ከልደቷ እስከ ትንሣኤዋ ድረስ ያለው የእመቤታችን ታሪክና የምጽአት ታሪክ ይሣላሉ፡፡

፭. ከምኂሕዋሩ በላይ በምሥራቅ ዕርገት፣በምዕራብ ቅድስት ሥላሴ በሰሜን ደብረ ታቦር፣በደቡብ ደብረ ምጥማቅ ይሣላሉ፡፡

፮. በመቅደስ በሮች በምዕራብ የመቅደሱ መዝጊያዎች ላይ ቅዱስ ሚካኤል ፈርያንን ከነሰራዊቱ እንዳሰጠመና ቅዱስ ሩፋኤል ዓሣ አንበሪውን እንደወጋ ተደርገው ይሣላሉ፡፡

፯. በአራቱም ገጾች ደግሞ ልዩ ልዩ የኾነ የመላእክትን ቅድስና የሚገልጡ ሥዕሎችና ሐረግ ይጣላሉ፡፡

፰.የቤተ ክርስቲያንን ሥዕሎች የሚያሥሉ ምእመናን ተማሕፀንኩ እያሉ በሚዘክሩት ሥዕል ሥር እንደወደቁ ይሣላሉ፡፡

በማንኛውም ቤተ ክርስቲያን ቢኾን ሥዕል የተሣለ ከኾነ የሚገኘው ይኸው ዐይነት አቀማመጥ ነው (ሀብተማርያም፣1962፣377) (ክርስቲንቻዮት፣1999፣143) (ኃይለማርያም፣2007፣107-110) ፡፡

የቅዱሳት ሥዕላት በመኖሪያ ቤት ውስጥ የአቀማመጥ ሥርዐት አለው፡፡ለጸሎት ተብሎ የተዘጋጀ የጸሎት ቤት በመሥራት በተገቢው ኹኔታ መቀመጥ አለባቸው፡፡ይኽን ማድረግ ካልተቻለ ደግሞ በቤት ውስጥ ለቅዱሳት ሥዕላት ለብቻ የተለየ ስፍራ በማዘጋጀት በመጋረጃ በመሸፈን ሻማ በማብራት በክብር ማስቀመጥ ያስፈልጋል፡፡ይኽም ትምህርተ ሃይማኖትን ዘወትር በማስታወስ ሥርዐትን ጠብቀው መቀመጥ እንዳለባቸው የሚያመለክት ነገር ነው፡፡ የአቀማመጣቸው ቅደም ተከተልም በመጀመሪያ የፈጣሬ ዓለማት የቅድስት ሥላሴ፣በኹለተኛ ደረጃ ምስለፍቁር ወልዳ፣ በሦስተኛ ደረጃ የጌታችን ሥነ ስቅለት፣በአራተኛ የቅዱሳን መላእክት፣በዐምስተኛ ቅዱሳን ነቢያት በስድስተኛ የቅዱሳን ሐዋርያት፣በሰባተኛ ቅዱሳን ሰማዕታት፣በመቀጠልም የቅዱሳን ጻድቃን እያደረግን ማስቀመጥ ይኖርብናል(ቃለ መጠይቅ ኃይለማርያም ሠኔ 20/015)፡፡

የቅዱሳት ሥዕላት አቀማመጥ ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ መኾን አለበት፡፡ለዚኽ ጥናት ምልከታ በሚደረግበት ወቅት በማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ፀሓይና በዝናብ የወየቡ ቅዱሳት ሥዕላት ተመልክቻለኹ፡፡ በየጎዳናው ለልመና፣ለሽያጭ፣በጭፈራ ቤት የሚያስቀምጡበት ቦታ ቆሻሻ ቦታ ላይ፣ለአቧራ በተጋለጠ መልኩ እየተቀመጡ ክብር እያጡ ነው፡፡ ይኽም ጉዳይ በቸልተኝነት እየተደረገ ይገኛል፡፡ይኽም ከቅዱሳት ሥዕላት የሚገኘውን ጥቅም የሚያሳጣ ነው፡፡በመኾኑም ሥዕሎችን መንከባከብ ያስፈልጋል፡፡

## ፩. ፲፩ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሥዕል ትምህርት አሰጣጥ ኹኔታ አኹን ባለንበት ዘመን

የጥንቷ ኢትዮጵያ የሥዕል ትምህርት የሚማሩት ካህናት እንደነበሩና በየገዳማቱ የሥዕል ሥራዎች እንደነበሩ የታሪክ መዛግብት ማየት ይቻላል፡፡ከበደ ሚካኤል የኢትዮጵያ የጥንት ሥዕሎች በሚለው መጽሐፋቸው ጥንታዊ ሥራዎች በክርስቲያን ሃይማኖት ላይ የተመሠረቱ መኾናቸውን የኢትዮጵያን ሥዕሎች በውጭ ሀገር እንዲታወቁ ለማድረግ አቤለሩዋ የተባለው አጥኚ ምርምር እንዳደረገ ይገልጻሉ፡፡

አኹን ባለንበት ዘመን ሲታይ የሥዕል ትምህርት ሙሉ ሙሉ ጠፍቷል ባይባልም አንስተኛ የኾነ እንቅስቃሴ አለ፡፡ይኽውም በማኅበረ ቅዱሳን ማኅበር የሥዕል ትምህርት ክፍል እያስተማረ ይገኛል፡፡ሐመረ ብርሃን የሚባለው ተቋም ውስጥም የቁም ጽሕፈት ትውፊትን መሠረት ያደረገ ሥዕል በተወሰነ መልኩ እንቅስቃሴ እያደረገ ነው፡፡በሰንበት ትምህርት ቤት ደረጃም እንቅስቃሴ

እየተደረገ ነው፡፡በገርጂ ማርያምና እግዚአብሔር ምስሌነ ደብረ ገሊላ ብዙ ሥራ እየተሠሩ ይገኛሉ፡፡በመንፈሳዊያት ዩኒቨርስቲዎች ውስጥ ግን ሥዕል ራሱን ችሎ እየተሰጠ አይደለም፡፡ አንድ በጣም ዐጭር ትምህርት ከመንፈሳዊው ትምህርት ጋራ ይሰጣል፡፡ኾኖም የሥዕል ትምህርቱ አለ ለማለት የሚያስችል አይደለም፡፡በተጨማሪም በየዐውደ ምሕረቱ ላይ ቅዱሳት ሥዕላትን በተመለከተ የተሰበኩ ትምህርቶች የሉም፤ሰባኪዎችም አያስተምሩም፡፡በመጽሐፍ ደረጃ የተዘጋጁ መጻሕፍት የሉም፡፡በበይነ መረብ(ኢንተርኔት) ላይም በቅዱሳት ሥዕላት ዙሪያ የተዘጋጁ መጻሕፍት የሉም(ቃለ መጠይቅ ሠኔ 20/2015)፡፡

## ፬. ፲፮ ሥዕል ለመሣል የሚያስፈልጉ ቅድመ ኹኔታዎች

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥዕልን ለመሣል የሚያስፈልጉ ዋና ዋና ቅድመ ኹኔታዎች መሟላት አለባቸው፡፡የመጀመሪያው የእግዚአብሔርን ፈቃድ በጸሎት መጠየቅ ያስፈልጋል፡፡ከዚያ በኋላ ምን ዐይነት ሠዓሊ እንደኾነ መጠየቅ ያስፈልጋል፡፡ሠዓሊው ጀማሪ ከኾነ ተገቢ የኾነ ትምህርት መማር ተገቢ ነው፡፡የሚሰጠውም ትምህርት ኹለት ዐይነት ሲኾን የመጀመሪያው ትምህርት መንፈሳዊ ትምህርት ነው፡፡የሚሣለው ታሪክ ከቅዱሳን ሕይወት ጋራ የተያያዘ በመኾኑ ታሪካቸውን ማወቅ ዋናው ጉዳይ ነው፡፡ታሪኩን ሳያውቁ መሣል አስቸጋሪ ይኾናል፡፡ኹለተኛው የመሣል ትምህርት መማር ያስፈልጋል፡፡ሥዕል መሣል ስለተቻለ ብቻ መሣል አይቻልም፡፡ታሪክን ማወቅ አስፈላጊ ነው፡፡የዕውቀት ደረጃው የቅኔ ደረጃ ባይደርስም መሠረታዊ የኾኑ የሃይማኖትን ትምህርቶች መማር ዋናው አስፈላጊ የኾነ ነገር ነው፡፡ይኽ ካልኾነ የሚሣለው ሥዕል ይዘቱ የተዛባ ይኾናል፡፡

ትምህርት በተገቢው ኹኔታ ከተጠናቀቀ በኋላ የሚቀጥለው ተግባር የሚኾነው ጸሎት ማድረግ ነው፡፡ንስሓ ገብቶ የሚሠራውን ሥራ ዕውቀቱ የእግዚአብሔር በመኾኑ ዕውቀቱን እግዚአብሔር እንዲያድለው ጸሎት ማድረግ ይገባል፤ምክንያቱም ታሪኩ የእግዚአብሔር ስለኾነ፣ የሚሣለው ሥዕል የቤተ ክርስቲያን ስለኾነ፣በመንፈስ ቅዱስ ለአባቶቻችን የተገለጸው ጥበብ እንዲገለጽለት እግዚአብሔርን በጸሎት መጠየቅ ያስፈልጋል፡፡የሚሣለውን ሥዕል ቅዱስ የሚያሰኘው ፣ለአገልግሎት የሚያለው ራሱ ባለቤቱ እግዚአብሔር ነው፡፡እያንዳንዱ ሥራ የእግዚአብሔር መኾኑን አምኖ መሥራት፣መዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡እነዚኽ ተግባራት ከተከናወኑ የሥዕል ሥራውን መጀመር ይቻላል፡፡

ለሥዕል ሥራ የሚኾኑ የቁሳቁሶችን ቀለም ሲገዛ በአግባቡ ጸሎት ተድርጎ ከተቻለም ለንስሓ አባት ዘንድ በማቅረብ አስባርኮ እና ራስንም በንስሓ ውስጥ አድርጎ ቢሠራ ከእግዚአብሔር ዘንድ በረከትን የሚያስገኝለት ይኾናል፡፡ሌላው ሠዓሊው ያላገባ ከኾነ እና ሕልመ ሌሊት ካጋጠመው የዚያኑ ቀን

መሣል አይቻልም፡፡ገላን በመታጠብ በቀጣዩ ቀን መሣል ይቻላል፡፡በለትዳርም የኾነ ሩካቤ ከፈጸመ ከአንድ ቀን በኋላ ገላን በመታጠብ መሣል ይቻላል፡፡አኹን ባለንበት ዘመን ሴቶችም የሥዕል ሥራውን እያከናወኑ ይገኛሉ፡፡ሴቶች ከኾኑ ደግሞ ልማደ አንስት በሚያጋጥማቸው ወቅት መሣል የለባቸውም፡፡ ከጨረሱ በኃላ መሣል ይችላሉ፡፡

ሊቃውንት(ገዳማውያን)ይሥሉ ነበር፡፡በኋለኛው ዘመን እየዳበረ ከገዳማውያን ውጪ የኾኑ ሰዎች መሣል እንደጀመሩ ይነገራል፡፡ ቅዱሳት ሥዕላት አብዛኛውን ጊዜ በጾም ውስጥ ይሣላሉ፡፡ጾም በማይኾንበት ጊዜ ቁጥብ በኾነ መንገድ ብዙ ምግብ ሳይበዛ በመጠቀም ይሣላሉ፡፡በድሮ ጊዜ በ11ኛው እና 12ተኛ ክፍለ ዘመን ከገዳማውያን ውጪ የኾኑ ሰዎች መሣል መጀመራቸው ይታወቃል፡፡በተለይ በጎንደር ዘመን ሠዓሊዎች ትልቅ ደረጃ ላይ ሲደርሱ አለቃ የሚባል ደረጃ ይወጣላቸዋል፡፡ሥዕል ሲሣል እነዚኽን ቅድመ ዝግጅቶች ያስፈልጋሉ፡፡በይኹን እንጂ አኹኑ ጊዜ የቅድመ ኹኔታው አሳሳቢ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡

## ፩. ፲፮ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሥዕል ከዓለማዊ ሥዕል ጋራ ያለው ልዩነት

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ከዓለማዊ ሥዕሎች የሚለይባቸው በርካታ ርእሰ ጉዳዮች አሉት፡፡መጀመሪያ በዓላማው፣በአገልግሎቱ በርእሰ ጉዳዩ ይለያል፡፡ዓለማዊ ሥዕሎች ርእሰ ጉዳይ ላይ መንፈሳዊ ያልኾነ ሐሳብ ይቀርባል፤የሥዕሉ ባለቤት ራሱ ይለያያል፡፡ኹለተኛው በአገልግሎታት ይለያል፡፡ዓለማዊ ሥዕሎች መንፈስን ለማደስ እንደማስዋቢያ ግብአት ሊያገለግል ይችላል፡፡የቤተ ክርስቲያን ሥዕል ግን ዓላማው መጽሐፍ ቅዱስንና ወንጌልን ማስተማር ሲኾን ከቅዱሳን ጋራ ለመገናኘት፣በጸሎት ጊዜ ለሥርዐተ አምልኮና ለመታሰቢያ አገልግሎት ይውላል፡፡የቤተ ክርስቲያን ቅዱሳን ሥዕሎች በንጹሕ ስፍራ በዓላማ የሚቀመጡ፣ሊጸለይባቸውና ከእግዚአብሔርና ከቅዱሳን ጋራ የምንገናኝባቸው ናቸው፤አክብረን ልንይዛቸው የሚገቡንና ባካበርናቸው መጠን መንፈሳዊ ጥቅም የምናገኝባቸዉ ናቸው፡፡

ዓለማዊ ሥዕላት መንገድ ዳር ሊሠራ የሚችል ሲኾን ሊወይብ እና ሊቆሽሽ ቢችል እንኳን ምንም የሚፈጠር ችግር የለውም፡፡ሦስተኛ ደረጃ የቤተ ክርስቲያን ሥዕሎች በሚሰጡት ጥቅም ይለያያሉ፡፡ቅዱሳት ሥዕላት የምእመናንን ጸሎት በሥዕላቱ ላይ ዐድሮ ቅዱሳን ይሰማሉ ፤ለሚያምን ሰው ኹሉ ቅዱሳት ሥዕላት ተአምር ያደርጋሉ፡፡ለሚያምን ሰው ኹሉ ተአምር ይደረጋል፡፡ብዙውን ጊዜ በቅዱሳት ሥዕላት አማካይነት ተአምር ሲደረግ ከጥንት ጀምሮ የሚነገር ነው፡፡ይኹን እንጂ ለተአምር ተብሎ ቅዱሳት ሥዕላት አይሣሉም፤የተለዩ ናቸው፡፡አራተኛው ቅዱሳት ሥዕላት የሚለዩበት ከዓላማቸው አንጻር የሚውሉበት አገልግሎት ንጹሕ የኾነ

አገልግሎት ላይ ይውላሉ።ዓለማዊው ሥዕል ግን ለእግዚአብሔር የተመረጠ አገልግሎት የለውም፤የእግዚአብሔር ለኾነ ለተለየ አገልግሎት አይጠቅምም፤ንጹሕ አይባልም።ሌላው ደግሞ ቅዱሳት ሥዕላት በሚሣሉበት ጊዜ ጥልቀተ አድማስን፤ጥላና ብርሃን  አይጠቀሙም በዚኽም ይለያሉ።

## ፬. ፲፩ የቀለም አጠቃቀም

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሚዘጋጁ ዋና ዋና የቀለም ዐይነቶች አራት ቀለሞች ናቸው።እነርሱም፡-ቀይ፣ቢጫ፣አረንጓዴና መደብ የለሽ ቀለሞች (ነጭና ጥቁር) ናቸው። እነዚኽ ቀለሞች በጥንቱ ከሣር ፣ከቅጠላቅጠል ከማዕድን የሚዘጋጁቀለሞች ነበሩ፤በቀደመው ጊዜ ከአካባቢ በሚገኙ ነገሮች ይዘጋጁ ነበር።

አኹን ባለንበት ዘመን ግን የፋብሪካን ውጤቶች አገልግሎት ላይ እየዋሉ ነው።ለማዘጋጀት ጊዜ ስለሚፈጅ እና በብዛት ቤተ ክርስቲያናት እየተሠሩ በመኾናቸው ለማዘጋጀት ጊዜ ይወስዳል።ከጊዜ ብዛት ቀለሞቹ ይደበዝዛሉ።ኾኖም በዚኽ ዘመን ለሥዕል ጥንቃቄ እየተደረገ አይደለም፤የቀለም ትውፊት የዳበረ አይደለም።ይኽ ጻድቅ ሲሣል ይኽን ቀለም ተጠቀሙ የሚል የዳበረ ትውፊት የለም።ትውፊቱ በተወሰነ መልኩ አለ፤ምክንያቱም በአካባቢያችን የሚገኙት ቀለሞች የተወሰኑ በመኾናቸው ነው።እመቤታችን በአብዛኛው ቀይ ቀለም ከውስጥ ሰማያዊ ከላይ ለብሳ ትሣላለች።እየዳበረ ሲመጣ አረንጓዴ ተደረገ።በ13ተኛውበ14 ተኛው ክፍለ ዘመን የተሣሉ የእመቤታችን ሥዕሎች ቀይ ወይም ቢጫ ተደርገው ተሥላለች።የራሳቸው የኾነ የአሣሣል ሥርዐት አላቸው።ኹልጊዜ እንደዚያ ተደርጎ ይሣላል ማለት ግን አይደለም ።የቀለም ዕጥረት ስለሚያጋጥም የሥዕል ሥራው እየዳበረ የሚመጣ ይኾናል።

## ፬. ፲፪ ኦርቶዶክሳዊ ትውፊትን ጠብቀው የተሣሉ ሥዕሎች

ትውፊትን ጠብቀው የተሣሉ ሥዕሎች የሚባሉት የቅዱሳኑ ምስል ሲሠራ ታሪኩን መሠረት አድርጎ የተሣሉትን ነው።የእያንዳንዱን ቅዱሳን ታሪክ ማንበብና ማስተዋል አስፈላጊ ነው።በንባብ አማካይነት የትውፊ ትን ዕውቀት ማዳበር ይገባል።

ትውፊትን የጠበቁ ሥዕላትን ማግኘት የሚቻለው የቅዱሳት መጻሕፍቱን ታሪክ ብቻ ሳይኾን የመጻሕፍቱን የአንድምታ ዕውቀት ያለው ሠዓሊ ሲሥለው ነው።ቀደምት ሥዕላት ይኽንን መሠረት አድርገው የሚሣሉ ናቸው፤ነገር ግን በአኹኑ ጊዜ የምንመለከታቸው ሥዕላት በተለይም በከተማ አብያተ ክርስቲያናት የሚታዩ ሥዕላት ከትውፊታቸው ወጥተው የውጪ ሠዐልያን ሥራዎች ተጽዕኖ ያረፈባቸው ናቸው፤ምክንያቱም የሚሥለው ሠዓሊ የድሮውን ስለማያውቅ የሚያውቀው ዓለማዊውን አሣሣል ብቻ በመኾኑ የሚሠራው ሥራ ከትውፊቱ ያፈነገጠ

ኾኗል፡፡መጽሐፍ ቅዱስን ሳይማሩ፣የቅዱሳንን ታሪክ ሳያውቁ፣የቅዱሳንን ትርጓሜ ሳይማሩ የሚናገሩ አሉ፡፡የነበረውን ትውፊት ተጠብቆ ስለማይሠራ የቤተ ክርስቲያኗ ገጽታ እየተቀየረ ነው፡፡የቤተ ክርስቲያኗን አስተምህሮ የማይወክሉ ቅዱሳት ሥዕላት አኹን ባለንበት ዘመን በርካታ ናቸው፡፡

## ፬. ፲፮ የቤተ ክርስቲያን ሠዓሊዎች ኹኔታ

በጥንቱ የትምህርት አሰጣጥ ቤተክርቲያን የራሷ ሠዓሊዎች ነበሯት፡፡ሠዓሊው ጉባኤ ቤቱን እየረዳ ከሥር ከሥር የቅዱሳት ሥዕላትን ታሪክ በማጥናት ሥዕሎችን ይሥላል፡፡ከዚያ በኋላ አስመስክሮ ይወጣ ነበር፡፡

አኹን ያ የነበረው የሥዕል ጥበብ እየጠፋ መጥቷል፡፡ ከአብዮቱ ዘመን ወዲኽ ሠዓሊዎቹ ውጪ ሀገር ኼደው እንዲማሩ ተደረገ፡፡ዘመናዊው የሥዕል ትምህርት መከፈቱ እና ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን የሚሠሩት በውጭ ሀገር ሰዎች በመኾኑ ለውጪ ሀገር ሠዓሊዎች ቅድሚያ ተሰጠ፡፡ድሮ ለሥዕል ሥራው ደጋፊ የነበሩት ነገሥታቱ፣መሳፍንቱ ነበሩ፡፡ነገሥታቶቹ ድጋፍ ስለሚያደርጉ ጉባኤ ዘርግተው ትምህርት መማር ይችሉ ነበር፡፡በመኾኑም ሥዕሉ ትምህርት እየቀረ መጣ፡፡ሠዓሊዎቹም ቃለ እግዚአብሔርን ሳይማሩ የቅዱሳንን ታሪክ ሳይማሩ ብሩሽና ቀለም ይዘው ሥዕል መሣል ጀመሩ፡፡

ትውፊትን ሳይማሩ ሥዕሎችን ስለሚሥሉ ውጤቱ በየቤተ-ክርስቲያኑ ጎልቶ እየታየ ይገኛል፡፡ለምሳሌ የቦሌ መድኀኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን እና የአፍሪካ ደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል በካቶሊክ፣በፕሮቴስታንትና በሰሸን ደይ ድቬንቲስቶች የተሣለ ነው (ቃለ መጠይቅ ሠኔ 20/2015) ፡፡

## ፬. ፲፯ የቅዱሳት ሥዕላት ተአምር

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በርካታ ተአምራት በቅዱሳት ሥዕላት ተአምር እንደተደረጉ እና ተአምር የሚከሠተው በየትኞቹ ሰዎች ላይ እንደኾነ ያመለክታል፡፡የታሪክ ማስታወሻ ኪነ ጥበብ፣ሥነ ጥበብ ፪ኛ በሚለው መጽሐፍ ላይ የቅዱሳት ሥዕላት ተአምር አድራጊነትን እንደሚከተለው ያስረዳሉ፡፡

> በጌታችንና በቅዱሳን ሥዕል ላይ ተአምር ይፈጸማል፡፡መላእክት በሥዕላቸው ላይ ይገለጻሉ፡፡እመቤታችን በሥዕሏ ላይ ትገለጻለች፡፡ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሥዕሉ ላይ ብዙ ተአምር ያሳያል፡፡መንፈስ ርኩስ የሚጋልባቸው ሰዎች ይኽን የመሰለ ተአምር ሊያዩ አይችሉም፡፡ከዚኽ ቀጥሎ የቀረበው ታሪክ ለክርስቲያን ነው፤‹‹እስቲ ይኽን ዛፍ እዘዘው›› ለሚሉ አይደለም፡፡በላይኛው በኤፍራጥስ ወንዝ ኡር በምትባል ከተማ የነገሠና በበሽታ የሚሠቃይ አብጋር የሚባል ንጉሥ ነበረ፤የክርስቶስን ዜና

ሰምቶ መጥቶ እንዲፈውሰው በታመነ አሽከሩ ደብዳቤ ጻፈ፡፡የተላከው አሽከር ሠዓሊ ነበርና ከክርስቶስ ጋራ ሲነጋገሩ የክርስቶስ መልክ በጣም ስለማረከው በወረቀት ላይ ነድፎት ነበር፡፡ኢየሱስ ለታመነው ንጉሥ የሰጠው መልስ እኔ አልመጣም ነው፡፡ግን የሰጠው ተስፋ‹‹እምነትከ አድኅነተከ››ግን ሳታየኝ‹‹አምነኻልና ትድናለኽ››በለው አለው፡፡መልእክተኛው ተመልሶ ትድናለኽ ብሎኻል አለው፡፡በዚኹ ጊዜ ያን የነደፈውን

የኢየሱስን መልክ አሳየውና መልኩን ዐይቶ ተፈወሰ፡፡ ከዚያ አብጋር የኢየሱስን ሥዕል በክብር ሰቅሎ ይሰግድለት ነበር፡ሕህዝቡ ኹሉ ሰገዱለት፡፡ብዙ ሕሙማን በዚያ ሥዕል ተፈወሱ፡፡

በቅዱሳት ሥዕላት አማካይነት ተአምር የሚፈጸምባቸው ሥዕሎች በተለያዩ መጻሕፍት ላይ ተገልጸዋል፡፡ቅዱሳት ሥዕላት አማኞች ፈውስን የሚያኙባቸው በመኾኑ ሥዕላቱ አዘጋጃጀት የሰዎችን ተመስጦ፣ፈውስን እና ሰማያዊውን ዓለም ማሳየት በኩል ከፍተኛ አገልግሎት የሚሠጡ ናቸው፡፡

# ምዕራፍ ዐምስት

## ፭. ማጠቃለያ

ይኽ ጥናት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሚገኙ ቅዱሳት ሥዕላት ላይ የተደረገ ሲኾን ትንታኔው በቅዱሳት ሥዕላት አሣሣል፣አቀማመጥ፣አመጣጥን፣በሥነ ልቡና በንድፈ ሐሳብ ስልት ላይ ተመሥርቶ ተካኺዷል፡፡ቅዱሳት ሥዕላት እንዴት እንደሚሣሉም ጥናቱ አሳይቷል፡፡የጥናቱን ዐላማ ከግብ ማድረስና የምርምር ጥያቄዎችን ለመመለስ ቃለ መጠይቅና ምልከታ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች አገልግሎት ላይ ውለዋል፡፡የቅዱሳት ሥዕላትን አሣሣል በተመለከተ በሥዕል ዐውደርእይ በመሳተፍ፣በተለያዩ መደብሮች የሚገኙ ቅዱሳት ሥዕላትን በመመልከት፣ቃለ መጠይቅ በማድረግ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች አገልግሎት ላይ ውለዋል፡፡መረጃዎቹም በምስልና በድምፅ መቅረጫዎች ተሰንደዋል፡፡በጥናቱ ውስጥ ቀደምት ሥራዎችን በመቃኘት ፣በታተሙና ባልታተሙ ሥራዎች ላይ ቅኝት በማድረግ ፣ያነሡትን ጉዳይ ልዩነትና ተመሳስሎ በዝርዝር እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡በፅንሰ ሐሳብ ደረጃ የሚገለጹ ሥዕላት ምንነት ፣የሥዕል አጀማመር፣ሥዕልና ፎክሎር፣ ትውፊት፣የጥንቱን ኢትዮጵያን የሥዕል ትምህርት አሰጣጥ የሚያሳዩትን የሊቃውንቱን ሐሳብ በማምጣት፣ያነሡትንም ሐሳብ በመግለጽ በዝርዝር እንዲቀርብ ኾነዋል፡፡ቅዱሳት ሥዕላት አኹን ያሉበት ደረጃም ተብራርቶ ቀርቧል፤የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የቅዱሳት ሥዕላት አሣሣል ሥርዐትን ማሳየትም ተሞክሯል፡፡

በምዕራፍ ሦስት እና አራት የጥናቱ ትኩረት የኾነው የቅዱሳት ሥዕላት የትውፊት ምንነት ማብራሪያ በመስጠት ቀርቧል፡፡ይኽ ትውፊትም የቅዱሳት ሥዕላትን አሣሣል የሚመራ በመኾኑ ማብራሪያ ተሰጥቶበታል፡፡የቅዱሳት ሥዕላት አገልግሎት ማስተማር በመኾኑ ሲሣል የቤተ ክርስቲያኗን ትውፊት በጠበቀ መልኩ መኾን እንዳለበት ተመክሯል፡፡የቅዱሳንን ታሪክ መማር፣ቅዱሳት ሥዕላትን ለመሣል ዝግጅት ማድረግ ማስፈለጉ ተነግሯል፡፡ዝግጅቶቹም ጸሎት ማድረግ፣ንስሐ መግባት፣የሚዘጋጁባቸውን ቁሳቁሶች ማስባረክና የመሣል ችሎታ ልምምድ አስፈላጊ መኾኑ ተገልጿል፡፡የቅዱሳት ሥዕላትን አሣሣል ትምህርት በተመለከተ በጥንታዊው የትምህርት አሰጣጥ የተጠናከረ እንደነበር ሠዓሊዎቹ የቲዎሎጂ ዕውቀት እንደነበራቸው የሚሥሏቸው ሥዕሎችም ከቤተ ክርስቲያኗ አስተምህሮ ጋራ የሚጋጭ እንዳልነበረ ተወስቷል፡፡አኹን ባለንበት ዘመን የሚሣሉ ቅዱሳት ሥዕላት ግን የሥዕል ትምህርቱ የተጠናከረ ባለመኾኑና በውጪ ዜጎች የተሣሉ ሥዕሎችን በመገልበጥ በመሠራቱ የቤተ ክርስቲያንን ትውፊት ያልጠበቁ ሥዕሎች እየተዘጋጁ እንደኾነ በዚኽ ጥናት ውስጥ በተደረገው መረጃ መሠረት ለመረዳት

ተችሏል፡፡በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ የቅዱሳት ሥዕላትን በተመለከተ በቂ ትምህርት አለመሰጠቱንና ለቅዱሳት ሥዕላት ክብር አለመደረጉን በተደረገው ምልከታ ማሳየት ተችሏል፡፡ቅዱሳት ሥዕላት በየመንገድ ዳር ላይ ለአቧራና ዝናብ በተጋለጠ መልኩ ለሽያጭ ሲቀርቡ፣በማስታወቂ ሰሌዳ ላይ ተለጥፈው ፀሓይና ዝናብ ሲፈራረቁባቸው እንደነበር በምልከታ ተረጋግጧል፡፡

## አስተያየት

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የራሷ የአሣሣል ዘይቤ ያላት በመኾኑ ወደነበረበት ደረጃ ለመመለስ በቅዱሳት ሥዕላት ላይ ያለውን ጉራማይሌ የኾነውን አሣሣል ማስወገድ ቢቻል፣የቤተ ክርስቲያን ሕንጻ አሠሪዎች ስለቅዱሳት ሥዕላት አቀማመጥ፣ አሣሣል፣ ቅድመ ዝግጅትን በተመለከተ አስቀድሞ ቢታሰብበት፣በየዐውደ ምሕረቱ ፣በሰንበት ትምህርት ቤቶች ላይ ስለቅዱሳት ሥዕላት ትምህርት እንዲሰጥ ቢደረግ፣ የተሻለ ነው፡፡ኦርቶዶክሳዊ ትውፊትን ያልጠበቁ ቅዱሳት ሥዕላትን መቀየር፣ቤተ ክርስቲያኗ የረሷ የኾነ የሥዕል ማተሚያ ቤቶች ብታቋቁምና ትውፊትን ያልጠበቁትን ሥዕሎች ለመለየትና ለመቆጣጠር ቢቻል መልካም ይኾናል፡፡

# ዋቢ መጻሕፍት

ሀብተማርያም ወርቅነህ።(1963) ።ጥንታዊ የኢትዮጵያ ትምህርት።ዐዲስ አበባ፣ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት።

ሐዲስ የሻነው።(2010ዓ.ም) ።ትምህርተ ሕግ ቀኖና ዘኦርቶዶክስ ።ዐዲስ አበባ።

ሕይወት ተፈራ።(2012ዓ.ም) ።ምንትዋብ።ዐዲስ አበባ፣ርኖቦት ማተሚያ ቤት።

መሐመድ ሰይድ።(1997) ።‹‹የነቢዩ የሱፍና የነቢዩ ሙሳ አሣሣል በቅዱስ ቁርኣን››።በዐዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣የኢትዮጵያ ስነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ለድግሪ ሟሟያ ጽሑፍ፣ያልታተመ።

መጽሐፍ ቅዱስ። (1953ዓ.ም) ።የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት።ዐዲስ አበባ፣ብርሃንና ሰላም፣ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ማተሚያ ቤት።

ሚሊዮን በለጠ አሰፋ። (1994) ።ቅዱሳት ሥዕላት።ዐዲስ አበባ፣ባናዊ ማተሚያ ቤት።

ማኅበረ ቅዱሳን። (2002ዓ.ም) ።የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጥናት መጽሔት ቁጥር ፩።ዐዲስ አበባ።

--------------። (1988ዓ.ም) ።ቤተ ክርስቲያንህን እወቅ።ዐዲስ አበባ፣

ሞገስ ዕቁበ ጊዮርጊስ። (1953) (ተርጓሚ) ።አንጋረ ፈላስፋ።ያልተገለጸ።

ሰሎሞን ተሾመ ባዬ። (2011) (ዶ/ር) ።ፎክሎር ምንነቱና የጥናቱ የትኩረት አቅጣጫ።ዐዲስ አበባ።ፋር ኢስት ትሬዲግ ኃላ.የተ.የግ. ማ።

ስርግው ሐብለ ሥላሴ (አዘጋጅ) ። (1969ዓ.ም) ።‹‹የአማርኛ የቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቃላት››። (ያልታተመ)

ብርሃኑ ጎበና። (1985ዓ.ም) ።ዐምደ ሃይማኖት።ዐዲስ አበባ፣ፋር ኢስት ትሬዲንግ።

ታየ ታደሰ። (1976ዓ.ም) ።ስለኢትዮጵያ ሥነ ጥበብ ዕድገት ሴሚናር፣ኤግዚቢሽንና ግምገማ።ኢትዮጵያ ጥናት ተቋም ዐዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ።

ታደሰ መስፍን። (1993ዓም) ።ሥነ-ጥበብ ‹‹ፈጠራ-ባህልና ጊዜ››።በሥነ-ጥበብና ዲዛይን ት/ቤት የተዘጋጀ ሲምፖዚየም።

ኃይለ ማርያም ላቀው። (2002) ።ሐውልተ ስምዕ።ዐዲስ አበባ፣ኤመርሰን ማተሚያ ድርጅት

ኃይለማርያም 2007) ።ኦርቶዶክሳዊ ቅዱሳት ሥዕላት።ዐዲስ አበባ፣ፋር ኢስት ትሪዲግ ኃላ.የተ.የግ. ማ።

----------------- ።(2007ዓ.ም) ።ሥዕለ ቅድስት አርሴማ።ፋር ኢስት ትሪዲንግ ኃላ.የተ.የግ.ማ።

አበራሽ ወ/ኢየሱስ ።(1988ዓ.ም)።እመቤታችንን እንወቃት።ዐዲስ አበባ፣ቦሌ ማተሚያ ድርጅት።
አገኘሁ አዳነ።(2009ዓ.ም)።‹‹ሥዕል፣ሠዓሊነት እና ሠዓሊ ገፀ ባህርያት በተመረጡ የአማርኛ ዘመናዊ ልብ ወለዶች››።ዐዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣የኢትዮጵያ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ ለሁለተኛ ድግሪ ሟሟያ ጽሑፍ፣ያልታተመ
ዓንዱዓለም ዳግማዊ።(2002 ዓ.ም)።ነቅዓ ሕይወት።አዲስ አበባ፣ኤመርሰን ማተሚያ ድርጅት።
ከፍ ያለው መራሒ። (1986) ።የቤተ ክርስቲያን አስተዋጽኦ ለኢትዮጵያ ሥልጣኔ።ዐዲስ አበባ ፣በት.መ.ማ.ድታተመ።
ኪዳነወልድ ክፍሌ።(1948)መጽሐፈ ስዋሰው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ።አዲስ
አበባ፣አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።
ካህሳይ ገብረ እግዚአብሔር።(2008ዓ.ም)።ባህልና ክርስቲያናዊ ትውፊት በኢትዮጵያ።ዐዲስ
አበባ፣ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ
መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን።
ክርስቲን ሻዮት (ተርጓሚ መልአከ ሰላም ዳኛቸው ካሳሁን)።(1999ዓ.ም)።የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ
ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ትውፊት እና መንፈሳዊ ሕይወት።ዐዲስ አበባ፣በኢትዮጵያ
ኦርቶዶእስ ተዋሕዶ በቴ ክርስቲያን በሰንበት ት/ቤቶች መምሪያ።
እንግዳ መርጊያ።(2013)።ቅዱሳት ሥዕላት።ዐዲስ አበባ፣ማህበረ ቅዱሳን ኅትመት አገልግሎት።
የማነ ብርሃን አዲሴ(ትርጉም)። (2006ዓ.ም) ።መጽሐፈ ጤፉት።ግሸን ደብረ ከርቤ ሰበካ
ጉባኤ።
ያለው እንዳወቅ።(2009)።የምርምር መሠረታዊ መርሖችና አተገባበር፣ዐዲስ አበባ፣ንግድ
ማተሚያ ድርጅት።
ይትባረክ ገሠሠ።(1992ዓ.ም)።የታሪክ ማስታወሻ ኪነ ጥበብ ሥነ ጥበብ።ዐዲስ አበባ፣ንግድ
ማተሚያ ድርጅት።
ደስታ ተክለወልድ።(1962 ዓ.ም)።ዐዲስ የአማርኛ መዝገበ ቃላት።ዐዲስ አበባ።አርቲስቲክ
ማተሚያ ቤት።
ጎርጎርዮስ።(1974ዓ.ም)።የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ።ዐዲስ
አበባ፣የኢትዮጵያ ኦርቶዶእስ ተዋሕዶ ቤተ ሐዋርያዊ ድርጅት የሥነ ጽሑፍ ክፍል።
ፈቃደ አዘዘ። (1991ዓ.ም) ።የሥነ-ቃል መምሪያ።ዐዲስ አበባ፣አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።
----------------------።(1973ዓ.ም)።ትውፊትምንድንነው?ያልታተመ።

Danel, Seifemicheal. (2004). Perpect on The Art History of Ethiopian Orthodox Twahdo Church (APANORAMA OF HER INGIGOUS ICONOGRAPHY AND ITS THELOGICAL BACKGROUND).

Dorson, M. Richard. (1972). Folklore and Folklife: An Introduction.Chicago: The University of Chicago Press.

Finnegan, Ruth. ()1992). Oral Tradition and the verbal arts London and Newyork; Routledge.

KOTHARI.Research Methodology Methods & Techniques.India New Age International (P) Limited, Publishers.1990.


Shimlis, Girma. (2008). Servey on Historical and theological Development of Holy icons in Ethiopian orthodox Tewahido church.

Solomon, Hailemariam, (2007). Origin and Development of Ethiopian Orthodox Twahido church iconogy Analysis in relation to Hymnology.

Yeneneh, Demse. (2010). The teaching of the orthodox churches concering holy icon.

## አባሪ ፩ የተለያዩ ፎቶዎች


ከሐመረ ብርሃን የብራና መጻሕፍት ሥራ ድርጅት ባዘጋጀው አውደ ርዕይ በምልከታ የተገኙ እንዲሁም ከሠዓሊ ዘሪሁን ገብረ ወልድ የተገኙ ናቸው።



ቅዱስ ዮሃንስ አፈወርቅ




ልደታ ማርያም



ቅዱስ ዳዊት



አቡነ ዜና ማርቆስ

**አባሪ ፪**

**በጥናት ወቅት መረጃ ለማሰባሰብ ላይ ከመረጃ ሰጪው ጋርና እየተሳሉ የነበሩ ምስሎች፡፡**





**በመረጃ ስብስባ ጊዜ በመሳል ላይ የነበረ ሥዕል**




**አጥኚዋ ከመረጃ ሰጪው ጋር**

**አባሪ ፫ መረጃ ሰጪ**

| ተ.ቁ | ጾታ | ስም | እድሜ | የሚኖሩበት አካባቢ | መረጃውን የሰጡበት ቦታ | ሥራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ወ | ኃይለማርያም ሽመልስ | 32 | አያት | ጣፎ ኮንደሚንየም የሚሰሩብት የሥዕል ፣ሙስሪያ ቦታ | ቅዱሳት ሥዕላት አሳሳል ማስተማር |

### አባሪ ፲ ፣ከትውፊት የወጡ ተብለው ከሚጠቀሱት ቅዱሳት መካከል ውስጥ






ከውጪ ሰዓሊ ተፅዕኖ እየተለመደ የመጣ የሚካኤል ምስልና(ጥልቀት አድማስ ያለው)፣ክርስቶስ መላእክት መቃብሩን ከፍተውለት ከመቃብር ሲነሳ

**አባሪ. ፬ ለመረጃ ለመሰባሰብ የተዘጋጁ ጥያቄዎች**

፩. በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እንዴት ተጀመረ?

፪. የቤተ ክርስቲያን ሥዕል መሣል ማን ጀመረው?

፫. ሥዕል በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ውስጥ ምንድን ነው?

፬. ሥዕላትን ለመሣል የሚያስፈልጉ ቅድመ ኹኔታዎች ምን ምን ናቸው? የሚሥለው ሠዐሊ ምን ማድረግ አለበት? እንዴት ይዘጋጃል?

፭. የቤተ ክርስቲያን ሥዕላት ከሌላው የዓለማዊ ሥዕል በምን ይለያሉ?

፮. ቀለማት እንዴት ይዘጋጃሉ? የቀለሞቹ ዓይነትስ ምን ዓይነት ናቸው?

፯. ቀለሞቹን ለየትኞቹ ሥዕላት(ቅዱሳት)እንጠቃማለን? ለክርስቶስ፣ ለማርያም፣ ለሰማዕታት፣ ለነቢያት ሐዋርያት መላእክት ምን ዓይነት ቀለም እንጠቀማለን?

፰. የቅዱሳት ሥዕላት የአሣሣል ሥርዐት እንዴት ነው?

የማርያም (ስደቷን፣ልደቷን፣እረፍቷን፣እርገቷን፣ትንሳኤ፣ባእታ ለማርያም፣ኪዳነ ምህረት፣ምስለ ፊቁር ወልዳ እና በላኤ ሰብን ስታማልደው) የኢየሱስ ክርስቶስ (ልደት፣ ጥምቀት፣ ደብረታቦር፣ሆሳእና፣ምሴተሐሙስ፣ስቅለት፣ትንሳኤ፣እርገት እና ዳግም ምጽዐት) ፣የሥላሴ፣የቅዱሳን(ከሐዋርያት)የነቢያት፣ከሰማዕታት(የቅዱስጊዎርጊስናየእስጢፋኖስን)፣ቅዱሳንት አንስት እና የመላእክት (የቅዱስ ሚካኤል እና ቅዱስ ዑራኤል) እንዴት ይሣላሉ?

፱. ከቅዱሳን ሥዕላት የሚገኘው ጥቅም ምንድን ነው?

፱. ከቅዱሳን ሥዕላት የሚገኘው ጥቅም ምንድን ነው?

፲. የቅዱሳን ሥዕላት የአቀማመጥ ሥርዐታቸው እንዴት ነው? ማለትም በቤተ ክርስቲያን እና በግለሰብ ቤት የአቀማመጥ ቅደም ተከተል አላቸው ወይ?

፲፩. ቤተ ክርስቲያን የራሷ የኾነ ሠዐሊያን አሏት ወይ?

፲፪. ትውፊት ምንድን ነው?

፲፫. ትውፊትን ጠብቀው የተሣሉ ሥዕሎች እንዴት ያሉ(የትኞቹ) ናቸው?

፲፬. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሥዕለ አድህኖ የአሣሣል ትምህርት ይሰጣል ወይ? ከተሰጠ ደግሞ የሥዕል ትምህርት ቤቱ ከጥንት ጀምሮ እስከ አኹን ያለበት ደረጃ ምን ይመስላል?

፲፭. የምዕራባውያን(የሮማ፣የባዛይታይን፣የቅብጥ) እና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የአሣሣል ሥርዐት ልዩነቱ ምንድን ነው? ልዩነቱ እንዴት ተፈጠረ?

፲፮. አኹን ባለንበት ዘመን የሚሰሩ አዳዲስ ቤተ ክርስቲያን የሚሣሉ ሥዕሎች እና በቀድሞ ጊዜ ከተሰሩት ሥዕሎች ጋራ ሲታይ የአሣሣል ልዩነት ይታያል፡፡ይኽ ልዩነት እንዴት ሊፈጠር ቻለ? ምክንያቱ ምንድን ነው?

፲፯. በቅዱሳት ሥዕላት ላይ የሚዘጋጁ አጫጭር ጽሰሑፎች ዓላማ ምንድን ነው?